ዲጓ ንዲ Dinq

Distributed in Atlanta/Denver/DC/Nashville/Dallas/Jaksonville
SanDiego/ Alexandria/Phoenix /Vegas and Seattle .Coming soon >> Maryland

Editorial የኛ ደምጽ

አንኳን ለጥር ወር አደረሳችሁ !

ጥር ወር በአገራችን የሠርግ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ስርጋችሁ ለምታደርጉ በሙሉ መልካሙን ሁሉ እንመኛለን። ትዳር ቀላል ጉዞ አለመሆኑን የምታውቁ ይመስለናል። አልጋ ባልጋ የሆነ ነገር አትጠብቁ። ቢሆንም የሚመጣውን ችግር አየተቋቋማችሁ የአብርሃምና የሣራ ጋብቻ እንደምታደርጉት ተስፋ አለን።

ይህ ወር ለፈረንጆቹም የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ወቅት ነው። ሮም ስትኖር አንደ ሮም ሁን ነውና አኛም መልካም አዲስ ዓመት መባባላችን የማይቀር ነው። ከዚያም አልፈን በጀት የምናወጣው፣ አዲስ ነገር የምናትደው ሁሉ በአገሩ ቀን መቁጠሪያ ነው። መልካም ነገር እትደን፣ በተግባር የምንፈጽም ያድርገን። ይልቁኑም በመንፈሳዊውም ይሁን በፖሊቲካው ፣ በማህበራዊውም ይሁን በቤተሰብ መካከል የሚታዩ ውጥረቶችና የከረሩ ግጭቶችን የምንፈታበት ዓመት ይሁን። ግጭት የሚፈታው አንዱ ወገን ሲያሸንፍ ብቻ አይደለም። ተሸናፊውም አምኖ ሲቀበልና ያስፈውን ረስቶ ወደፊት ማየት ሲጀምርም ነው። ለዚያ አንዚጋጅ።

አዲስ ዓመት ሲመጣ በጀት እናወጣለን ብለናል። በርግጥ ግን እናወጣለን? በዓመቱ ውስጥ የምናደርገውን የምንገዛውን፣ የምንለግስውን ቀድመን አውቀን ፣ በገቢያችን መጠን ልክተን እንዚጋጀለን? ብዙዎቻችን ያንን አናደርግም። ማህበራዊ ትሥሥሮቻችን በማም በመብዛታቸው፣ ርዳታ ጠያቂውም በመጨመሩ ያለ በጀት አየኖርን አየተማረርን ነው። በዚህ ወር የወሩ ጉዳይ ይህንን አናያለን።

በየክተማው ያላችሁ የድንቅ አንባባዎች ለአስተያየትና ጥቆማችሁ አናመሰግናለን። ባለሙያዎች ዕውቀታችሁን አካፍሉበት፣ አንባቢያን ደግሞ በምትሄዱባቸው ባለሙያዎች ዘንድ ሁሉ "በድንቅ መጽሔት አስተዋውቁ" አያላችሁ ንገሩልን። በነጻ መጽሄታን ለማደላችን ክፍያው ይህ ይሆናል።

መልካም አዲስ ዓመት ፣ በዓለም ላይ ምርጥ የሆነውን ሁሉ ለናንተ ለአንባቢያን ተመኝን። ቸርስ !!

ማዉጫ INDEX

BUSINESS CATAGORY PAGE

Auto Service	33/35	Restaurants/Mart/ Stores/	
Bakery (Cake)	25	.....lounge	9– 33
Construction /Heating/		School	31
Plumbing/ Electric	52/53	Shipping	28/56
Computer school ,,,,,,,,,,,,,	80	Singer /wedding	72
Funeral home	80	Sound System	72
Driving School	36/38	Tax and Accounting ..	64-69/73
DUI school	6	Travel Agents	54– 57
Electronics / Luggage	43	T shirt print	68
Game Machine	28	Towing	39
Gift to Ethiopia	20	Video, Decor, wedding hall,	
Hair salon /barber	58-63	and Photo > singer » middle	
Insurance	62-65 /60-68	pages, ... 43-47/71	
Lawyers		ARIZONA Classified 94	
..... Inside cover/ 4/72		....	
Medical, Dental, Chiro.		BLUE PAGE - 70	
..... 75-85/ Inside back cover			
Pharmacy	64		
Money transfer	3/ 71		
Real Estate//Mortgage	40- 41		

ዐምዶች

Better life10 / የወሩ ጉዳይ 11....

አንድ ለመንገድ 12
ከአሃፊያን አምባ ... 14.....
Humor 16..... አስትሮጂ 18
የአንሰሳት ዓምድ 22 ..ልቦለድ 27/29 .
African News 30 ...
ቅምሻ 36/37 ስፖርት 44
የጤና ዓምድ 46 አጫጭር
ዜናዎች 50 ... ከወደ ሃይሌ 52
Dating Corner 56 / 61.....
ቆይታ 65 .....የፎቶ ማህደር 66
ፍልስፍና 69 .....
አንድ ጥያቄ አለኝ 73 ...
ከለታት አንድ ቀን 73....
የወሩ አንግዳ 74 ..
ሬት ለፈት 77 .. ቅኝት 79.....
Kids/Parents page 82
ዝክረ ታሪክ 84
ጠብታ ማር / ጠቃሚ ስልክ
ቁጥሮች 88

Editor:
Tewodros Haile .
Asst. editor:
Tariku Tesemma
Graphic Design
Fasika Negatu: ,
Ethiopia representative: Firew Alyo
Contributors:-
Dr. Ephrem Mekonnen ,Haile kas.
Daniel Kibret Tsege Aynalem.
Merhawit Tesfa. Kebede Haile
Naome Seifu. Mistre Aderaw
Gemoraw
Advisors:
Endeshaw Worku
Tesfaye Haile.
Melkamu Demissie.

በዚህ መጽሔት ላይ የወጡ ጽሑፎችንም ሆነ ማስታወቂያዎች ያለ አዘጋጁ ፈቃድ በይም ምንም ሳይጠቅሱ ዝብብ መውሰድከልክ ያለመ የማስታወቂያዎቹ ባለቤት አስተዋዋቂዎች እን ድንቅ መጽሔት አይደለም።
All articles and advertisement de in this magazine are copyrighted unauthorized duplication of them is forbidden.
Contents on each and every ad is a responsibility of the magazine. but the advertiser

Main office: 404 394
Fax/Tel:- 404 92
Ethiopia:- 0911 9

dinqmagazine@gmail.
2791 Clairmont rd. st.
Atlanta, GA 3
www.dinqmagazin

dinq ethiopian magazine dinqmag

facebook



በጀትና ዕርዳታ ያልተነገረው ታሪክ

በጀት ማለት ዕቅድ ሲሆን፣ የሚሰራው ግን ለገንዘብ ነክ ነገሮች ነው። ለመዝናኛ በጀት ሊያዝ ይችላል። ለርዳታ በጀት ሊያዝ ይችላል፣ ለምግብ በጀት ሊያዝ ይችላል፣ ለየለት ለት እንቅስቃሴ በጀት ሊያዝ ይችላል።

ሰዎች በጀት የሚያወጡት በሥርዓት ኑሯቸውን ለመምራት ነው፣ ካቅም በላይ የሆነ ነገር ውስጥ ገብተው ኋላ መውጫው እንዳይጠፋቸው ነው። ከዓመቱ ቀናት ሁለት መቶውን አሸሼ ገዳሜ ብለው የቀረውን 165 ቀን መውጪ መግቢያ እንዳያጡ ነው። ጥሩ ገቢ ያለው ዘና ያለ ኑሮን ሊያቅድ ይችላል። ክሌለን ደግሞ ቁራሽ ልናቅድም አንችልም።

አብዛኛዎችን ኢትዮጵያውያን ኑሯችን ሲታይ የቸገረን አይመስልም። መዝናናት እናውቅበታለን - በየቀኑ። ረድቶን የሚያልቅ አይመስልም - በየሳምንቱ ለመጣ የርዳታ ጥያቄ ሁሉ ሰጪ ነን። በአዳራሽ መካከል አስቲ አዋጡ ሲባል አንድ ሺ ብር ሰጥተን ስናሰጨበጭብ በፈገግታ ነው።

ግን በርግጥ ናሮን ነው? ወይስ በዕቅድ ስለማንኖር? ላንኖር ከሆነ በአደባባይ ሰጪ መመስሉ ለምን? ያበሻ ይሉኝታ?

ይህንን ድክመታችንን የሚያውቁ ደግሞ በተለያየ ሰም፣ በተለያየ መድረክ ርዱን፣ ትኬት ግዙ፣ ለፖንሰር አድርጉን፣ መዘተ. እያሉ ያጣድፋሉ። ስንቶቻችን ለጭብጨባ ወይም "ክፉ ላለመባል" ፈርተን ሰጥተን የመብራት የምንከፍለው አጥተናል? ምርጌጅ የምንከፍለው አጥተን ቤታችን ተወርሶብናል? ወይም ኑሯችን አንደ አደባባዩ ሳይሆን፣ ክአጅ ወደ አፍ ሆኖብናል? ከልጆቻችን አፍ ቀምተን አየሰጠን ልጆቻችንን ጎድተናል?

አውንም የምናወራው ኖሯቸውና ተርፏቸው ስለሚሰጡት አይደለም። የምናወራው ስለኛ እና ስለ አናንተ ያለ አቅማችን በአደባባይ ለመወደስ ወይም "ከሰው ላለመለየት" ወይም "ስማችን እንዳይጠፋ" ወይም ከንቱ ውዳሴ ፈልገን ስለምንሰጠው አንጂ።

አግዚአብሔር ለሰው ልጅ ስለሚያስብ በመንፈሳዊው በኩል የጠየቀን ክአሥር አንድ ነው። ዘጠኙን አምጡ ቢል ኖሮ ምን እንሆን ነበር? ታዲያ ፈጣሪ አንደዚያ ሲያስብ አኛ ለዓለማዊው መዋጮ ያለ አቅማችን እና ያለ ዕቅዳችን ከአሥር ፣ አምስት እና ስድስት የምንሰጠው ምን መሆናችን ነው?

የሚገርመው እንዳንድ ርዳታ ጠያቂዎች፣ መንፈሳዊውም ቦታ ይሁን ዓለማዊው ቦታ ገንዘብ እንደሌላችሁ እያወቁ፣ የምትሰጡት ያለ አቅማችሁ እንደሆነ እያወቁ፣ "ግደለም ያንተ አንኳን ይቅር፣ ለራስህስ ምን አለህ? ቤትህ መኪናህ፣ ሶፋና ጠረጴዛህ ሁሉ በብድር አይደል አንዴ የተገዛው? ደግሞስ በቅርቡ አይደል አንዴ መንታ ልጅ የወለደከው፣ ብዙ ወጪ ይጠብቅሃል አኮ፣ ያንተ አንኳን ይቅር፣ ባይሆን ለበረከቱ ይቺ ትበቃህለች ብለው ከአሥር ነጥብ አምስት በመቶ (1/2 %) ዝረ ይሁን 1% አንኳን አይጠይቁም። መቅሰብ ነው።

አንዲህ ዓይነት አሰራር መቀጠሉ ለማህበረሰቡ አይጠቅምም። አትላንታ አንኑር ራሳይልራይ፣ ዲሲ አንኑር ራኒክስ፣ ዲንቨር አንውን ሲያትል ያው ነው።

አንደሚታወቀው የመዋጮው ዓይነት ብዙ ነው። የመንፈሳዊ ቦታዎች ሀንጻ ማሰሪያ አንዳለ ሆኖ (በየክተማው የሚያቋርጥ ጥያቄ መሆኑን የሚደርሱን መረጃዎች ያሳያሉ)፣ ለሰቅሶ፣ ለክርስትና፣ ለልደት፣ ለምርቃት ሥነ ሥርዓት፣ ለበጎ አድራጎት፣ አገር ቤት ላሉ ህጻናት መርጃ፣ ለአንትን የፖለቲካ ድርጅት ርዳታ፣ ለሬዲዮ ጣቢያዎች ርዳታ፣ ለምናምን አንዲሆን ተብሎ ለሚከፈት የጎ ፈንድ ሚ አካውንት ፣ ተቸግሮ መንገድ ላይ ለወደቀ ሰው ... ወዘተ. ዓይነቱ ብዙ ነው።

ንግድ ቤት ያላቸው ደግሞ ከግስበብ አልፎ የንግድ ወጪም ይጠየቃሉ። ዓይተውና ሰምተው ለማያውቁት ድርጅት ሁሉ ፣"አምቢ የማይባሉ ሰዎች" ይላኩባቸውና ስፖንሰር አድርጉ ይባላሉ።

አነዚህን ጥያቄዎች መቀቸታችን አይደለም። ብዛትና ዓይነታቸውን

ወደ ገጽ 80 ዘርል

አንድ ለመንገድ ማነው?

ገመራው ዘደቡብ አትላንታ

አንድ ሰውዬ ሚሰቱ የመሰማት ችሎታዋ ከቀን ቀን እየደከመ በመምጣቱ በጣም ይጨነቃል። ስለዚህ ወደህኪም ሄደ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ መሆኑን ያምንበታል።
አንድ ቀን ወደ ሐኪም ይሄድና አነዲህ ሲል ይጠይቃል።

"ዶክተር፤ አንድ ትልቅ ችግር ገጥሞኝ ነው የመጣሁት.."
ዶክተሩም፤ "ምን ችግር ገጠመህ?" ሰውዬውም "ባለቤቴ የመሰማት ችግር እንዳለባት አውቅ ነበር፣ አሁን ግን ከቀን ወደቀን ችግሯ እየተባባሰ መጣ"
"ለምን?.." ዶክተሩ ጠየቀ።
"ለምን እንደሆነማ አላውቅም። ግን ብሶባታል። ያንን እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር አችላለሁ። በጣም አስጨንቆኛል ነገሩ።"

ዶክተሩም፤ "ወደሌላ የህክምና ደረጃ ከማለፌ በፊት አንድ የፍተሻ ሙከራ ማድረግ ይኖርብኛል.."
"ምን ዓይነት ፍተሻ ዶክተር?"
ዶክተሩ፤ "ልነግርህ ነው። አንተ ብቻ እኔ የምነግርህን ነገር ሄደህ አቤትህ ትፈጽማለህ"
"መልካም እንዳሉኝ እደርጋለሁ። ብቻ ክትሚ በላይ አንዳይሆን ዶክተር" .....
"በጭራሽ ክቅምህ በላይ አይሆንም። ማንም በቀላሉ ሊሠራው የሚችለው ነገር ነው።"

"እሺ ምን ማድረግ አለብኝ?"
"ቤት ትሄድና ክባለቤትህ ጀርባ በተለያየ ርቀት ላይ አየቆምክ፤ ጥያቄ ትጠይቃታለህ.."
"ምን ዓይነት ጥያቄ ነው የምጠይቃት?"
"የፈለከውን"
"በጣም ጥሩ። በምን ያህል ርቀት ላይ ልቁም?"
"በመጀመሪያ በአሥር ሜትር ርቀት ላይ ቆመህ ትጠይቃታለህ.በጂ.."
"ቀጥለህ በአምስት ሜትር ርቀት ላይ ትቆምና ትጠይቃለህ"
"በጂ.."

"በመጨረሻ፤ በጣም ቀርበሃት ከጀርባዋ ትቆምና ትጠይቃታለህ"
"እሺ ዶክተር ያሉኝን እደርጋለሁ።"
ሰውዬው የዶክተሩን ምክር ይዞ ወደቤቱ ይሄዳል። ባለቤቱ ወደ ምድጃው ፊቷን አድርጋ ምግብ ትሠራለች።
ስለዚህ ከጀርባዋ በጣምት አንድ አሥር ሜትር ርቀት ላይ ቆመና "ውድ ባለቤቴ፤ ዛሬ ለአራት ምን አዘጋጀሽልኝ?." ሲል ይጠይቃታል።
ምንም መልስ የለም።

ወደ አምስት ሜትር ያህል ይጠጋና ደግሞ ይጠይቃል-
"ውድ ባለቤቴ፤ ዛሬ ለአራት ምን አዘጋጀሽልኝ?.." አሁንም ምንም መልስ የለም።

በመጨረሻ አጠገቧ ደርሶ ከጀርባዋ ይቆምና፤ "ውድ ባለቤቴ፤ ዛሬ ለአራት ምን አዘጋጀሽልኝ?" ይልና ይጠይቃታል።

ባለቤቱም ወደ አሱ ዘወር ብላ "ለሦስተኛ ጊዜ መናገሬ ነው - ሹሮ እየሠራሁ ነው አልኩህ! አኮ!.." አለችው በቁጣ!

ለካ መስማት አያቃተው ያለው ራሱ ባልየው ናሯል!

ዛሬም አኛ እያወራን የማንደማመጥ፣ እየተነጋገርን የማንግባባ ሆነናል። በጣም ቀላል ነገር እየነገራችሁት የማይረዳ ሰው አጋጥሟችሁ እያውቅም? ያ አኮ ከአውቀት ማነስ አይደለም— ይልቁኑ ካለማዳመጥ አንጂ።

አንዳንዴ ደግሞ ያልገባን አኛ ሆነን፣ የማናዳምጠው አኛ ሆነን፣ ለፍቅር ፣ ለአንድነት ያልተዘጋጀነው አኛ ሆነን፣ ቂምና ጥላቻ፣ ምቀኝነትና ክፉ ሃሳብ ያለብን አኛ ሆነን ሳለ፣ የምንከሰውና የምንወቅሰው ሌላውን ነው። አስቲ ራሳችንን እንፈትሽ? ጆሯችን ይሰማል? አይናችንስ ያያል?



ከመሬያን አምላ

(በዕውቀቱ ሰዩም)

ክብደትን የመቀነስ ፕበብ
(ካልፎሂያጂ ማስታወሻ የተቀነጨበ)

ያኔ ባቡር ላይወጠን- የሃያ ሁለት ማዞርያ አየር ባስመረት ሽር ሳይታጠን -ዓባይን የደፈረው መሪ (ሆስኒ ሙባረክ) ሳይከነበል- ታምራት ገለታ ቃሊቲን ሳይዳበል- ታምራት ላይኔ ጌታን ሳይቀበል- ካገር ወጣሁ።

አሜሪካ እንደገባሁ በመጀመርያ የፈጸምኩት ተግባር ቢናር መውፈር ነው። አትፍረድብኝ። አሜሪካ ውስጥ ሰው መንቀሳቀስ እቁሟል። ኑሮ ማለት ከሰፋ ወደ መኪና ፤ከመኪና ወደ አማንሠር መንፏቀቅ ማለት ሆኗል ። ሁሉ ነገር የሚፈጸመው online ነው። ያሜሪካ ገበሬ ራሱ የሚያርሥና የሚያጭድ በላፕቶፑ ይመስለኛል፤ "ገብስዎን ለማጨድ ከፈለጉ አልቢን ማጭድ የሚለው ላይ ክለክ ያድርጉ " የሚል ላፕቶፕ ላይ ተጥደ አየሞለ፤ ገበሬ ነኝ የሚል ስንት ፈረንጅ አለ (ሳልፈልግ ገጠመብኝ)

የሆነ ጊዜ ላይ፤ በዩንበርሲትያችን ውስጥ በሚገኘው ጂም ተመዝግቤ ስፖርት መሥራት ጀመርኩ።

መሮጫ ማሽኔ ላይ ዱብ ዱብ እያልሁ፤ ካጠገቤ ባለው ማሽን ላይ ከሚሠሣረው ናይጀርያዊ ጋር ሲያቀብጠኝ ራሴን እወዳድራለሁ ። መጀመርያ የብሄራዊ ስሜት እየገፋኝ(ከአበበ ቢቂላ አገር መጥቶ እንዲት በቀላሉ ያለከልካል እንዳልባል) ጥርሴን ነክሼ አሄን ሩጫ አስነካሁት ።

እግርና ሳንባ ለብሄራዊ ስሜት ግድ እንደሌላቸው ያወኩት ሃያ ደቂቃ ከሮጥኩ በኋላ ነው። ሰው ያበበ ግደይን ተስጥኦ ይዘ እንደአበበ ቢቂላ ካልሆንኩ ብሎ ይማሚቃል? ድንገት ትንፋሼ ብትን ብትን ይላል። የእንግላል እንዳልወድቅ የማሽኑን መደገፍያ አመረኮዛለሁ ። ጥቂት ቆይቶ ራሱ ናይጀርያዊውን ሰውየ አደገፈለሁ። ናይጀርያዊው ሁለት እግር ያለው ፈረስ ማለት ነው። የማሽኑ ሞተር ክጠፋ በኋላ እንኳ መሮጡን አያቆምም። በኋላ በጣም መረረኝ።

ትንሽ ፈርገጥ ፈርገጥ ካልኩ በኋላ በጀሙ አዳራሽ ውስጥ በተሰቀለው ቲቭ ላይ የሚተላለፈውን ፊልም ስመለከት ውየ ወደ ቤቴ መመለስ ጀመርኩ ። ለኔ ጂም ቤት መግባት ማለት የስፖርት ቱታ ለብሶ ሲኒማ ቤት እንደመግባት ሆነ።

ደሞኮ አሳፍርም፤ አንደ ሰዎች ሴክስ. ሆኖ መታየት ያምረኛል። ሳፕቶፔ ላይ ቦርጭ የሚያጠፋ ሶፍትዌር ጭኘ ፤ ፎቶዎቼን ሽንቶጥ እያደረግሁ ፌስቡክ ላይ መለጠፍ ጀመርኩ። ምን ዋጋ አለው። ባለፈው አንዱ ከኔ ጋር የተነሣውን ፎቶ አንደወረደ ለቀቀው።

ዘውዳለም ታደሰ የተባለ ያዲሳባ ተራቢ ያን ፎቶ አይቶ "አሪ የኪንያ ፖሊስ መሰልክ "ብሎ ከተረበኝ በኋላ የገዛ ሰውነቴ አንደ ወህኒቤት ዩኒፎርም ቀፈፈኝ። የኪንያ ፖሊስ ይሄን የበቶሎ ግንፎ አየነፋ ፤አንደ ዋርካ ስለሚሰፋ ሌባን መጠቅም አንጂ ሌባን አባርሮ መያዝ አይችልም ይባላል።

ምነው የማይመለከትህን- የኪኒያ ፖሊስ ላይ ችክ አልህ? አለኝ አንዱ አሁን በኢኖቦክስ ። እና ሃያ ሁለት ማዞርያ አየኖርኩ ፤ ሰማንያ ዓመት ለመኖር አያቀድኩ፤ ያዲሳባን ፖሊስን አንድተች ትጠብቃለህ?)

አገሬ በገባሁ በሳምንት ጊዜ ውስጥ ዘጠኝ ኪሎ ቀነስኩ። ሽገር ውስጥ ያ ሁሉ ክብት አያለሁ ፤ያ ሁሉ ሥጋ አየተበላ ሰው የማይወፍርበት ምንያት የገባኝ አሁን ነው።

ያዲሳባ የኑሮ ውጣ ውረድ በራሱ የማይፎረሽበት ጅም ነው ውንድሜ ። መታወቂያ ለማውጣት የሆነ ቢሮ ሂድ። የሆነች ሴትዮ ትቱበልህና " ሁለተኛ ፎቅ ሄደህ ክፈል" ትልሃለች ። አየተቅመደመድህ ትወጣለህ። አዚያ ስትደርስ አንዱ ይቱበልህና " ይሀን ደረሰኝ ይዘህ አራተኛ ፎቅ ላይ የሚገኘው ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ሂድ ፤ ማህተም ያደርግልሃል" ይልሃል። አደለከለክህ አዚያ ስትደርስ፤ የባለማህተሙ ጸህፊ ትቱበልህና "ሥራ አስኪያጁ ለሥራ ውጥተዋል። አስኪመለሱ ድረስ ሰባተኛው ፎቅ የሚገኘው ካፌ ሽይ ቡና አያልህ ቶይ "ትልሃለች ።

ያዲሳባ ፎቅ ለወጉ ሊፍት ተገጥሞለታል። ግን ሊፍቱ ጥቂት ሠርቶ በመብራት ኃይል ስፖንሰር አድራጊነት ወደ አቃ መጋዘንነት ይቀየራል። ሰባተኛው ፎቅ ላይ አስክትደር አንድ ምሰት ኪሎ ቀንሰሃል። እና አዛ ቁጭ ብለህ ሻይህን ፋት አያልህ "እተት ሰባት ሰዎችን ገደለ" የሚል ዜና ሲተላለፍ በቲቪ ታያለህ። ሰምንተኛው ያተት ስማለት አንተ ልትሆን አንደምትችል ቃሰብና በሰጋት ሌላ ሁለት ኪሎ ትቀንሳለህ። ከዚህ ሁሉ ወደ ጎረቤት አገር ዞር ብየ ለአናት አገሬ ብተርፍላት አይሻልም? ብለህ ማሰብ ትጀምራለህ። የህይወቱ ቤዛ፤ አንደምነሽ ቪዛ?

ቪዛ ሰል የሚከተለው ትዝ አለኝ። የሆኑ ሽማግሌ አንደነገሩኝ በኃይለሥላሴ ጊዜ ላንድ ኢትዮጵያዊ ቪዛ ማግኘት፤ ወደ ፍኖተ ሰላም የሚሄድ አውቶብስ ትኬት ከማግኘት በጣም ይቀል ነበር።

ሽሮሜዳ አካባቢ በአግርህ አየተንሸራሸርህ ትንሽ ካካፋ ዝናቡ አስኪያባራልኝ ለምን ቪዛ አልጠይቅም ? ብለህ ወደ አሜሪካ ኢምባሲ ጎራ ማለት ነው። አምባሳደሩ በቢሯቸው ተቀብለውህ አሪፍ ቡና አየጋበዙህ ኩኪሱን ገፋ አያደረጉልህ " አንተ ጠሣት ኢትዮጵያዊ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ስለፈቀድህ በጀን ኤፍኪኒዲ ስም የተሰማኝን ደስታ አገልጽልሃለሁ። የማትቸኩል ከሆነ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። ለመሆኑ ቪዛውን የት ላይ ብመቃልህ ትመርጣለህ? ፓስፖርትህ ላይ ወይስ የቀበሌ መታወቂያህ ላይ ? " አለቀ።

ዛሬ የኢምባሲ ጥያቄዎች ምን ብለን ጠይቀን እንጣለው የሚሉ ነው የሚመስሉ ። ስምሌሌ የቺስታ አገር ዜጎች እንደሆንና ገንዘብ ለመሥራት እንደምንሄድ አያወቁ የባንክ ደብተራችንን ለምን አንደሚጠይቁን አይገባኝም። የዛሬ ምናምን አመት ክበበው ገዳና ተስፋየ ካሳ ከኢምባሲ ኢምባሲ ይንከራተቱ ነበር። እንዴ ፤ ጀርመን ኢምባሲ ገብተው ጥያቄ በጥሩ መንገድ ሲለመልሱ ክቆዩ በኋላ "ተቀማጭ ገንዘብ ካላችሁ ልታሳዩ ትችላላችሁ?" ስትል ጠየቀች ጀርመኒቱ።

ተስፋሽ ፈጠን ብሎ መለሰ። " "ጀርመን ደርሰን ስንመጣ ማሳየት እንችላለን?"

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለቱ ቺስታ ክመ ድ ያ ና ች እንደ ማ ሽ ላንገታቸውን ደፍተው ከኢምባሲ ወጡ። ያካባቢው ጎረምሶች ከበቧቸው።

"ስሚችሁ ? ስሚችሁ ? " አሉ ጎረምሶች።

"አዎ" አለ ክበበው አንገቱን እንደደፋ " ፓስፖርታችንን ሰጡን!! "

-በጀኔሬተር የሚሰራ ጀኔሬሽን
ካልፎሂያጂ ማስታወሽ የተቀነጨበ
ሰዋንቃቄ ሲባል በብእር ስም የተፃፈ (ከቤኩምሳ ሰዩም)
የሆነ የድሮ ዘፈን ትዝ አለኝ:: ዘፈኑ፡ "በጎፈራው ማህል I ሚደውን ስክቶ" .. አይሂ "በድልድል ጫንቃው ላይ አልቢኑን አንግቶ" .. አይሂ እያለ ይወርዳል::
የድሮ ጉብል ሲያንጣጥር ፤ሲተኩስ፤ሲመታ ሲገድል ስለሚውል በምን ጊዜ እንደሚያፈቅር አይገባኝም::
የድሮ ሰዎች ያለ ትግል መኖር እንደማይችሉ ስመረዳት የሚፈልግ የጦርነት ዘፈኖችን መስማት አይጠበቅበትም:: የሰርግ ዘፈኖችን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው:: አሁን ሰርግን በመስለ የፍቅር መደረክ ላይ " አናስገባም ሰርገኛ አደጅ ይተኛ"ብሎ ነገር ፍለጋ ምንድነው:: ይሄ አኮ" የማክበር ሰላ-ምታ-ችንን እያቀረብን ፤ በልጃችን የሰርግ ስነስራት ላይ ያዘጋጀነውን ዱላ እንዲቀምሱልን እንጠይቃለን" የሚል መጥርያ እንደመላክ ነው:: (ማህበረሰቡ ለድብብ ያለውን ፍቅር ለማወቅ የሚፈልግ ሰው "አስክስታ ምታ፤ ቤት ምታ "የሚሉ ቃላትን መ መ ል ከ ት ይ ች ላ ል :: የሚገርመው፤"ስላምታ"በሚለው ቃል ውስጥ ራሱ "ምታ"የሚል ቃል መገኘቱ ነው)
ኮኔክሽን ያላችሁ እንደምናችሁ !! እኔ ጉንፋንና ኮማንድ ፖስቱ ሰንገው ይዘው ያናፍጡኛል:: የድሮ ጉንፋን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም:: ድሮ ጉንፋን ሲይዘን

ወደ ገጽ 20 ዘርል

-ባእንሰሳት ዓለመ ዶሮ



ዶሮ በምድር ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የወፍ ዘር ሳይሆን አይቀርም። በእጠቃላይ ከ13 ቢልዮን የሚበልጡ ዶሮዎች እንዳሉ ይገመታል! እንዲሁም ሥጋው በጣም ተወዳጅ በመሆኑ በየዓመቱ ከ33 ቢልዮን ኪሎ ግራም በላይ ለምግብነት ይውላል። ከዚህም በተጨማሪ ዶሮዎች በዓለም ዙሪያ በእንድ ዓመት ውስጥ 600 ቢልዮን ገደማ እንቁላሎችን ይጥላሉ።ዶሮ በምዕራባውያን አገሮች በብዛት የሚገኝ ሲሆን ዋጋውም ርካሽ ነው። ከአሥርተ ዓመታት በፊት በአሜሪካ አጨ ተወዳዳሪዎች ለምርጫ በሚቀርክበት ጊዜ በምርጫው ካሸነፉ ዶሮ በገፍ ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ ለመራጮቻቸው ቃል ይገቡ ነበር።

ይሁን እንጂ ዛሬ ዶሮ እንደ ቅንጦት ምግብ መታየቱ ወይም የጥቂቶች ምግብ ብቻ መሆኑ ቀርቷል። በዓይነቱ ልዩ የሆነው ይህ የወፍ ዘር እንዲህ በብዛት እንዲገኝ እንዲሁም በጣም ተወዳጅ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው? ድሃ አገሮችን በተመለከተስ ምን ማለት ይቻላል? አነርሱስ የተትረፈረፈው ምርት ተቋዳሽ መሆን የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖር ይሆን? የዶሮ ታሪክዶሮ የአስያ ቀይ የዱር ጅግራ ዝርያ ነው። ሰው ዶሮን በቀላሉ ማልመድ እንደሚችል ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም። እንዲያውም ከ2, 000 ዓመታት ገደማ በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ ዶሮ ጨጩቶቿን እንደት ከክንፎቹ በታች እንደምትሰበስባቸው ተናግሯል። (ማቴዎስ 23:37፤ 26:34) ይህን ምሳሌ መጠቀሙ ሰዎች ባጠቃላይ ስለ ዶሮ በደንብ ያውቁ እንደነበር ያሳያል። ሆኖም ዶሮና እንቁላል ለገበያ ለማቅረብ ሲባል በሰፊው የዶሮ አርባታ የተጀመረው ከ19ኛው መቶ ዘመን በኋላ ነው።የዶሮ ሥጋ ዛሬ በብዙዎች ዘንድ በጣም ተወዳጅ ምግብ ነው።

የከተማ ነዋሪዎችን ጨምሮ በሚልዮን የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ለራሳቸውም ሆነ ለገበያ ለማቅረብ ዶሮ ያረባሉ። አንዳያውም የዶሮን ያህል በተለያዩ የአየር ጠባዮች መርባት የሚችል የግብርና እንስሳ የለም ማለት ይቻላል። ብዙ አገሮች ለራሳቸው አገር የአየር ጠባይ የሚስማሙና ጥሩ ምርት የሚሰጡ የዶሮ ዝርያዎችን አራብተዋል። ከእነዚህ መካከልየአሙሰትራሊያው አውስትራሎፕ፣ መጀመሪያ በሚድትራኒያን የተገኘውና አሁን በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በብዛት ያለው ሌግሆርን፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚረቡት ኒው ሃምፕሻየር፣ ፕሊይማውዝ ሮክ፣ ሮሚ አይላንድ ሬድ እንዲሁም ውያንዶቴ፤ የአንግሊዞቹ ኮርኒሽ፣ ኦርፒንግቶን እና ሱሴክስ የሚባሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

በአርባታ ረገድ የተገኘው የተሻሻለ ሳይንሳዊ ዘዴ ዶሮ አርባታ ስኬታማ የግብርና ኢንዱስትሪ እንዲሆን አስችሎታል። የዩናይትድ ስቴትስ ገበሬዎች የዶሮ በሽታን በሳይንሳዊ መንገድ ከመቆጣጠራቸው በተጨማሪ አመጋገባቸውንና አሰፋፈራቸውን በተመለከተ ጥንቃቄ በተሞላበት ዘዴ ክትትል ያደርጋሉ። አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ያለውን በገፍ የማርባት ዘዴ እንደ ጭካኔ ይቆጥሩታል። ይሁን እንጂ ይህ አመለካከት ገበሬዎቹ በየጊዜው ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ የዶሮ ማራቢያ ዘዴዎችን ከመፈለግ አላገዳቸውም። ዘመናዊው ዘዴ እንድ ሰው ብቻውን ከ25, 000 እስከ 50, 000 የሚያክሉ ዶሮዎችን እንዲያረባ ያስችላል።

አንድን ዶሮ ለገበያ ለማድረስ የሚወስደው ጊዜ ሦስት ወር ብቻ ነው።*የሥጋ ዶሮየትኛውም ሆቴል፣ ሬስቶራንት ወይም ምግብ ቤት ብትገቡ ዶሮ የማይጠቀሰበት የምግብ ዝርዝር አታገኙም ለማለት ይቻላል። እንዲያውም ቶሎ የሚደርሱ ምግቦችን የሚያዘጋጁ ሬስቶራንቶች የዶሮን ሥጋ በማዘጋጀት ረገድ የተዋጣላቸው ሆነዋል። ልዩ ዝግጅት ሲኖራቸው ዶሮ መሥራት የሚመርጡ ማኅበረሰቦች አሁንም አሉ። እንዲሁም እንደ ሕንድ ያሉ እንዳንድ አገሮች አስደናቂ የሆነ የተለያየ ዓይነት የዶሮ አሠራር ዘዴ አላቸው። ለምሳሌ ያህል በበርበሬ የተሠራ ዶሮ ወይም ላል መርጊ፤ ዶሮ ዝልዝል ወይም ከርጊ መርጊ፤በዝንጅብል የታሸ ዶሮ ወይም አድራክ መርጊ የመሳሰሉ የዶሮ አሠራሮች አጅ የሚያስቀረጥሙ ናቸው!ከዶሮ የተዘጋጀ ምግብ ይህን ያህል ተወዳጅ የሆነውለምንድን ነው?


አንዱ ምክንያት የዶሮን - ያህል በተለያዩ ቅመማ ቅመሞች ጣፍጠ ሊሠራ የሚችል ምግብ የለም። አንተ የምትወደው በምን መልክ ተሠርቶ ሲቀርብ ነው? ጥብስ፣ አሮስቶ ወይስ ውጥ? ማንኛውንም የምግብ አዘገጃጀት ብትመለከት አያንዳንዱን ምግብ አንዲዮም ለማድረግ የተዘጋጀ በደርዘን የሚቆጠር የዶሮ አሠራር ዓይነት ትችላለህ።ዶሮ በብዙ አገሮች በብዛት ስለሚገኝ በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ርካሽ ነው ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ዶሮ ለሰውነት አጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ፕሮቲን፣ ቫይታሚንና ማዕድኖችን ስለያዘ በምግብ ጥናት ጠበብት ዘንድ ተመራጭ ነው። ሆኖም በዶሮ ሥጋ ውስጥ ያለው የካሎሪ፣ የጠገር ቅባት (saturated fats) እና የሌሎች ቅባቶች መጠን አነስተኛ ነው።በማደግ ላይ ያሉ አገሮችን መመገብአርግጥ ነው፣ ሁሉም አገሮች የተትረፈረፈ የዶሮ ምርት አላቸው ማለት እይደለም። የግብርና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት ያሰሣራው አንድ ግብረ ኃይል "በ2020 የዓለም ሕዝብ ብዛት 7.7 ቢልዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል።

. . . ይሁን እንጂ አብዛኛው (95%) የሕዝብ ብዛት ጭማሪ የሚጠበቀው በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ነው" በማለት ያቀረበው ሪፖርት የሁኔታውን አሳሳቢነት የሚያሳይ ነው። አሁንም እንኳ 800 ሚልዮን የሚያክል ሕዝብ በተመጣጠነ ምግብ እጦት እንደሚሰቃይ ስትገነዘብ የችግሩ አሳሳቢነት ይበልጥ ጎልቶ ይታይሃል!የሆነ ሆኖ ብዙ ጠበብት ለረሃብ የተጋለጠውን ይህን ሕዝብ ለመመገብና ገበሬዎች የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ዶሮ አርባታ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ይስማቸዋል። ችግሩ ለድሃ ገበሬዎች ዶሮን በስፊው የማርባቱ ጉዳይ ተፈታታኝ ሊሆንባቸው ይችላል። እንደኛ ነገር በድሃ አገሮች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ዶሮ የሚረባው በጠባብ የገጠር አርሻ ቦታዎች ወይም በጓሮ ውስጥ ነው። ይህ ሁኔታ በሚታይባቸው አገሮች ውስጥ ዶሮዎች ጥሩ መጠለያ የላቸውም።

ቀን ቀን የትም ምግባቸውን ሲለቃቅሙ ይውሱና ማታ ወደ ቤት ተመልሰው ዛፍ ላይ ወይም በሽቦ በተሠራ ቤት ውስጥ ይሰፍራሉ።በዚህ መንገድ ከሚረቡት አብዛኛቹ ዶሮዎች ውስጥ እንዳንዶቹ በፈንግል በሽታ ማለቃቸውና ሌሎች ደግሞ የአዳኝ አውሬና የሰው ሲሳይ መሆናቸው እያስደንቅም። ብዙዎቹ ገበሬዎች ዶሮዎቻቸውን በበቂ ሁኔታ የመመገብ፣ ተገቢ የሆነ መጠለያ የማዘጋጀት ወይም በበሽታ እንዳይጠቁ የመከላከል አቅሙም ሆነ ችሎታው የላቸውም። በዚህ ምክንያት በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ያሉ ገበሬዎችን ለመርዳት ሲባል የማስተማር ፕሮግራም ተጀምሯል።

ለምሳሌ ያህል የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የአርሻ ድርጅት "በአፍሪካ ገጠር ውስጥ የሚኖሩ ድሃ ገበሬዎች በዶሮ አርባታ የሚያገኙትን ጥቅም ለማሳደግ" ያወጣውን የአምስት ዓመት ዕቅድ በትርቡ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።በቅን ልቦና በመነሳሳት የተወሰዱት እነዚህ አርምጃዎች የሚያስገኙት ውጤት ወደፊት የሚታይ ይሆናል። ዶሮን የየዕለት ምግባቸው ያደረጉ በበለጸጉት አገሮች የሚኖሩ ሰዎች አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ትንጣቢ የዶሮ ሥጋ ያረረበት መሆኑ ሊያሳስባቸው ይገባል። ለአብዛኛው የዓለም ሕዝብ 'ዶሮ በሽበሽ' ይሆናል የሚለው ሐሳብ ከሕልም አንጀራ የሚቀጠር ነው።

ልብወለድ



(በቅዱስ ሰውነት)

ቅጽሜ ።

ወንደላጤ ነኝ።

በግራ እጇ ጫቴን፣ በቀኜ የዕለቱን ጋዜጣ አንጠልጥዬአለሁ። ወደ ቤቱ እየተንደረደርኩ ነበር።

"ሄይ!" - ታክሲው ካለፍኩት የቀመ ዘመናዊ መኪና ውስጥ በመስኮቱ እንገቱን አስግጎ ጠራኝ።

ዞርኩኝ። ባለ መነጽር ጎልማሳ።

ዝም ብዬው ልሄድ ነበር። በግራ እጇ ጣቶች በምልክት ጠራኝ።

እየሱሳዊ አጠራር።

ሚነው አሱ?

ሄድኩኝ። "አቤት ጌታዬ" አልኩት።

"መንገድ የጠፋው ቀብራራ"

አላለሁ በሆዴ።

ተንጠራርቶ የጎኑን በር ከፍቶ እንድገባ ጋበዘኝ።

ሚነው ይሄ ዘንካታ?

ግባሁ። መነጽሩን

አውልቆ የካኒቴራው አንገት ላይ በቁንጥ አንጠለጠለው።

"ማነው ይሄ ጉረኛ?" ራሴን አጠይቃለሁ። የበርጫ ሰዓቴን በውስጤ አስላለሁ። ሙሉ በሙሉ ወደ አሱ ዞሬ እየሁት።

የት ነበር የማውቀው? የት ነበር? የት ነበር? ወደ ትዝታዬ ጎጆ በረርኩ።

ግራ እጁን እንስቶ መረው ላይ በስታይል አኖረው። 'ማነው ይሄ ቁንጠኛ ትርፍ ጣት!?'

ፈገግ አለ። የሆዴን የሰማኝ መሰለኝ።አፍሬ እንገቴን ደፋሁ። ድንገት ግን ዞሬ አየሁት። ሚጢጢ ሰያፍ ሽራፊ።

ጮህኩኝ። "ውብ ሰራ!"

እንገት ለእንገት ተጠማጠምን። እናቴን ደባበሰኝ።

"ይሄ ሁሉ ሽበት ምንድን ነው?"

፪

"ቦስ!"

በአሱ በኩል ባለው መስኮት፣ እንድ ዘናጭ ወጣት ቀሞ ናዶል።

"እዚህ ያለው ጉዳይ ትንሽ ጊዜ ሳይወስድ አይቀርም። በእንድ ሰዓት ውስጥ መልሼ አደሙላለሁ። ምሳ ማድረግ ይችላሉ እስከዚያው"

"ኦ! መልካም! እኔም ደውዬ አሱኑ ልልህ ነበር። ደውል።"

የድምጹ ግርማ ሞገስ! ወይ ጊዜ! ይሄ አሁን አውን 'ውብሰራ ትርፍ ጣት' ነው? ማን ያምናል?

"እሺ ሰር"

ወጣቱ ሄደ።

"ታዲያ ምሳ የት ነው እየበላን የምናወጋው?" ወደኔ ዞረ።

መኪናውን አስነሳ።

"ሽሮ ዋጀ ነው የወጣሁት። እሷን መቋደስ እንችላለን" አልኩት።

"ሃሃሃ! ግደለም ለእራት ተጋቢኖ ሆና ትቀይህ፤ ዛሬ እኔ ነኝ ጋባዧ" ጋዜ አላዘነችኝ።

፫

ጥሬ ሰጋና ጥብስ ጋበዘኝ። ወጣቱ ጋ ራሱ ደውሎ ተጠሮውን አራዘመ። እንዲት ቡና ቤት ደጃፍ፣ ዛፍ ያረበባት ጥላ ስር፣ እኔ ቢራ፣ አሱ ስሙ የማይታዘዝ አልኮል አዘዝ ተቀመጥን።

ንግግሩ ቀጥተኛ ዓይነት ነው። "ምን ትሰራለህ?" እለኝ ወሬ እንደ ጀመርን።

"አስተምራለሁ"

"ምን?"

"ታሪክ"

"የት?"

"አንድ ሃይ ሰኩል ውስጥ"

ሰለ ደሞዝ፣ ሰለ ኑሮ፣ ሰለ ትዳር፣ ሰለ ሃይማኖት አከታትሎ ጠየቀኝ። በሁሉም መምክኔን ነገርኩት። ሰለ አሱ እንዲያወራኝ ጓጓሁ።

"ያንተን ታሪክ አልረሳውም" አልኩት።

አቋረጠኝ።

"ያ አስክንድርስ? ለመሆኑ አለ?" ጠየቀኝ።

"አሱማ ሞቶ"

"ትውኒ እንጂ! ያ ተንኮስኛ ጓደኛው አንዳሻውስ?"

"አሱ ባክህ ያለበት አይታወቅም.....ወይ አንተ! ትምህርት ሲታቋርጥ ትዝ ይልሃል?" መልሱን ዘለለው።

"ስለ መስታወትስ ሰምተህ ታውቃለህ?"

"አሷ አንኪን ጎብኳለች አሱ። እንደውም ምን የሚባል ከተማ፣ ማሩም ሆቴል ከፍታ ትሰራለች አሉ። ትዝ ይልሃል? አንተ እና እሷ..... "

አላስጨረሰኝም።

"ያ'ሳ 'ኡስታዝ' የምንለው፣ ካንተ ጋር ሁሉ ትምህርት ቤት ጓር እየዞራችሁ ይሰግድ የነበረው፣ ጀኒየስ ልጅ? ማን ነበር ስሙ?"

" ሃይክል፤ ኑሮውን ሳውዲ አረቢያ ካደረገ ስንት ጊዜው"

፬

ሞቅ እያለን ሄደ። በሞቅታችንም ውስጥ አንዳች የሚሸሸው ጨዋታ አንዳለው ታዘብኩ። አልለቀውም!

"ከድሮ ጓደኞቻችን ማንን ታገኛለህ?" ጠየቅኩት።

"ማንን አገኛለሁ ብለህ ነው?"

"እስታውሳለሁ፣ እየጎረመሰን ስንመጣ፣ሰሳንት ሲነሳ፣ሁላችንም አናዘን ነበር።" አልኩት

"ምን ታዝናላችሁ።" አለ "

የአብደት ዘመን:: የተማረውስ ይሁን የመምህራኖቹ መባስ:: እንደዚያ ሲያሰቃዩን፣አናንተም ያንን ችላችሁ በትምህርት መማፋታችሁ ይደንቃል።"

እውነት ነው። ልጅነት ጋርዶን አንጂ ቦታው ግማሽ ሲያል ነበር። ግማሽ ገነት።

"ከትምህርት ከወጣህ ወዲያ ምን ጀመርክ?" አልኩት።

አንዴት ትምህርት እንደተወ አውታለሁ።

ትዝ ይለኛል። ትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥ አሱ፣መስታወትና ስማቸውን አሁን የረሳኋቸው ጥቂት የሌላ ክፍል ልጆች፣ በተማሪዎች መግቢያና መውጫ ሰዓት ከረሜላ፣ ማስቲካና የተጠበሰ አንደ ብይ ድቡልቡል ሰሊጥ ይሸጡ ነበር። አስተማሪዎቻችን ይህን ሰራቸውን ይክለክሏቸው ነበር። አነሱ ግን አየተደበቁ ሰራቸውን ይቀጥሉ ጀመር። የሆነ ቀን በየክፍሉ ፍተሻ ተደረገ። ውብሰራ

ከነሰሊጡ ተያዘ። እኛ ማቲዎቹ አየተሻማን ሰሊጠኝን በላናቸው:: ውብሰራ በትምህርት ቤቱ ዩኒት ሊደር ጭንቅላቱን እንደ አባብ በሸንበቆ አየተተጠቀጠ ከክፍል ተባረረ። ቅጣቱ እንኳ ጊዜያዊ ነበር። አሱ ግን ትምህርቱን አስከ ወዲያኛው አቋርጠት ተረ። የልጅነት ሰቅሰውን በሳቃችን እጅበን ሸኘነው::

ከዚያስ? አራሱ ውብሰራ ይንገረን።

"ያው ሰምታችሁታል። ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት ከተዘረጋው አስፓልት ማደ፣ የቀበሌው ጽህፈት ቤት አጠገብ ካለው የሸንኮራ አገዳ ማከፋፈያ ቤት ከመኪና አውራጅ ሆኜ ተቀጠርኩ። በሳምንት ትንሽ ብር እያገኘሁ፤ ግማሹን

ወደ ገጽ 29 ዞሯል

ውብሥራ
ካገጽ የዞረ

እየቆጠብኩ፣ ግማሿን ለእናቴ እየሰጠሁ፣ ኑሮዬን ቀጠልኩ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ በብድርና በዱቤ መለስተኛ ቦታ ተከራይቼ የራሴን ሽንኮራ አውርጂ መሰራት ጀመርኩ።"

ይሄንን አሰማ ነበር። እኛ ያን ጊዜ ሃይ ሰኩል ገብተናል። "እናንተ ያን ጊዜ ሃይ ሰኩል ገብታችኋል።" አለ ውብሰራ ደግሞ "የአግራችሁን ዳና ማጸመጫን አላቆምኩም። እንድ ቀን ተሰፈንጥሬ ከፊታችሁ እንደምቶም አውቅ ነበር። መንገዴን ቀጠልኩ። ጊዜው ወደፊት ሄደ። ቆይቶ፣ የገጠር እህል አምራቾችን ከከተማ ነጋዴ ጋ የማገናኘት የኮሚሽን ስራ መስራት ጀመርኩ። ብዙ ገንዘብ አገኝ ጀመር። እያደር የራሴን የንግድ ስራ የምጀምርበት እድል አገኘሁ። ሀይወቴ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ።"

"የትምህርትህስ ነገር?"
"ተውኩታ! አውነት ልንገርህ? አሰከ ጉልምስናዬ መባቻ ድረስ፣ እያንዳንዳችሁ የክፍሌ ልጆች ሞታችሁ፣ ያ በልባችሁ ያለው አሳዛኝ ታሪኬ አብሯችሁ መቃብር አንዲወርድ ምኞቴ ነበር። በኋላ፣ ከብዙ ጊዜ በኋላ፣ ወስራ በየሄድኩበት ከተማ አችደ ሃዋርያት ተበትናችሁ የምትገፉትን የተበደለ ኑሮ ሳይ፣ ሁላችሁንም ይቅር አልኳችሁ።"
'ይሀን ሰው በድለነዋል' አልኩ፤ ለራሴ። ልቤ ሃዘንና ጸጸት አነሰ። ከሃሳቤ መለሰኝ።

ድንገት ተነሳ።
"ኋለኞች ፊተኞች ፣ ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ" አለ አየሳቱ። ከብዙ ብሮች መሃል ቶጥር፣ ሂሳባችንን ከፈለ።
ግማሽ መንገድ በመኪናው ሽኘኝ። ጫቱንና ጋዜጣዬን ይዤ ተሰናብቼው ወረድኩ።
"በዚህ አግኝኝ" ብሎ ትንሽዬ የአድራሻ ካርድ በመሰከቱ በኩል አቀበለኝ።
መኪናው አቧራ ረጭቶኝ ተሰወረ።
ወደ ካርዷ አቀረቀርኩ።
ቆሜ ቀረሁ።







ከበደ ኃይሌ
(kbdeh2013@gmail.com)

መፍትሔ ያላገኙ ጉዳዮቻችን የጊዜ እጥረት፤ መዘግየት፤ ክፍፍል

በአሜሪካ የሚገኘር ኢትዮጵያውያን ሕብረተሰብ መፍትሄ ያላገኘንላቸውና አሁንም በክፍተኛ ደረጃ ከምናስተናግዳቸው ጉዳዮቻችን መካከል ቀጠሮ ያለማክበር፤ ያልተጋባዙ እንግዶችንና ልጆችን አስከትሎ በግብዣ ላይ በመገኘት በደጋሾች ላይ ስለሚያስከትለው ተጨማሪ መስተንግዶና ተጨማሪ ወጪ፤ የጊዜ እጥረትየአርስ በአርስ ክፍፍል የተስኙትንና ከእነኝሁ ጋር ተዛምዶ ካሳቸው ጥቂት ጉዳዮች ጋር ዋቢ አደጣቀሰን ለመመልከት እንምክራለን።ርዕሰ-አንቀጽ ተዘጋጅቶ ለአንባቢያን እንዲቀርብ የተደረገበት ዋናው ምክንያት የመዘግየትና ያለመዘግየት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በተጋባዥ እንግዶች መዘግየትና ጉዳዮች ሳይከናውኑ ሲቀርም ጊዜ በማጣት ነው እየተባለ ስለምናሳብበው ዋንኛው ምክንያታችንን ከባህላችን ጋር አያዛመድን ነገረ-ጉዳዮቻችንን ዘርዝረን በማስቀመጥ መረጃዎችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማስተላለፍ ነው።ይህ ርዕሰ -አንቀፅ የተለያዩ መጠነ ሰፊ ጉዳዮቻችንን ያቀፈ ቢሆንም፤ ሸፍኖ አንድ የተመለከተው በግብዣ፤በተጋባዦች መዘግየትና በምግብ አዘጋጅ ደርጅቶች ላይ ስለሚያስከተለው የሥራ አፈጻጸም ችግሮች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፤ ሌሎች ርዕሶችንም አንዲሁ በቅደም ተከተል አንዲቀርቡ ይደራጋል።

ቀጠሮ ያለማክበር፤ ያልተጋበዙ እንግዶችና ልጆችን አስከትሎ ስለመምጣት ጉዳይ በተሳታፊው ህብረተሰብ ላይ ጎጂነታቸው አሁን አሁን እየተጋለጠ በመታየት ላይ ሲሆን፤በእኪያውም የልጆች ብዛትና ያልተጋበዙ ሰዎች መምጣት ዘግይቶ ለሚመጣው እንግዳ ውንበር፤ምግብ፤ መጠጥ ማጣትና የቦታ መጣበብ ምክንያት ሆኖ ስለታየ ዘግይቶው ለሚመጡ እንግዶች መቀጣጫ ሆኖ ታይቷል። በተለይ በዕድሚ ክፍ ያሉ ልጆችን አስከትሎ ለማምጣት ከሚሰጡት ምክንቶች አንዱ የአገራችንን ባህል ለማሳየት ነው የሚል ምክንያት እየተሰጠ የሚታለፈው ስህተት በጋብዣ ባለቤቶችና በምግብ አዘጋጆችም ላይ ተጨማሪ የስራ ጫናና የወጪ ሓላፊነትን እንደሚያስከትል በዕቅድ በሚናርበት አገር ማሰብ የተሳነን ወይም የማይለሸነት አካሄድ ይመስላል።

በዚህ 2017 ዓመት አጋማሽ ላይ ብዛት ያላቸው የሰርግ በተለይም የተማረዎች ምርቃት የግብዣ ድግሶች የተካሄደባቸው ወቅት ስለነበር በአትላንታና በዙሪያዋ ከተሞች የሚኖሩ የኢትዮጵያውን ኅብረተሰብም ከወራዊ ውጭ ለሆነ ወጪ የዳረገ፤ ጊዜያቸውን ያማበከና በአንጻሩም የመገናኛ መድረክ ፈጥረው አንዳገለገሉ ተሳተፍን የነበርን ሰዎች ሳናስተውል አልቀረንም።ይሁንና የተጋበዙት አንግዶች ይመጣሉ ተብሎ ከተወሰነው ሰዓት ቢያንስ ከ2 አስከ 3 ሰዓታት ባለነሰ ሰዓታት ዘግይተው ስለሚመጡ በዘግዮች ምክንያት መስተንግደው ለምን በሰዓቱ እንደማይጀመርና ሰዓቱን አክብረው የመጡት አንግዶች ካለጥፋታቸው ሳይስተናገዱ የሚመለሱበት ምክንያት መኖር የለበትም።ደጋሽ ባለቢቶቹ ስለዘገዩ የመስተንግዶው መንተት በጥቂቱ ተቀባይነት ቢኖረውም፤ የደጋሾች መዘግይትን ግን በአብዛኛው ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ሆኖ ቀድሞ መገኘት የሚኖርባቸው ጋባዦች መሆን ነበረባቸው።ነገር ግን በተጋባዥ አንግዶች ምክንያት መዘግየት ሳቢያ በሰዓቱ የመጡት አንግዶች የማይስተናገዱበት፤ ምግቡ ለመቀዝቀዝ ምክንያት የሆነበት ተቀባይነት አይኖረውም። አንዲያውም ድግሱን በሰዓቱ በመጀመር ለዘግይ አንግዶች ማሳየቱ ትምህርት ቀስመው መቀጣጫም በሆናቸው አንዲሁም ምግቡ ሳይቀዝቅዝ ለመብላት በተቻለ ነበር።በሰዓቱ ያለመጀመሩ ግን ድግሱ የሚጠናቀቅበትን ሰዓት ከማራዝሙም በላይ ሰዓቱን አክብሮ የመጣው አንግዳ ተስተናግጂ መሄድ አለብኝ የሚል ጥያቄ ለማቅረብ የተገደዳበት ጊዜ የታየበትን ውቅት ለማይት አድርዕል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ኅብረተሰቡ በሚገባ ቢረዳውም ሰዓቱን አክብሮ በግብዣው ላይ የሚገኘው ሰው እጅግ ጥቂት የሆነበት አይነተኛ ምክንያቱ "ሰው አይመጣም በሰዓቱ ሄጂ ለምን ጊዜዬን አጠፋለሁ" አየተባለ በፋከክር ስለሚዘገዩ፤ ብሎም የሚፈለጉ አንግዶች እስከሚመጡ ድረስ መስተንግዶዎ መጓተቱ ነው። በመሠረቱ በሰዓቱ ስለመገኘትና ዘግቶ ስለመምጣት ጉዳይ ወደ አገር ቤቱ ባህል መለስ ብለን በዓይነ-ሂለና ሰንቃኘው፤ ተጋባዥ አንግዳ በግብዣ ላይ ቀደም ብሎ ሄዶ ከተገኘ ሰው ይታዘበኛል፤ አንደችግረኛ/አንደተራበ ሰው ያስቆጥራል የሚል አመለካከት አንደ ባህል ተቆጥሮ ይታይ ስለነበር አራስን ዝቅ ካለማድረግ አኳያ አየታየ ይህን ጎጂ ባህል የጊዜ ቁጠባ በሚፈለግበት አገር ሲኝእባረት መታየቱ ዘግይቶ የመድረሱን ምክንያት አየተቀበልነው የጊዜ ጠቃሚነቱ አየተዘነጋነው የመሄድ አዝማሚያ እንዳለ ያመላክታል። ዘግይቶ መድረስ ግን ከቁጥጥር በላይ ካልሆነ በቀር በፕሳን ኑሮን አንደማንመራው ስለሚያሳይ በየትኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት አይኖረውም፤፤ በአገራችን ባህልም ቢሆንም በግብዣ ላይ አንግዳው ምግብ አንስቶ ሲበላ መድረስ ዘግይቶ የሚደርስውን ሰው ያሸማቅቃል።

አንዳንዴም ህብረተሰባችን ዘግቶ የመምጣቱን ነገር መቀበላችንን የሚጠቁመው የተጋበዘ የውጭ አገር ዜጋ ሰዎች ካሉ በሰዓቶ መጥተው በክንቱ ሰዓታቸው አንዳይባክን አየታሰባላቸው ዘግይተው አንዲጣጡ በቅድሚያ ይነገራቸዋል። ዘግይተው ሲመጡም ምግብ አንዳያጡና የሚፈልጉትን መጠጥ ሳያገኙ አንዳይሄዱ ለአንሱ ለብቻ ምግብና መጠጥ አንዲቀመጥላቸው ትአዛዝ ሲተላልፍ ሲሰማ፤ አንዳንዴም ስተጋባዡ ኢትዮጵያውያን ያልቀረበለት የምግብና የመጠጥ ዓይነት ቀርቦላቸው ሰስተናገዱ ሰስተዋል ክራስ ወገናችን ይልቅ ለውጭ አገር ዜጋ ክብር ስንስጥና ስንቆረቆር ያሳዝናል።ይህ የራሳችንን ሰው አየናቅን ለውጭው አገር ዜጋ ተጋባዥ የምንሰጠው ልዩ ክብር፤አንክብካቤና መስተንግዶ አጓጉል ባህላችን ለማያውቅ ሰው አንደጥሩ ነገር ተቆጥሮ ድክመታችንን በማስተማር ላይ አንደምንገኝ ስንቶቻችን ተገንዘበነውና የታዘብን ሰዎች አንኖር ይሆን? አንዚህ አንዲህ አየተባለ ግብዣው ለጠናቀቅ ግማሽ ሰዓት ሲቀረው የመጡ አንግዶች ተጋብዘው ቀሩ አንዳይባሉ አንጂ አንደመጡ አይቆጠርም።ነገር ግን ሲመጡ የመቀመጫ ውንበር ባልተጋበዙ አንግዶችና በልጆች ብዛት በመያዙ ቆመው የመስተናገድ አድል ሲገጥማቸው፤በአነሱ ብሶ በሚገባ ሳንስተናገድ ተመለሰን ብለው እሮሮ ሰያሰሙ ያስደንቃል።

የተጋባዥ በሰዓቱ ያለመገኘት የሚነካካው አነሱን ብቻ ሳይሆን ደጋሾችንና የምግብ ዝግጅቱን ሐላፊነት ለተቀበሉ ደጋሽ የግል ድርጅቶችና በአዳራሽም ላይ ያልታሰበ ተጽእና አንደሚያስከትልባቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። የድግስ አዘጋጅ ድርጅቶች አንደሚሉት ከደጋሾች ጋር በመጀመሪያ ሲዋዋሉ ምግቡና መጠጡ ለተገባዥ ዕንግዶች አንጂ ባልታሰቡ ሰዎች ምግቡ ቢበሳና አጠረት ቢፈጠር፤ ግብዣው በሰዓቱ ባለመጀመሩ ምግቡ በመቀዝቀዙና ምግቡ አንደገና ሞቆ አንዲቀርብ፤አጠረቱን ለማካካስ በተጨማሪ ለቀረበው ምግብ ዋጋ በመጠየቅ ድርጅቶቹ ለመወቀስና ለመጠየቅ ተጠያቂ መሆን የለብንም ይላሉ።አንደደጋሽ ድርጅቶች አባባል ለተጋባዥ አንግዶች ቁጥር መብዛት ዋና መንሲዔው በደጋሾች ቤት ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ በየፊናው ማለትም ወላጅ፤ልጆችና በቅርብ ዘመድ-አዝማድ በየግሳቸው ሰዎች ከጠሩ ለቁጥር አመቺ ካለመሆኑም በላይ ድርጅቶችና ደጋሾችን ላልታሰበ ወጪ ይዳርጋል። አንደሚታወቀው ምግብና መጠጡ የሚዘጋጀው በአንግዶች ቁጥር ስለሆነ ያልተጋበዙ አንግዶች ይዘው ባመጧቸው ልጆችና በተለሳፊ ሰዎች ስለተበላ ብሎም ወንበርና ጠረጴዛዎችም ሲያዙ ዘግይተው የመጡት አንግዶች በወንበር እጥረት ሳቢያ መቀመጫ አጥተው ተቸልኩለውና ግድግዳ ተደግፈው ቆመው ድግሱን የተካፈሉ፤ምግብ አንኳ ሳያገኙ የተመለሱ አንግዶች ነበሩ።ባለማወቅም ሆነ በግድየለሽነት በምንሰራው ስህተት አያድርገውና

ወደ ገጽ 35 ዞሯል



[አሸቴ አሰፋ በሸገር አንዳቀረበው]

ወደ ዮርዳኖስ ጉዞ (1)

ወደ ጥንታዊ ፈላሽ መንዝ፣ ብሉይና ሐዲስን በጥምቀት መዳመሰለለው መንዝ፣ወደ ዮርዳኖስ መንዝ፣ ወደ ሙት ባህር።

ዕለቱ አርብ ነው፤ ጊዜውም ነግህ ሆኗል፤ አጅግ የንጓሁለት ጉዞ ነውና ገስግሽ ተነሳሁ። ለአኔም ሲሉ ቀንዓና ብሩክ ገስግሰው ቀነሱ። የምንሄደው ወደ ዮርዳኖስ መንዝ ነውና ከመጠመቃችን በፊት ቁርስ ለመብላት አልፈለግንም። ይህ ደግሞ ከአማን በቶሎ አንድንወጣ ረዳን። ወደ አማን የሄድነው በዘመናዊ ቀይ መኪና ነው። አማን እየሰነጠቅን ባለፍን ቁጥር ባለፉት ቀናቶች ያላየኋቸውን ታላላቅ ሕንፃዎችና ሐውልቶቿን እየሁላት። መቼም የምታደንቅ ከተማ ናት፤ በርካታ መኪናች እኛ በምንሄድበት አቅጣጫ ይከንፋሉ፤ ፍጥነታቸው አያድርስ ነው።

በሀገረ ዮርዳኖስ የሰምንቱ የአረፍት ቀን አርብ ነው። ስለዚህ ቤተሰብ ተሰባስቦ ወደ ሙት ባህር መሄድ ልማዳቸው ኖሯል። በፍል ውሃ እየተጠመቁ፣ በሙት ባህር እየዋኙ፤ ማሳለፍ የማይሰለቹት ልማዳቸው መሆኑን ሰማሁ። ዮርዳኖስ ስለሌሎች የዐረብ አገሮች ከምንሰማውና ከምናየው በብዙ ትለያለች። ለምሳሌ፦ እነዚያን የሚርመሰመሱ መኪናች በአብዛኛው ፆሚነዱት ሴቶች ናቸው፤ሴቶች በዮርዳኖስ እንዲፈኑና አንዲገደቡ አይደረጉም። ደረታቸውንና ባታቸውን እያሳዩ ፀጉራቸውን እንደ ፊልም ተዋናይ እየበተኑ፣ ሲሻቸው ሲጋራ እያጨሱ በከተማዋ ሽር ብትን ቢሉባት ከልካይ የላቸውም።

የምንሄድበት ከመሬት ወለል በታች ከዓለም የመጨረሻው ዝቅተኛ ቦታ ነውና የብሩክ መኪና ከፊቷ የተተክለች መሰለች። የመሬት ወለል ዜሮ ከሆነበት ቦታ ላይ ደረስን፤ ከመሬት ወለል በታች 350 ሜትር እንንደረደራለን። የመሬቱ ወለል ዜሮ በሆነበት ቦታ ፎቶ ልንነሳ ስንሞክር ሃይለኛ ንፋስ ገጠመን። ጃኬታችንን ክላያችን ላይ አውልቆ የሚሄድ የሚመስል ዲደን ንፋስ አንገላታን። ከመሬት ወለል በታች እያዘቀዘቅን በመሬድን ቁጥር የምናየው ሚዳና ለም መሬት ብቻ ነው። የሀገራችን ዳሎል ከመሬት ወለል በታች 119 ሜትር ዝቅ በማለቱ መፈጠሩን የሚያስመርር ሙቀት እንዳለው እናውቃለን። የዮርዳኖስ ወንዝ ግን ከመሬት ወለል በታች ወደ 400 ሜትር ዝቅ ብሎም አየሩ ቀዝቃዛ ነው።


ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እየተጠጋን ነው። ወደ ወንዙ ከመድረሳችን በፊት ኪሳ ላይ ቶምን፤ መኪና ትተን በእግራችን መንዝ ጀመርን፤ አካባቢው ነጭ ንጣፍ ድንጋይ የተነጠፈበት ይመስላል። ድንጋዩ ነጭ፣ አፈሩም ነጭ ነው። በስተቀኛችን ከጉብታዎቹ ስር ዋሻዎች አሉ። ያኝን ዋሻ ኤልያስና ተክታዮቹ ነብሩበት ብሎ ኢያን ነግሮናል። ይሁንና ማንም ተቀመጠባቸው ማን ጥንታዊነታቸው አርግጥ ነው።


በኪላው ዙሪያ የመጠመቂያ ቀሚስና ቅብዓ ቅዱስ፣ መስቀልና ቅርፃ ቅርፆች የሚሸጥበት ሱቅ ለእኛ የሚሆነንን እነ ቀንዓ ከመሃመድ ሱቅ ገዙ። በዮርዳኖስ እንዲህ ነው፤ በሙስሊም እምነት ተክታዩ ሱቅ ውስጥ የክርስቲያኖችን መገልገያ ማግኘት ይቻላል። ስለ ዕቃውም ሲያረዳ ከመፀሀፍ ቅዱሱ አባባል አንዲትም አያድልም፤ ወደ ወንዙ ከመድረሳችን በፊት አዚያው በቅርቡ በቅዱስ ዮሀንስ የተሰየሙ የግሪክና የሩሲያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያኖች ተሰርተዋል። የሩሲያው ትልቅና ባለ ወርቅ ቅብ ጉልላት ነው፤ አዲስ የሚሰራ ትልቅ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንም ተጀምሯል።


የምንሄድባትን ቀጭን የአግር መንገድ ተክትለን ወደፊት ስንሄድ ከወታደር የዮበቃ አጥር ጋ ደረስን። ዮርዳኖስ ከእስራኤል ጋር የምትዋሰንበት የዮርዳኖስ ወሰን ስለሆነ ወሰን ጠባቂ ወታደሮች አካባቢውን ይጠብቃሉ። ከወታደሮቹ አነስተኛ መጠለያ በሰተቀር በውንዙ ዳርቻ ምንም ነገር የለም። ሌላው ቀርቶ የልብስ መልወጫ አነስተኛ ክፍል እንኳን አልተሰራም።

ይኸውና ከአመታት በኋላ በሰድሜ ጠገቡ የዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ቆመናል፤ ውሃው ድፍርስ ነው፤ መሰስ ብሎ ይወርዳል። እኛ ከቆምንበት ወደ ማዶ ቢለካ 50 ሜትር አይሆንም፣ ማዶ ደግሞ የእስራኤል ግዛት ነው፣ ጨክ ብሎ ቢያውሩ አንኳ ይሰማል። አይኔ እስከደከመ ድረስ የዮርዳኖስ ወንዝ ከላይ የሚመጣበትን ሸለቆ እየሁ፣ ወደሚገባበትም ሙት ባህር ደረስ

ወደ ገጽ 39 ዞሯል







መፍትሄ... ከገጽ 32 የዞረ

አዳራሹ ክፍሉ ከመጠን በላይ ሰው በመብዛቱ አደጋ ቢደርስና ደጋሾች በህግ ቢጠየቁ ከቅርብ ወገኖቻቸው በቀር ሌላው እንግዳ ከንፈር ከመምጠጥ አልፈው ለጋባዦች እንደማይደርሱላቸው እውን ነው፡ ፡በእነዚህና በተንደኛ ነገሮች ደጋሽና ምግብ አዘጋጅ ደርጅቶችን ለማጭትና ጥርጣሪ ላይ ለመውደቅ በተደጋጋሚ ዳርጓቸው እንደነበር ትዝታቸውን ለአሐፊው ሲያካፍሉ ሰሐተቱ የማን እንደሆነ ዳኝነቱን ለአንባቢያን ሰጥተዋል።

ይህ ሁናቴ እንዳይፈጠረና ካልታሰበ ወጪ ለመዳን አንግዳው በሚገባ ተስተናግዶ እንዲመለስና ድግሱም እንደታሰበው ተከናውኖ እንዲጠናቀቅ በማሰብ ኑሮን በዘይ ይዞ በበጀት እየተመሩ መኖር የሰለጠነው አገር ህዝብ የሚከተለውን የአኗኗር ዘይቤ የቀሰሙ ሰዎች የድግሳቸው አካሄድ ለየት ባለ ውጥን ጀምሮ ለመጨረስ ሲሉ አባክዎ በሰዓቱ ይገኙልን፤ "ልጆችና ያልተጋበዙ አንግዶችን አስከትለው አይምጡብን" ብለው በግብዣ ጥሪው ወረቀት ላይ መልዕክት ያስፈሩ ትን ጋባዥ ቤተሰብን ለወቀሳ ማድረሱ ተሰምቷል።

ይሁንና የጋባዦቹ ዋና ዓላማ ድርጊታቸውና ጥሪታቸው ለኑሮአቸው እገዛ ከማድረግም አልፎ ጊዜያቸውን፤ጉልበታቸውንና ገንዘብ እንዲቆጥብላቸው የወሰዱት እርምጃ እንጂ የሰው ጥላቻ አይመስለንም።

ነገር ግን ሕብረተሰባችን ምንም በሰለጠነው አገር ቢቆይና ቢማር ከኋላ ቀር ባህሉ ያልተላቀቅን ስላለን የግላችንን ጥቅም ብቻ በመመልከት እንግዶች ይጋበዙ አይጋበዙ በምን ያውቀሉ በማለት የፈለግነውን ሰው ይዞ ወይም ጠባቂ በማጣት ለእካለ መጠን ያልደረሱትንና በዕድሜ ከፍ ያሉ ልጆችን ይዘው የሚመጡ እንግዶች አንዳሉ ሁላችንም የምናውቀው የሕብረተሰብ ገዳያችን ነው።

በተለይ ልጆች ይዘው የሚመጡ እንግዶች "ልጆቼን ያለ ከእንጀቱ እኔን ያለ ከእንቴ" (If You Love Me, You Love My Kids. if not you hate my kids) በሚል ምክንያት ልጆች አመጣችሁ ብሎ አስቲ ይመልሱኝ በማለት በድፍረት ጠቅላላ ልጆቻቸውን አግተልትለው በግብዣው ላይ ለተገኙ ወላጆች እንዳንዶችም "ልጆች አታምጡ ብሎ መናገር ባህላችን አይደለም ድግሳቸው ይቅርብኝ ልጆቼ ይበልጡብኛል" ብለው በልጆቻቸው ምክንያት እፈግጥው በግብዣው ላይ ያልተገኙና ቅያሜ ያተረፉ ሰዎች እንዳሉ በቁም ነገር ያጫወቱ ጋባዦች ነበሩ።

እንደ እኛ ጎብረቱሰብ አይብዛ እንጂ እንዳንድ የአገሩ ሰዎችም የእኛኑ ድርጊት ሲፈጽሙት ይታያል። የጊዜ አጠቃን በተመለከተ ከደሃና ከሃብታም ትርፍ ጊዜ ያለው ሀብረተሰብ ማነው በሚለው የጥናት መንስኤ የተገኘው ውጤት አነስተኛ ገቢ ያለው ሀብሀረተሰብ እንደሆነ "Why the Rich Now Have Less Leisure Time than the Poor"በሚል ርዕስ The Economist April 18, 2014 በወርሃዊ መጽሄት ላይ የአጥኒ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ጠቅሶ ያውጣው ጽሁፉን ለአንባቢያን እንዳተረበ የአነበብን ሰዎች አንኖር ይሆናል።

ጥናቱ አንዳመላከተው በቀጠሮ ሰዓት የሚዘገዩ በአርግጥም አንደ እኛ አነስተኛ የገቢ ምንጭ ያለው ሕብረተሰብ ለመሆኑ በተግባር የተረጋገጠ ስለሆነ ተጨማሪ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚያሰፈልግ አይመስልም።ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፍና በቀጠሮ ሰዓት ላለመገኘት እንቅፋት የሆነን ዋናው

ወደ ገጽ 35 ዞሯል

ቀመሻ 1

በአገራችን የሚሰጡ ቅጽል ስሞች - የርስዎ የትኛው ይሆን? የማንን ያስታውሳሉ?

(አፈንዲ ሙተቂ)

1. ግሰሌ
2. ኒያላ
3. ፒተር
4. ሮዝማን (አራቱም የሲጋራ ስሞች ናቸው)
5. ጀርመን
6. ጅቡቲ
7. ሃርዲም
8. ዲንዲን
9. ቦኪ
10. አምቦ
11. አንጫር
12. ቦርዶዲ (እነዚህ በቦታና በሀገር ስሞች ነው የሚጠሩት)
13. ባዙቃ
14. ማይክል
15. ብሩህ ተስፋ
16. ኢሠፓ
17. ደርጉ
18. ወያኔ
19. ሻዕቢያ
20. WBO (የኦነግ ወታደራዊ ክንፍ ማለት ነው)።
21. ቄቶ (አከካም ማለት ነው፤ ሰውዬው ግን "አቤት" ይላል)
22. ፈልፈላ (መተተኛ ማለት ነው)
23. ጠንቋይ
24. ሽርተቴ
25. ጋሞራ
26. አሻንቲ
27. ቦጌምቦ (ሁለቱ የህንድ ፊልም አክተሮች ናቸው)
28. ቾንዲ
29. ሾልሾ
30. ሬንጌጅ
31. ቦቴ
32. ቢኖ
33. ጂንዶ
34. ከሚቾ
35. ቦምቢ
36. ኦሬንጅ
37. ታኪታ
38. መርዙ
39. ሽብሩ
40. ሲቲ
41. ኮማንደ
42. ዝቴ
43. መሎ
44. ሺልሚ (ከብቶችን የምትመጠው መዝገር ማለት ናት)
45. ቦንባ
46. ባሬ (ሁለቱ ስሞች ወሬ የሚያበዛ፣ ውሸት የሚቀድ፣ በሌለው ነው የሚኮፈሰን ሰው ነው የሚያመለክቱት
47. ማመኔ
48. ሽሜ
49. ፕርሶ
50. ዘንዶ
51. ጀዌ (በኦሮምኛ "ዘንዶ" ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ስማቸው "ጀውሃር" እና "ጀዋድ" የሆኑ ሰዎች በቁልምጫ የሚጠሩበት ቅጽል ነው)
52. ታጨር
53. አደባ
54. ራምቦ
55. በላቀላ
56. ጩቤው
57. ስንጢ
58. ወተሩ
59. ዳሎ (ዳለቻ)
60. ቀሮ
61. ግራጫ
62. ቦሪ
63. ሚሎ
64. ወፍጮ (ብዙ ጫት ለሚቅሙ ሰዎች የሚሰጥ ነው)
65. ሶስት ክስልሳ (ሶስት ብር ከስልሳ ሳንቲም ሰርቆ ሰለተያዘ ነው)
66. ቁሩንፋድ
67. ጁንፈልዬ
68. ሚሊሻ
69. ኩባ
70. ኢልኪ
71. ጃምቦ
72. ርቶ (አሁን በቅርቡ የመጣ ነው፤ ለወፍራም ሰዎች የሚሰጥ ስም ነው)።
73. ግራሩ
74. አምቡላንስ
75. ዲራ
76. ቲምቦ
77. ቀርንዲ (እነዚህ ሁለቱ የትምባሆ ዓይነቶች ናቸው)
78. ሽመድ (አማሩ የተንሻፈፈ ሰው ለማለት ነው)
79. ሽልንጌ
80. ቁምቢ
81. ሱቱ
82. በተሮ (እነዚህ ሁለቱ "ዘገምተኛ" ወይንም "ቀርፋፋ" ሰውን ነው የሚያመለክቱት)።
83. "እኒ" ("ልብ" ማለት ነው በኦሮምኛ)
84. መታ ("ራስ" ማለት ነው በኦሮምኛ)
85. መተራስ (ራሱን የሚያወዛውዝ ሰው ማለት ነው፤ በርግጥም ሰውዬ ራሱን እያወዛወዘ ስለሚሄድ አዲስ ሰው ይገረምበታል)።
86. ደረቱ
87. ለጴ (ይህኛውም "ደረቴ" ማለት ነው)።
88. ሎንቼ
89. ቲቶ
90. ቾምቢ
91. ቶዬ
92. ሞክሪ
94. እንበሴ
95. ነብሮ
96. ሚዳቆ
97. ኩሩጴ (በኦሮምኛ "ሚዳቆ" ማለት ነው)
98. ጫቁስን/ሽቁሴ (በልጅነቴ ብዙ ገድሎችን አብረን ከፈጸምናቸው ሰዎች አንዱ ነው)
99. ሀረንጉዳ (እንሽላሊት ማለት ነው-በኦሮምኛ)

"You must be the change you wish to see in the world."
Gandhi

ምርጥ የአፍሪካዊያን አባባሎች"

1፦"በችግርጊዜ ብልሀ ሰው ድልድይ ሲገነባ፤ ሞኝ ደግሞ ግድብ ይገድባል!! (ናይጀሪያዊያን)

2፦"ሀብት ሲጠቀሙበት እያለቀ ይሄዳል፤ ትምህርት ግን እየተጠቀሙበት በሄዱ ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል!! (ታንዛኒያ)

3፦"እውነቱን ላለማየት ዓይናችንን የምንጨፍን ከሆነ ልንማር የምንችለው ከአደጋ ይሆናል!! (ኬንያዊያን)

4፦"ከማሸነፍ ይልቅ በመሸነፍ ወቅት ብዙ ትምህርት ይገኛል!! (ጋቦናዊያን)

5፦" ሞኝ ጨዋታውን በሚለምድበት ጊዜ ተጨዋቹ ይበተናል!!"(አሻንቲዎች/

6፦" ምክር ልክ እንደ-እንግዳ ነው። የሚቀበለው ካገኘ ያድራል፤ የሚቀበለው ካጣ ግን የዚያኑ ቀን ተመልሶ ይሄዳል!! (ኮንጎዎች)

7፦" እዋቂዎች በበዙበት ቦታ የእጻማጭ ዕጥረት አለ!!"(ስዋሂሊ)

8፦" በአንበጣዎች መካከል የሚደረግ ፀብ ለከብቶች መዝናኛ ነው!! (ቦትስዋናዊያን)

9፦" ትልቅ ወንበር ብቻውን ንጉሥ ሊያደርግ አይችልም!!"(ሱዳናዊያን)

10፦" በረር ዶሮዎችን የመምራት ሃላፊ ካለው፤ ቀበሮን ጠባቂው አድርጎ መቅጠር ይኖርበታል!! (ሴራሊዮናዊያን)

11፦" ቤተሰብ ልክ እንደ-ደን ነው። ክፉት ሲያዩት ጥትጥት ያለ ሲሆን፤ ሲገቡበት ግን እያንዳንዱ የየራሱ ቦታ አለው!!" (ዘየራዊያን)

12፦" የገንዘብ ስልት ከጦር ሰልት ይበልጣል!! (ካሜርናዊያን)

13፦" ገንዘብ ማውራት ባይችልም፤ ውሸትን እውነት የማድረግ አቅም ግን አለው!! (ደቡብ አፍሪካዊያን)

14፦" ከገንዘብ ውስጥ ሰንጠጣ አዋቂ አየሆንን እንሄዳለን!!(አይቮሪኮስታዊያን)

15፦" እስኪያወራ ድረስ አያንዳንዱ ሰው ውብ እና ቀንጃ ነው!! (ዙምባቤዎች)

16፦" ያለሰዓቱ የሚጮኽ ዶሮ መንጋቱን ሳይሆን መታረዱን ያውጃል!!"(ኢትዮጵያዊያን)

ታሪኩ ወደ ፓሪስ ይመለደናል። ካመታት በፊት በአንድ ቤተ ኦፔራ ውስጥ የተከሰተ ነው። አንድ ዝነኛ ዘፋኝ የሙዚቃ ኮንሰርት ሊያቀርብ ተጋብዞ አድናቂዎቹ ትኬታቸውን ገዝተው የኮንሰርቱን ቀን ይጠባበቃሉ። በኮንሰርቱ ምሽት አዳራሹ አሰከገደፋ በሰው ተጨናነቀ። የኮንሰርት አቅራቢው ሰው ተጠበቀ። ፕሮግራሙን ያዘጋጀው ሰው በድንገት ወደ መድረኩ ብቅ አለና፤

‹‹ክቡራትና ክቡራን ታዳሚዎቻችን ስለ ጋለሙ ትብብራችሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። እንድ አሳዛኝ ዜና ደርሶኛል። ጊዜአችሁን ሰውነታችሁ በዚህ ምሽት በናፍቆት የጠበቃችሁት ዝነኛው አገሌ በድንገት ታሞ ስለቀረ ኮንሰርቱን ልናቀርብ አልቻልንም፤ ይሁን እንጂ በእርሱ ምትክ ከጋበዝነው ሌላ ሰው ጋር ባልተናነሰ መልኩ ጥሩ የመዝናናት ጊዜ እንደምታሳልፉ ተስፋ እናደርጋለን›› አለ።

ታዳሚው እጉረመረመ። የተተኪውን ሰው ማንነት አንኳ ለመስማት ትዕግስት አልነበረውም። የአዳራሹ ድባብ ከጋለ ድምፅ መዳያው ጨፈገገ። የተተካው ሰው ዝማጅቱን አቀረበ። አንደ ጨረስ፣ አዳራሹ በፀጥታ ተዋጠ፤ ከአንድም ታዳሚ ጭብጨባ አልተቸረውም።

ይህን ጊዜ በድንገት ካዳራሹ መግቢያ ላይ አንድ ትንሽ ልጅ ብድግ ብሎ ‹‹ባቢ፣ አደንቅሃለሁ! ለእኒ ድንቅ ነህ! የሚል የእድናቆት ጩኸት አሰማ። አዳራሹ አንደገና ነቃ፤ ከዳር እስከ ዳር ታላቅ ጭብጨባ አስተጋባ።

ሁላችንም በሕይወታችን አንዳንድ ጊዜ ብድግ ብሎልን፤ ‹‹አደንቅሃለሁ! ለእኒ ድንቅ ነህ! የሚለን ሰው ያስፈልገናል። !!!

ቀመጸ 2 ለጠቅላላ እውቀት

በሰው ልጅ ሰካል ዙሪያ ያሉ 20 አስደናቂ መረጃዎች፦

1. ሕጻናት እንደተወለዱ ቀለምን መለየት አይችሉም፤ በመሆኑም ሕጻናት እንደተወለዱ በጥቁርና ነጭ (Black and White) ነው የሚያዩት።
2. ልጆች ከሁሉም ወቅቶች በተለይም በጸደይ (Spring) ወቅቶች በፍጥነት ያድጋሉ።
3. ማንም ቢሆን ራሱን ኮርኩሮ መሳቅ አይችልም።
4. አባብ ቆዳውን መቀየሩ ይታወቃል። የሰው ልጅም በየጊዜው ቀሰበቀሰ ቆዳውን ይቀይራል - አርጌውን አራግፎ በአዲስ ይቀይራል። በአንድ የሕይወት ዘመንም አንድ ሰው በአማካይ 22 ኪሎግራም የሚመዝን ቆዳ አራግፎ ይተካል። አርጌው ቆዳም በየቀኑ በብናኝ መልክ ነው ከአካላችን የሚወገደው።
5. የሰው ልጅ ጥርስ ማብቀል የሚጀምረው ከመወለዱ ከ6 ወራት በፊት ነው።
6. ከሰውነትህ ጡንቻዎች ትልቁ አሁን የተቀመጥክበት ነው።
7. የዓይናችን መጠን በሕይወት ዘመናችን አይጨምርም አይቀንስም። በአንጻሩ ጆሮ እና አፍንጫ ግን በሕይወት ዘመናችን ማደጋቸውን እያቋርጡም።
8. ሰውነታችን ውስጥ ያሉ የደም ቧንቧዎች ቢዘረጉ 96 000 ኪሎሜትር ይረዝማሉ - ይህም የመሬትን ወገብ ከ7 ጊዜ በላይ እንደማለት ነው።
9. በድንጋጤ አልያም በሌላ ምክንያት ፊታችን ሲቀላ፣ በዚያው ቅጽበት የጨጓራችንም ግድግዳ ይቀላል።
10. የአንጎላችን 80 % ውሃ ነው።
11. ሰናነጥሰ የልብ ምታችንን ጨምሮ ሁሉም የሰውነታችን ክንዋኔዎች ይቆማሉ።
12. ጸጉራችንና ጥፍራችን የተሰሩት ከተመሳሳይ ነገር ነው።
13. ምላሳችን ላይ ያሉት ለመቅመስ የሚረዱን ሕዋሳት በየ10 ቀኑ ሞተው በሌላ ይቀየራሉ። ሕጻናት ከአዋቂዎች የበለጠ ብዙ የመቅመሻ ሕዋሳት ምላሳቸው ላይ አለ።
14. ምግብ ስንውጥ በ7 ሰከንድ ውስጥ ጨጓራችንጋ ይደርሳል።
15. ሕጻናት ሲወለዱ የጉልበት ሹሚ (Knee cap) የላቸውም። ሹሚው ብቅ የሚለው ከ2 አሰከ 6 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።
16. ልባችን በቀን ውስጥ 100 000 ጊዜ ይመታል።
17. ከሰውነታችን አጅግ ጠንካራው ጡንቻ ምላስ ነው።
18. በአማካይ በሰውነታችን ውስጥ 100 ቢሊየን የነርቭ ሕዋሳት አሉ።
19. ስንወለድ ሰውነታችን ውስጥ 300 አጥንቶች ነበሩ። አዋቂ ሰው ስንሆን ግን በሰውነታችን ውስጥ ያሉት አጥንቶች ቁጥር ወደ 206 ዝቅ ይላል። የዚህም ምክንያቱ የተወለኑት አጥንቶቹ አሰር በርስ ስለሚገጥሙ ነው።
20. በመሐከለኛው ጣታችን ላይ ያለው ጥፍር ከሌሎቹ በላቀ ፍጥነት ያድጋል።

"ይህን ያውቁ ኖሯል!?"

፦....."The Quick Brown fox jumps over the lazy dog!" ከ1885 አንደ-ኤርፐያውያን የጊዜ ቀመር አንሰቶ የሚታወቀው፦"ፈጣንቀ ቡናማ ቀበሮ በሰነፍ ውሻ ላይ ተዘላለች!!" የሚለው የእንግሊዘኛ ዐረፍተ-ነገር 26ቱንም የእንግሊዘኛ ፊደል ይዘዋል!! በቀድሞ የ5ተኛ ክፍል የእንግሊዘኛ መማሪያ መማፍ ላይ አስታወሳችሁት? ይሄ ዓረፍተ ነገር ከተፈጠረ ዘንድሮ 131ኛ ዓመቱ።

፦.....ከአውሮፕላን ላይ ለአደጋ ጊዜ የሚዘለልበት ፓራሹት ከተሰራ በኃላ ይሰራል? አይሰራም? የሚለውን ለማወቅ መጀመሪያ የተሞከረው በውሻ ነበር።

፦.....እ.ኤ.አ በ1997 የዛየሩ ፊላሜ-ቶራሜ ፕሬዝዳንት የነበሩት፦"ሞቡቱ ሴ ሴ ሴኮ" በካቢላ የሚመራው አማፂ ቡድን ከሰልጣን ካስወገዳቸው በኃላ፦አዲስ ለማሳተም የሚወጣውን ወጪ ለመቆጠብ ሲባል ከህገረቱ የገንዘብ ኖት ላይ ምሥላቸው ብቻ ቆርጠክም አንዲወጣ ተደርጎ ገንዘቦቹ ይሰራባቸው ነበር።

፦..... ...ኮካ-ኮላ ምርቶቹን በብዙ ሀገሮች ውስጥ በመሸጥ ተወዳዳሪ የሌለው ኩባንያ ነው። በአሁኑ ሰዓት ኮካ-ኮላ በፎፈ የማይሸጥባቸው ሁለት ሀገሮች ኩባና-ስሜን ኮሪያ ብቻ ናቸው። ኩባ ከ1906 ዓ.ም ጀምሮ ከ-USA ውጪ ኮካ-ኮላ ከሚገኝባቸው ማንባር ቀደም ሀገሮች አንድዋ ነበረች፤ ሆኖም ከፊደል ካስትሮ የኩባ አብዮት በኃላ ኮካ-ኮላ የሚሰል በዓይኔ አያሳየኝ ብላ ሀገርዋ አንዳይገባ አገደች!!...

.....በቅርቡ አባማ የሁለቱን ሀገራት የዘመናት ኩርፊያ በዲፕሎማቲክ ዕርቅ ለማደስ የሄዱበት መንገድ ሙሉ በሙሉ ሽጋ ከሆነ ይሄ ቱሙልድ በዚያች ሀገር ኮካ ይጠጣ ይሆናል፤.....ሰሰሜን ኮሪያ ግን ኮካ-ኮላ ምንድነው? አስኪባል ጉበቶ አያውቅም።

፦.....በዓለማችን የሚገኙ አህጉራት ማለትም፦.....አፍሪቃ፤ አውሮፓ፤ አስያ፤ አንታርቲካ፤ አሜሪካ፤ አውስትራሊያ..... በእንግሊዘኛ ፊደል ሲፃፉ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደሎቻቸው አንድ አይነት ናቸው።

፦.... .....በመካከለኛው ማዳጋስካር ፋምዲዛና አየተባለ በሚጠራ ልማድ በየ7 ዓመቱ ሰዎች የሞቱ ወላጆቻቸውን አስክሬን ከመቃብር አውጥተው ሽቶ ከቱቦዋቸው በኃላ፦ አዲስ ልብስ በማልበስ አስኪበቃቸው ዳንስ ያስደንሱዋቸውና መልሰው ይቀብሩዋቸዋል። !!!!!

"እንቅልፍ ነው ሚያስወስድህ"

"ዜም አልኪችው ዝም ይበሉኝ
ትኾቸዋለሁ ይተዉኝ
አልነካቸውም አይንኩኝ"
ብለህ ፥ ተገልለህ ርቀህ
እውነት ይተዉኛል ብለህ
እንደት ተሰፋ ታደርጋለህ?!....
ተሰፋ አርገህስ ምን ልትሆን ፥
ወይስ ተሰፋው ምን ሊሆንህ?
እንቅልፍ እንጂ አሚያስወስድህ ።
"አልጠራቸውም አይጥሩኝ
አይንኩኝ ስሜን አያንሱሻ"
ብለህ እንደት ትመኛለህ ፥
እንደማይቱዉህ ስታውቀው
የተመጋ በቅቶት ቢኖ ፥
የመጋ መች እንቅልፍ አለው
የጅምሩን ካልጨረሰው?
የተበደለ ቢችልም
ቢሸሸግም ቢደበቅም
የበደለ ዝም አይልም ።
እንደት አሰችሎት ዝም ይበል?
ለፍልፎ ከማስለፍለፉ
አደል እንዲ የሱ ቤዛ ፥
የበደሉ ጥቅም የግፉ
ሰላም መንሳት አደል ትርፉ? ..
ዝምማ ካለ ጉድ ፈላ
ነገር በጤና ሲብሳሳ
አደደር ሲጣራ ኋላ
ግፉ ይፈ ይሆናላ! . . . .
ሰላምማ ከለገሠህ
ሕመምህ አየታወስህ
ትዝታ አየቀሰቀስህ
የሕሊናም ሚዛን ረግቶ፥
ጉዱ ሁሉ ኩልል ሲል
ያደፈረሰው ሲያጠልል
እግዜር ያሳያችሁ ብለህ ፥
ፍረዱኝ ዳኜኝ እንዳትል
ከነአካቴው ሳይጨርስህ
ምን ቢሆን ሰላም አይስጥ ።
አሱስ ቢሆን ያለትክሉ ፥
ያላጥንቱ የሰላም ውርስ
ከቶ የማያውቀውን ቅርስ
ይሰጠኝ ብትል የት ይሆናል
ያልተዘራ መች ይበቅላል? . . . .
የጋር ጉመን ሲያጠላ
አዋፊ ቅሉን እንዲያፈላ
እንዲያው በነገር ቀደም ፥
እንደሱስ ስሙን ቢለፍፍ
ሰላምን የሰጠህ መስሎህ፤
በጉንት ሰታሰፈሰፍ
ተሰላልሰህ እንደታተትክ፥ ተሰፋ
አርገህ እንዳትል አርፍ ።
እና ዘበት ነው ዋረትህ
በክንቱ ተሰፋ ማድረግህ
ሳያዋጣ መመኘትህ
የሰላም ቅዠት ማየትህ
ምን ልትሆን? ምን ሊሆንህ? . .
ይቅርብህ ። በኔ ይሁንብህ
እንቅልፍ ነው እሚያስወስድህ ።

ባለቅኔ ሉሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን

ወደ ዮርዳኖስ ..ከገጽ 34 የዞረ


አይኔን ሳላረፍኩ። ተነግሮ የማያልቅ ተሰምቶ የማይጠገብ ታሪክ ባለው የወንዝ ዳርቻ ቆሜ ወደ ኋላም ወደፊትም አሰብኩ።

የዮርዳኖስ ወንዝ 360 ኪሎ ሜትር ይጓዛል። አነሳሱ ከሶሪያና ከሊባኖስ መሰን ኬሔርሞን ተራራ ጥግ ነው። ወደ ደቡብ እየፈሰሰ በእስራኤል ሰሜን በኩል ወደ ገሊላ ባህር ይወርዳል። እስራኤልንና ዌስት ባንክን ከጆርዳን ጋር እያዋሰነ ወደ ሙት ባህር ይገባል። የዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠጥና ለመስኖ ልማት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ የፖለቲካና የጦርነት መነሻ ሲሆን ቆይቷል።

"የፀብ መጀመሪያ ውሃ መከልከል ነው" እንደሚባለው ሶሪያ፣ ዮርዳኖስና ሊባኖስ እስራኤል ሊሟሉት በፈለጉ ጊዜ ውሃቸውን አቅጣጫው ተስተውሟል፤ ምልዓቱም ቀንሷል ይባላል፤ ተፈፀሙ የተባሉት የታሪክ ክስተቶች ለምሳሌ፦ ክርስቶስ የተጠመቀበት፣ ንፅሳን የነገበት፣ ኤልያስ የተሻገረበት እዚህች ቦታ ነው ብሎ መናገር ያስቸግራል። የሚያሰማማው በዚያው አካባቢ ነው ማለቱ ነው። በዚህ ወንዝ ጦርነት ተነስቷል፣ ተግምራትም ተሰርቷል።

የዮርዳኖስን ወንዝ ታሪክ ከአብርሃምና ሎጥ ወዲህ እንኪን ብንጀምረው ሊነሳበት የሚችለው ታሪክ እጅግ ብዙ ነው። አስራኢላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጥተው ኢያሱ ወደ ተስፋይቱ ይህም ብቻ እይደለም፣ ነብዩ ኤልሳዕ የሶሪያውን የሰራዊት አለቃ ንዕማንን ከለምፁ የፈወሰው በዮርዳኖስ ወንዝ እጥምቅ ነው። "በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ታጠብ፣ ስጋህም ይፈወሳል" አለው ኤልሳዕ።

ንዕማን በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያለ ተጠምቆ ከለምፁ ነፃ። እነዚህን የመሰሰሉ ቢነገር የማያልቅ፣ ቢሰማ የማይሰለች ታሪኮች የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶታል። እነዚህ በብሉይ ኪዳን የተፈፀሙ የዮርዳኖስ ወንዝ ድንቅ ታሪኮች በኋለኛው ዘመን የኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቂያ በመሆን የበለጠ ታድሰዋል።



ኢየሱስ ክርስቶስ ከዛሬ 1975 ዓመታት በፊት እዚያው አኛ በቆምንበት በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። እንግዳ ተቀልቶ የተገኘለው መጥምቁ ዮሀንስ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው። "ከውሃ በወጣ ጊዜም ሰማያት ተከፍተው፣መንፈሰም በእርግብ አምሳል ወርዶ ተናገረ" ይላል መፅሀፉ። ይህንን ሁሉ የዮርዳኖስ ወንዝ በዘመናት ቆይታው ይመሰክራል። እኛም እነዚያ ሁሉ አስደናቂ ተግምራቶች የተፈፀሙበትን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት የዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠመቅ ከዳርቻው ቆመናል።

ሁለት የዮርዳኖስ ወታደሮች ጠመንጃቸውን ይዘው በዳርቻው ይንጎራደዳሉ። ከማዷችን ከእስራኤል በኩል 50 የሚሆኑ ጎብኚዎች ቁስ ይዘው ይጠመቃሉ። የእስራኤል ወታደሮች እየተንጎራደዱ ደጋግመው ያዩናል። ዕለቱ ቀዝቃዛ ነው፣ ወንዙም ውርጭ ሆኗል፣ ግን የደስታችን ግለት ሰለ ቅዝቃዜው ለማሰብ ፋታ አልሰጠንም፤ ከመፃመድ ሱቅ የገዛነውን ቀሚሳችንን እጠለቅን። በአንጪት መወጣጫ ላይ እየተራመድኩ ቀድሜ ወደ ባህሩ ገባሁ፤ የመሰላሉን እንጨት በእንድ እጄ ይዤ እስከ ደረቴ ተዘፈቅኩበት፤ ወደ መሃል ዋልቀት ስላለው ከዚያ በላይ ማሰፋ አይቻልም፤ ከልጅነት ጀምሮ ሰለ ዮርዳኖስ ወንዝ ክብር ሲሰማ ለነበረ ሰው፣ የዮርዳኖስን ወንዝ የተጠመቀ ሰሞት ሲጋው አይፈርሰም መባሉን እየሰማ ላደገ ሰው፣ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቅ የሚሰጠው ሰሜት ምን ያህል እጥግ እንደሚደርስ ይገባኛል። የዮርዳኖስን ወንዝ ውሃ በብልቃጥ ለማግኘት እግር እየሳመ ስናረ ሰው በጥልቁ የዮርዳኖስ ወንዝ፣ ክርስቶስ በተጠመቀበት ወንዝ፣ እስከ ደረቱ ለመዘፈቅ ሲበቃ የጋለ ሰሜት ይሰማዋል፤ እናም የጋለ የደስታ ሰሜት ተሰማኝ።

ወደ አገሬ ስመለስ የሚያውቀኝ አብዛኛው ወደ ዮርዳኖስ መሄዴን ሲሰማ የሚጠይቀኝን አሙቱዋስሁና በሰበሰብናቸው የላስቲክ ጠርሙሶች ያለከልካይ የዮርዳኖስ ውሃ ቀዳሁ። በጥንቱ ዘመን በዚያ ሁሉ በረሃ በአግራችው እየተንዙ ከዮርዳኖስ ውሃ የሚያመጡትን መነኮሳትንም አስታወሰኩ፤ በአሀያ ጭነው በትከሻቸው ተሸክመው የሚወሰዱትን እኔ በአውሮፕላን ለማምጣት ምን ያስቸግረኛል!

በተጨነገ የደስታ ሰሜት ፈዝዘን በዳርቻው በፀጥታ ቁጭ እልን፤ ግን ሁሉም ነገር ማብቂያ አለው፤ ጊዜያችን ውስን ነውና ሰሜታችን ያልፋል። የማይመሰን ጊዜ ያሳቸው የዮርዳኖስ ወንዝና የጨው ባህር ናቸው። ወደ ሙት ባህር የዮርዳኖስን ወንዝ ወደሚውጠው የጨው ባህር መሄድ አለብን። የዮርዳኖስን ወንዝ ወደኋላችን ልንተወው ነው። "እንተ የታላላቅ ክስተቶች መምጣትና መሰውጥ ምስክር የሆንክ የዮርዳኖስ ወንዝ ደህና ሁን" አልነው።

ወደ ገጽ 89

ለመገደብ ተነሱ። አስራኤልም የሕልውናዋ መሠረት አድርጋው ወደ ጦርነት ገብታለች። የእስራኤል ከፍተኛ መሪ አዛዥ እንደተናገሩት የሰድስቱ ቀን ጦርነት መነሻ የዮርዳኖስን ወንዝ የማግኘትና ያለማግኘት ጥያቄ ነበር። የዮርዳኖስ ወንዝ ማለት የመካከለኛው ምስራቅ ምስቅልቅል ማጠንጠኛ መሆኑ ነው። በአማኖች ዘንድ ግን ከዚህ የላቀ ዋጋ የሚሰጠው ከዓመተ ዓለም አስከ ዓመተ ምህረት የእምነት መገለጫ መሆኑ ነው። ከአብርሃም አስከ ክርስቶስ ድረስ የዮርዳኖስ ወንዝ በርካታ ተግምራቶች የተፈፀሙበት መሆኑን መፅሀፍ ቅዱስ ይተርካል።

የዮርዳኖስ ወንዝ በመሬት መንቀጥቀጥና በጊዜ ብዛት



በኃይሉ ኪሴ

የቀድሞ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ዘላለም ተሾመ አፄር የህይወት ታሪክ



ዘላለም ተሾመ - ከእባቱ ከአቶ ተሾመ ታደሰ እና ከእናቱ ወ/ሮ ዮብዳር ማርዬ አ.ኢ.አ. በ1959 በአዲስ አበባ ከተማ፣ ልደታ አካባቢ ተወለደ።

ዘላለም ተሾመ አድሜው ለትምህርት ሲደርስ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በፍራህይወት ትምህርት ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተድሞ ልዑል መኮንን በአሁኑ አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት አጠናቋል።

ዘላለም ተሾመ በነበረው ከፍተኛ የስፖርት ፋላጎት እና ዝንባሌ በተለይ በአማር ኪስ ፉዉታ ላይ በማተኮር፣ ከሰፈር ቡድን ጀምሮ፣ በተበለና በከፍተኛ ደረጃ በተዋቀሩ የአማር ኪስ ቡድኖች ውስጥ ተሰትፏል። ዘላለም ተሾመ በተለያዩ ግዜያት፡

-በዮቱር አንበሳ የአማር ኪስ

-በባህር ትራንዚት

-በድሬዳዋ ምድር ባቡር

-በአንበሳ ትራንስፖርት የተጫወተ ሲሆን፤

-በመጨረሻም በኢትዮጵያ መብራት ኃይል የፕሪሚየር ሊግ ለሁለት አመት ያህል በቋሚ ተሰላፊነት ተጫውቷል።

ዘላለም ተሾመ በተሰለፈባቸው ቡድኖች ውስጥ በአማካይ እና አጥቂ ቦታዎች ላይ በመጫወት ባሳየው ከፍተኛ ችሎታና አቅም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞችን አይን ለመሳብ በመቻሉ፤ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በመመረጥ አገሩን በመወከል፣ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በመጫወት አኩሪ ግዲቱውን በመወጣቱ ይታውቃል።

ዘላለም ተሾመ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ከአገር በመውጣት በኬንያ --በ1983 ናኩሪ ትራንስከሃም የአማር ኪስ ቡድን

-ለጉርማይህ ፕሪምየር ሊግ አማር ኪስ ቡድን ተጫውቷል።

ዘላለም ተሾመ ከኬንያ ወደ አሜሪካ በማቅናት፤ በአትላንታ ጆርጂያ ለ22 አመቶች፤ በዋሺንግተን ዲሲ. ደግሞ ለ2 አመቶት ያህል ኖሯል። በዚህ ወቅት በተለይ ለአትላንታ የኢትዮጵያውያን አማር ኪስ ማያግ እና ተጫዋቾችን በፍጥር በማሰባሰብ ባደረገው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይታውቃል። የአትላንታ ቡድን በተለያዩ ግዜያት ለሞንጫ ሲሰይ፡ አቶ ዘላለም የቡድኑ ካፒቴን በመሆን ቡድኑን ለሞንጫ ያበቃ የኪስ አምበል ነበር።

በተለይም ቃዳቢ ህጻናትን በማሰባሰብ፣ በአካል እና በአእምሮ በማጠንከር፣ የአማር ኪስ ፉዉታን ለማሰልጠን ብዙ ጥረቶችን ያደርግ ነበር። የመጀመሪያውን ኢትዮጵያዊያን ቃዳቢ ቡድን በመመስረቱ፤ እርስ በርስ በሚጋጠም፣ የማበረታቻ ዋንጫ በመሸለም ብዙ ጥረቶችን ሲያደርግ ግዜውንና የግል ገንዘቡን ለዚህ በጎ አላማ አውሏል። ዛሬ የአትላንታ ኢትዮጵያውያንን በመወከል በየአመቱ ለአማር ኪስ ዋንጫ የሚጫወቱት በርካታ ወጣቶች፤ የዘላለም የኪስ ፕሮጀክት ውጤቶች ለመሆናቸው ሰራቹው ምሰክር ነው።

ከዘጓናት ቡድኖች በተጨማሪ፤ አትላንታ ውስጥ የነበሩትን በርካታ የስፖርት ቡድኖችን በማስተባበር፣ ቡድን በመስራት እና አደንዳንዴ ቡድን በሬስቶራንቶች እና ንግድ ቤቶች ስም አንዲጫወት በማድረግ፤ በአትላንታ የኢትዮጵያውያን የኪስ ፉዉታ በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚህም ሌላ "አፍሪካን ካረቢያን ዋንጫ" በሚል የውጭ አገር ቡድኖችን በማካተት ልዩ ልዩ ግጥሚያዎችን ያከናውን ነበር። አንዲሁም በአትላንታ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ሲደረጉ፤ በተለይ የኢትዮጵያ ሚሊኒየን በአትላንታ በድምቀት ሲከበር፤ የጃማይካ፣ የሁማሊያ፣ የናይጀርያ እና የኢትዮጵያ ቡድኖችን ለዋንጫ በማጫወት ታሪክ የማይረሳው መልካም ስራ አበርክቷል።

ዘላለም ከኪስ ፉዉታ በተጨማሪ፤ የሙዚቃ ፍላጎቱ ከፍተኛ ነበር። በሙያ አገር ለሚገኙ እና አርዲታ ለሚያፈልጋቸው የቀድሞ ኪስ ተጫዋቾች ገቢ አንዲሆን፤ ከአመታት በፊት አንድ ሙሉ የሙዚቃ አልበም አውጥቶ አንደነበር ይታወቃል።

ዘላለም ከሃያ አመታት በላይ በአትላንታ በነሞረነት ክቡየ በጓላ፤ ከሁለት አመታት በፊት በሰራ ምክንያት ወደ ዋሽንግተን ዲሲ. ተዛውሮ ቢሄድም፤ ዳግም ህዝቡን በስፖርት ዙሪያ ለማስባሰብ ከሚቀጥሉ አመት ጀምሮ በግንቦት ወር - ሜሞሪያል ቀን ላይ በመላው አለም የሚገኙ የቀድሞ አማር ኪስ ተጫዋቾችን በማስባሰብ አመቃዊ የስፖርት ፌስቲቫል አንዲደረግ፣ ከጓደኞቹ ጋር ጥሪት አደደረገ ነበር። የዘሀ አዲስ ፕሮጀክት ጅምር አትላንታ ላይ አንዲሆን በማሰብ፤ ከጓደኞቹ ጋር ይህን የማሰተባበር ስራ በመስራት ላይ አደለ ነው፣ ድንገተኛ ህመም ላይ መውደቁ የተሰማው።

ዘላለም ተሾመ ከወ/ሮ ጥሩነሽ የሰውርት ጋር ትዳር መስርቶ አንዲት ሴት ልጅ አፍርቷል። ዘላለም በህይወት ዘመናቹው በቤተሰቡ፣ በጓደኞቹ፣ በሰራ ባልደረቦቹ አጅግ ተወዳጅ የነበረ ፈርሃ እግዚአብሄር ያደረበት፣ አጅግ ደግና ሰው አፋቃሪ፤ ለሰው ልጅ ችግር ቅድሚያ የሚሰርስ ሰው ነበር። ዘላለም ተሾመ በደረሰበት ህመም ምክንያት በአሜሪካ አገር በህክምና ሲረዳ ቆይቶ፣ የጤናው ሁኔታ አየተባባሰ በመምጣቱ ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ፣ በተወለደ በ50 አመቱ ህዳር 28 ቀን፣ 2009 ዓ.ም. ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል። !!!!!

ቅድሚያ ጤና

እድሜን የሚያሳጥሩ 10 አደገኛ ነገሮች

በአለም የጤና ድርጅት መረጃ መሰረት በ2013 በአለም አቀፍ ደረጃ በህይወት የመቆያ እድሜ 71 አመት ነው።

ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት የአድሜ ጣሪያ እድገት አያሳየ መምጣቱም ይነገራል።
ለዚህም ውጤታማ ክትባቶችና መድሃኒቶች የሰው ልጆችን ህይወት የሚቀጩ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ማስቻላቸው በምክንያትነት ይጠቀሳል። ጤናማ የምግብ አመሳሰድ ባህል መዳበሩ፣ ምቹ የሰራ አውድ መፈጠሩና የንጽህና አጠባበቅ ልማድ መጎልበትም በህይወት የመቆያ እድሜ እንዲያድግ አድርጓል ነው የተባለው። መቼም ጤናማ እና ረጅም እድሜ መኖርን የሚጠላ የለምና እኛም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን 10 ነጥቦች አስተውለን ብንመለከታቸው መልካም ነው እንላለን።

1. ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ

ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ ለስኳር፣ ልብ፣ ስትሮክ እና ለተለያየ አይነት የካንሰር በሽታዎች በማጋለጥ እድሜን በከፍተኛ ደረጃ የማሳጠር አቅም እንዳለው ይነገራል። አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ በፋይበር የበለጸጉ ምግቦችን፣ ጥራጥሬዎችን፣ ዝቅተኛ የስብ መጠን ያላቸውን የወተትና ሰጋ ውጤቶችን መመገብ ለጤናማ እና ረጅም እድሜ ወሳኝ መሆኑን ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት።

2. መቀመጥ ማዘውተር

በ2015 በአሜሪካ ጆርናል ላይ የወጣ አንድ ጥናት የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን አለማድረግ ካለአድሜ ለመቀጨት አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክቷል።
የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች በሽታ የመከላከል አቅማችንን ከማሳደጋቸው ባሻገር የአተነፋፈስ ስርአታችን ጤናማ ያደርጋሉ። ለጡንቻዎች ጥንካሬ፣ የምግብ መፈጨትን ለማፋጠን፣ ለአስደሳች እንቅልፍ እና ከድብርት ለመገላገልም እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ተገቢ ነው።

3. በቂ እንቅልፍ አለማግኘት

የእንቅልፍ መብዛትና ማነስ በህይወት የመቆያ እድሜ ጋር ግንኙነት እንዳለው በ2007 ሰሲፐ ጆርናል ላይ የወጣ ጥናት ጠቁሟል። በቀን ውስጥ ከ6 ሰዓት በታች መተኛት ለ8 ሰዓታት ከሚተኙት ጋር ሲነጻጸር ካለጊዜያቸው ለሞት የመዳረግ አድላቸው ሰፊ ነው ተብሏል።

ከእንቅልፍ ስንነቃ የድካም ስሜት ከተሰማን እና ከመኝታችን የመነሳት ፍላጎታችን ከተዳከመ በአርግጥም በቂ እንቅልፍ አንዳላገኘን ማሳየ ስለሆነ በቀን ቢያንስ ለ8 ሰዓት መተኛት እንዳለብን ይመከራል። ጥሩ እንቅልፍ ለመተኛትም ቀለል ያለ ራት መመገብ፣ የመኝታ ክፍላችን ደብዘዝ ያለ ብርሃን እንዲኖረው ማድረግ፣ ከቴሌቪዥን እና ሞባይሎች መራቅ እንደሚገባ ነው የሚመከረው።

4. ውጥረት

ከፍተኛ ጭንቀት በሰውነታችን ውስጥ ኮርቲሶል የተሰኘ ሆርሞን እንዲጨምር በማድረግ ለልብ በሽታ፣ ለምግብ አለመፈጨት እና በሽታ የመከላከል አቅም መዳከም ይዳርጋል።

በ2012 በብሪቲሽ ሜዲካል ጆርናል ላይ የወጣ ጥናት የልብ ህመም እና ስትሮክ ከከባድ ጭንቀት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አሳይቷል። ስለሆነም ጭንቀት እና ፍርሃትን መቀነስ በሽታ የመከላከል አቅምን ለማሳደግ እና የበሽታ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ይጠቅማል።

ለዚህም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ፣ በቂ እንቅልፍ መውሰድ እና የተመሰጠ ጊዜ ማግኘት ይመከራሉ።

5. ሲጋራ ማጨስ

ሲጋራ በውስጡ ከ1 ሺህ በላይ ጎጂ ኪሚካሎችን የያዘ በመሆኑ በአጫሾች እና በዙሪያቸው በሚገኙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። ኪሚካሎቹ ለሳንባ ካንሰር፣ ለልብ በሽታ፣ ክቀዳ፣ ጥርስ እና ጉሮሮ ጋር ለተያያዙ ህመሞች በማጋለጥ አድሜን የማሳጠር አቅማቸው ከፍተኛ ነው።

6. አልኮል እና አጽ

ሌላኛው አድሜን የሚያሳጥር ነገር አልኮል እና አጽ መውሰድ ነው። ከድብርት እና ጭንቀት ለመውጣት በሚል ምክንያት የሚወሰዱ እንደ ኮኬን፣ ሄሮይን፣ ሜታምፌታሚን ያሉ አጾች በአጭር ጊዜ የህይወት ምስቅልቅል እንደሚፈጥሩ ይነገራል።

ከልክ ያለፈ አልኮል መጠጣትም ለጉበት፣ ለልብ እና ለስኳር በሽታ ከማጋለጡም ባሻገር የሰውነታችንን በሽታ የመከላከል አቅም በእጅጉ ያዳክማል። ብዙ ጊዜ የአጽ እና አልኮል ሱሰኞች ከድንገተኛ አደጋ፣ የግድያ ወንጀል፣ ሰላም ከራቀው ጋብቻ እና ራስን ከማጥፋት ሙክራ ጋር የተያያዙ ናቸው።

7. ለአፍ ንጽህና ትኩረት አለመስጠት

የአፍ ውይም የጥርስ ንጽህናን መጠበቅ በአፍ ውስጥ የሚገኙ ባክቴሪያዎችን ለማስወገድ ይረዳል። በአፍ ውስጥ የሚከማቹ ባክቴሪያዎች ካልተወገዱ ለኩላሊት፣ ልብ፣ ስትሮክ፣ ለስኳር በሽታ እና ለከፍተኛ የመርሳት በሽታ (አልዛይመር) ሊዳርጉ እንደሚችሉ ነው ተደጋግሞ የሚገለጸው።
ከአፍ ጋር የተያያዙ ህመሞች በአለማችን 743 ሚሊየን ሰዎችን የሚያጠቁ ሲሆን፣ በአሜሪካም ከሁለት ውሻቶች አንደኛው በዚሁ ችግር ውስጥ ይገኛል። የአፍ ውስጥ በሽታን ለመከላከል ጥርስን በየቀኑ ከማጽዳት ባለፈ የአፍ መድረቅን ለመከላከል የስኳር መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ ማስቲካዎችን ማኘክና በቂ ውሃ መጠጣት ይመከራል።

8. ለጸሀይ ብርሃን ተጋላጭነትን መቀነስ

በብዛት ለጸሃይ ብርሃን መጋለጥ ለቆዳ ካንሰር ተጋላጭነትን ይጨምራል የሚለውን በመፍራት አንዳንድ ሰዎች ከጸሃይ ሙሉ በሙሉ ይርቃሉ። ይሁን እንጂ በጠቅላላው ከጸሃይ ብርሃን መራቅ ለጤናችን አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ሲሆን፣ ተመጣጣኝ የጸሃይ ብርሃን በሰውነታችን ውስጥ የቫይታሚን ዲ መመረትን ያፋጥናል።
የቫይታሚን ዲ እጥረት ለተለያዩ የካንሰር አይነቶች፣ ለልብ ህመም፣ ለደም ግፊት፣ ለድብርት፣ በዘር ለሚተላለፉ በሽታዎች እና ሌሎችም በሽታዎች መነሻ እንደሚሆን ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

9. አሉታዊ አስተሳሰብ

አሉታዊ አስተሳሰቦች አስደሳች እና ምክንያታዊ ህይወት እንዳይኖረን ያደርጋሉ። ቁጣ፣ ፍርሃት፣ ግልፍተኝነትና ድብርት የአሉታዊ አመለካከት (Negative Thinking) ውጤቶች ናቸው።

በመሆኑም ክዚህ አሉታዊ አመለካከት ለመውጣት ሰላልን ነገር ማመስገን፣ መሳቅና መጨወት፣ ችግረኞችን መርዳት እና ውሏችን በመልካም ሰዎች የተከበበ እንዲሆን ማድረግ ይገባል።

10. ተደጋጋሚ የህክምና ክትትሎችን አለማድረግ

በተመሰነ የጊዜ ልዩነት የጤናችን ሁኔታ ወደ ህክምና ተቋማት በማምራት መከታተል በርካታ ጥቅሞች አሉት። የመጀመሪያው በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ ህመሞችን ከሰሩ ለመከላከል ነው፤ ቃሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ እንደሚባለው። ሁለተኛው ደግሞ ወጪን መቀነስ ነው።

የጡት ህመም፣ ኮሌስትሮል እና የደም ግፊት፣ የአዮንት ክብደት፣ የአንጀት ካንሰር፣ የጥርስ እና የመሳሰሉ ህመሞች በህክምና ተቋማት ከሚደረጉ ቀላል የምርመራ የማጣራት ስራዎች መካከል ይጠቀሳሉ። በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው 10 ነጥቦች በምንኖርባት ምድር የሚኖረንን ቆይታ ያሳጥራሉ ነው የሚሉው መረጃው።


ስለሆነም ህመም እጋጥሞን አልያም እንዲሁ ለጤና ክትትል ወደ ህክምና ተቋማት ስናመራ የእኗኗር ባህላችንን እና ጤናማ ያልሆኑ ስሜቶቻችንን በግልጽ መንገርና ከሀኪሞች የሚሰነዘርልንን ምክር ከልብ መቀበል ያስፈልጋል።

The End

አጫጭር ዜናዎች

ኢትዮጵያዊቷ እናት በመኪና አደጋ ህይወታቸው አለፈ

በዚህ በአትላንታ ከተማ ላለፉት 21 ዓመታት ነዋሪ የነበሩት ወይዘሮ



ብርሃን ሃድጎ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ህይወታቸው ማለፉ ተነገረ። ወይዘሮ ብርሃን ህይወታቸው ያለፈው ባለፈው ዲሴምበር 11 ቀን፣ በ አግራቸው ሲጓዙ መኪና ገጭቷቸው ነው። ወይዘሮ ብርሃን የ48 ዓመት ሴት ሲሆኑ አንዲት የ13 ዓመት ታዳጊ ወጣት እናትም ናቸው።

ታሪካቸውን የበለጠ አሳዛኝ የሚያደርገው፣ ባለቤታቸው አቶ ሃዲሽ አበራ ከ10 ወራት በፊት በህመም የተለዩዋቸው በመሆኑ ልጃቸው ያለ ወላጅ መቅረቷም ጨምር ነው። ነፍስ ይማር።

ኢትዮጵያዊው ኮሌጅ ተመራቂ ህይወቱን አጣ



ይህ አሳዛኝ ድርጊት የተፈጸመው ባለፈው ዲሴምበር 10 ቀን ነው የ 24 ዓመቱ ወጣት ቴዎድሮስ ፍሰሃ በድንገተኛ ሁኔታ ነው ህይወቱን ያጣው። ወጣት ቴዎድሮስ ፍሰሃ በዚህ ዓመት ከኤምሪ ዩኒቨርሲቲ በኦብር ተመርቀ ፣ የህክምና ዶክትሬት ዲግሪውን ለማግኘት በማያሚ ፍሎሪዳ ሚለር ስኩል ኦፍ ሜዲሲን ስኮላርሺፕ አግኝቶም ነበር።

በቤተሰቡና በጓደኞቹ ተወዳጅ እንደነበር የሚነገርለት ቴዎድሮስ ፍሰሃ ህይወቱን መቅጠፉ ሲነገር፣ ወላጆቹ፣ እንዲት እህቱ እና መላው ዘመድና ወዳጅ ይህ አሳዛኝ አጋጣሚ እንቅቅልሽ እንደሆነባቸው ተናገረዋል።

ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንዲህ ዓይነት ድርጊት ሲፈጽሙ መታየታቸው ማህበረሰቡን ሊያወያይ እና ለመፍትሄም ሊያተጋ እንደሚገባ ብዙዎች ይስማሙበታል።

የአፓርትመንት ዋጋ እየጨመረ መሄዱ ሊያነጋግረን እንደሚገባ ተነገረ፡

.... በዚህ በ2016 ዓ.ም የአንድ መኝታ ቤት አማካይ የኪራይ ዋጋ በአትላንታ 1300 ዶላር ሲሆን፣ የሁለት መኝታ ቤት አማካይ ዋጋ 1700 ዶላር ነው። የአንዳንድ አካባቢዎችን ዋጋ በወፍ በረር ሲቃኝም ዚፕ ኮድ 30363 ሁለት መኝታ ቤት አፓርትመንት 1840 ብር፣ .. ዚፕ ኮድ 30326 በክሄድ አካባቢ ሁለት መኝታ ቤት አፓርትመንት 1659፣ .. ዚፕኮድ 30327 ፣ 30307 እና 30306 - 1500 ለሁለት መኝታ ቤት አፓርትመንት ሲከፈል ...፣ ዚፕኮድ 30319 እና 30308 1400 አካባቢ፣ አንዲሁም ዚፕ ኮድ 30324 ፣ 1300 ዶላር ለሁለት መኝታ አፓርመንት ነው እየተከራየ ያለው። የአትላንታ የአፓርመንት ዋጋ ካለፈው ዓመት በ8% ጨምሯል ። በሌሎችም ከተሞች በተመሳሳይ መልክ እየጨመረ እንደሆነ



አሃዝች ያሳያሉ።

አዚህ ሜትሮ አትላንታ አካባቢ፣ ኢትዮጵያውያን በብዛት በሚኖሩበት በክላርክስተን ጆርጂያ የሚገኙ አብዛኞቹ አፓርትመንቶች አንድ መኝታ ቤት 650 ብር ፣ ለሁለት መኝታ ቤት 750 በአማካይ የሚያከራዩ ናቸው። ለምሳሌ ሃይላንድ ቪሌጅ አፓርመንት አንድ መኝታ ቤት 580 ዶላር ያከራያል። ኢንዲያን ቫሊ የተሰኘው አፓርመንትም እንዲሁ የአንድ መኝታ ቤት ዋጋው 520 ዶላር አካባቢ ነው። ቴስካኒ ቪሌጅ የተሰኘው አዚያው ክላርክስተን የሚገኘው አፓርትመንት ለአንድ መኝታ ቤት 544 ለሁለት መኝታ ቤት 650 አካባቢ ያስከፍላል።

ሲልቨር ኦክስ አፓርትመንት (ብዙ ኢትዮጵያውያን ይኖሩበታል) አንድ መኝታ ቤት 650 ሁለት መኝታ ቤት 860 አካባቢ ያከራያል። ዋይልድ ክሪክ አፓርመንት 825 እና 958 ዶላር ለአንድና ለሁለት መኝታ ቤቶች የሚያከራይበት ዋጋ ነው፣ .. ብዙዎቹ ግን ዕድሜ ጠገብ በመሆናቸው ከተማው እያደገ ሲመጣ በአዲስ መተካታቸው የማይቀር ነው። ለምሳሌ በጠቅላላ 356 አፓርትመንቶች ውስጡ ያለውና በርካታ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ክላርክስተን ስቴሽን የተባለው አፓርትመንት ከተሰራ 45 ዓመት ሆኖታል። ዋጋው ጥሩ በመሆኑ በአሁኑ ሰአት የሚከራይ ትርፍ ክፍል የለውም።

ነገር ግን ወደፊት በዚሁ ዋጋው ላይቀጥል ይችላል። ወደፊት አየተሰሩ የሚመጡት ደግሞ የሚሰሩት ዘመናዊ (ላግዠሪ) የሚባሉ ዓይነት አፓርትመንቶች ይሆኑና ዋጋቸው መጨመሩ አይቀርም።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የክላርክስተን ከተማ የአፓርመንት ኪራይ ዋጋ በ12% የጨመረ ሲሆን፣ ባለፉት አራት ወራት ብቻ ደግሞ 3% መጨመሩን አሃዞች ያሳያሉ። አስቀድሞ ራስን ማዘጋጀት ካሁኑ ተገቢ መሆኑን ለማሳሰብም እንወዳለን።

የዶናልድ ትራምፕ ቤተሰብ ኩባንያ ወደ ኢትዮጵያ ሊዞር ነው

የዶናልድ ትራምፕ ልጅ፣ የኢቫንካ ትራምፕ ጫማ ፋብሪካ ክቻይና ወደ ኢትዮጵያ ሊዛወር መሆኑን ዲይሊ ሚይል ዘግቧል፣ ምክንያቱ ደግሞ "በቻይና ለአንድ ሰራተኛ የሚከፈሉ፣



በኢትዮጵያ ለአምስት ሰራተኛ መክፈል ስለሚቻል ነው" ይላል ዜናው። አንደ ዲይሊ ሚይል ዘገባ፣ በቻይና ለጉልበት ሰራተኞች የሚወጣው ወጪ በመጨመሩ ፣ ኩባንያዎች እንደ ኢትዮጵያ ባሉና ርካሽ የሰው ጉልበት አለባቸው ወደሚባሉ የአፍሪካ አገሮች እየዞሩ ነው።

በዚሁ መሰረት የዶናልድ ትራምፕ ልጅ ኢቫንካ የምታስተዳድረው የጫማ ፋብሪካ ፣ ኢትዮጵያ ይዘራል ተብሏል። ፋብሪካውያንም ቻይናውያን ያስተዳደሩታል። ከዚህ በኋላ የሚመረተው የዶናልድ ትራምፕ ቤተሰብ ጫማ "ሜድ ኢን ኢትዮጵያ—በኢትዮጵያ የተሰራ" የሚል ምልክት ሊኖረው ነው።

አንጋፋው ኢትዮጵያዊ ጠበቃ ህይወታቸው አለፈ

አቶ ተሾመ ጉበረማርያም ይባላሉ። በ1923 ዓ.ም በሰዳሞ ክፍለሃገር የተወለዱት አቶ



ተሾመ ያረፉት በ86 ዓመታቸው ነው።

ወደ ገጽ 93»>>»>

የፎቅር ኸቡሬዳ

18+

ፋቀረርጎ ዶዞ መዝለቅ

የጥበቦች ሁሉ ታላቅ ጥበብ፣ ይዞ መዝለቅ

"ያላንቺ መኖር አልፈልግም፣ መቶ ዓመት የምትኖሪ ከሆነ፣ ለመቶ ዓመት አንድ ቀን አስኪቀረሙ ደረስ ብቻ ነው መኖር የምፈልገው"
ኤሌ ሚልን

ከስካሁን ባንብብናቸው ገፆች በወንድ ልጅ ሕይወት የሴት ልጅ ጥቅምና ተዕዕና ምን እንደሚመስል፣ መማረክ በወንድና በሴት መካከል ያለው ልዩነት፣ ሴትን መማረክ የሚችሉ የወንድ ብቃቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ አልፋ ወንድ ማለት ምን ዓይነት ወንድ እንደሆነ እንዲሁም የወደድካትን ሴት እንዴት ቀርበህ የግልህ ልታደርጋት እንደምትችል በዝርዝር ለማስረዳት ሞክሬያለሁ። ነገር ግን በፍቅር ግንኙነት ሂደት የጥበቦች ሁሉ ታላት ጥበብ የሆነው ጉዳይ ገና አልተነካም። ከላይ ያየሃቸው ጥበቦችና መረጃዎች በሙሉ የሚያስፈልጉትና የሚያገለግሉት ለዚህ "ይዞ መዝለቅ" የሚባል ታላቅ ጥበብ ነው።

የምትወዳትን ልጅ ይዘሃት ካልዘለቅክ...ማነጋገሩ፣ ስልክ ቁጥር መቀበሉ፣ መቀጣጠሩ፣ ጊዜያዊ ጣፋጭ የፍቅር ጭማቂ መጠጣቱ ምን ዋጋ አለው? ምክንያቱም አንዲት ሴት ማረካት፣ተዋወቅካት፣ በእጅህ አስገባሃት ማለት ዕድሜ ልክ ካንተ ጋር ትሆናለች ማለት አይደለም።

የምትወዳት፣ የምታፈቅራት ልጅ በተለያዩ ምክንያቶች ድንገት ብትለይህ በጣም አሳዛኝ ነው። በተለይ ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቃትህ ቀንሶባት ጥላህ ከሄደች ትርፍህ ስቃይ አዘል ትዝታ ነው የሚሆነው። ስለሆነም ይህንን "ይዞ መዝለቅ" ጥበብ ማወቅ ግድ ይላል። እንዲት ሴት ማርከህ እጅህ ከገባሃት በኋላ ካንተ ጋር ከላቂነት እንድትቆይ የሚያደርጓት ነገሮች ምን ምንድናቸው?

የሚሊዮን ብር ጥያቄ ነው!

ወንዱ ሴቶችን ለመማረክ ብዙ ብቃቶች እንደሚያስፈልጉት ሁሉ ይዞ ለማቆየትም በርካታ ብቃቶች ይጠበቁበታል። ወንዶች ያፈቀሩዋቸውን ሴቶች በዘላቂነት ይዘው ለማቆየት የሚጠበቁባቸው ዋና ዋና ብቃቶች የባህርይ፣ የስብዕና፣ የችሎታ እና የቁመና በሚሉ አራት ክፍሎች የሚጠቃለሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው በስራቸው አምስት አምስት ዝርዝር ብቃቶች አሏቸው። እንድ በአንድ እንመልከታቸው፦

ሀ. የባህርይ ብቃቶች

ታማኝነት

ሰዎች በፍቅር ግንኙነት፣በትዳር አብረው እንዲዘልቁ "ታማኝነት" ወሳኝ ሚና አለው። ሁሉም ብቃቶች ኖረውህ ለፍቅረኛህ እና ለባለቤትህ ታማኝ ካልሆንክ ሚስጦን ብቃቶችህ ተደማረው ሚዛን አይደፉም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለፍቅረኛሞችና ለባለትዳሮች መለያየት ቁጥር አንድ ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው ታማኝ አለመሆን ነው።

ኃላፊነት መውሰድ

ሴቶች ኃላፊነት መሸከም የሚችል...ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ወንድ ዘላቂ ፍላጎት እንዲኖራቹው ያደርጋቹዋል። የተዋሰውን መፅሐፍ አስታውሶ የሚመልስ፣ ቃል የገባውን የሚፈጽም፣ የእናቱን የጤና ምርመራ ቀን አስታውሶ አናቱን ሐኪም ቤት የሚወስድ ወንድ ሴቶች "ለባልነት ከፍተኛ አቅም ያለው" በሚል ያጨቃል።

ርህራሄ

ሴቶች አንድ ጊዜ ብቻ የሚኖሯት ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡት ወንድ ርህሩህ እንዲሆን አጥብቀው ይፈልጋሉ። ታክሲ ውስጥ ከታክሲ ረዳት ጋር፣ ካፌ ውስጥ ከአስተናጋጆች ጋር፣ መንገድ ላይ ከየኔ ቢጤ ጋር እንዲሁም በአጠቃላይ ሰዎችን ለማገዝና ለሰዎች ባለው ፍቅርና ክብር ይመዝኑታል።

ሐቀኝነት

ሃቅ ከታማኝነትና ኃላፊነት ጋር ይያያዛል። የሚዋሽ ሰው ታማኝ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። ለሚዋሽ ሰው ኃላፊነት መስጠት ይከብዳል። ስለሆነም ሴቶች ተሳስተህ እንኳን ትንሽ ስትዋሽ ከያዙህ ባንተ ላይ ያላቸው የወደፊት እምነት አደጋ ላይ ይወድቃል።



ጥሩ አባትነት

ሴቶች ጥሩ አባት የመሆን ብቃትና አቅም ያለው ባል እንዲኖራቹው ይፈልጋሉ። ይህ ብቃትና አቅም በአንድ ወንድ ውስጥ መኖሩንና አለመኖሩን ለመለየት አይቸግራቹውም። መንገድ ላይ ተበትነው ለሚታዩ የአኔ ቢጤ ሕፃናት ባለህ አመለካከት፣ ስለ ሕፃናት ሲነሳ በምትሰጠው አስተያየትና ስለወደፊት ልጆችህ በሚኖርህ ራዕይ ትለካለህ።

ሐ. የስብዕና ብቃቶች

ጨዋታ አዋቂነት

ጨዋታ አዋቂነት ሴቶችን ለማንበርከክ የምትጠቀምበት ውሳኝ መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ የምትወዳትን ልጅ ለመማረክ ከተኮሰከው በኋላ የምትጥለው ሳይሆን ዕድሜ ልክ የግልህ ልታደርገው የሚባል ፍቅረኛህን በዘላቂነት ማርከህ የምትይዝበት ኑክሌር መሳሪያ ነው። ስለሆነም ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ሳይሆን ዘላቂነት ያለው ጨዋታ አዋቂነትህን ልታሳያት ይገባል።

ብሰለት (ዕውቀት)

በየጊዜው ሊዳብር የሚችል ብቃት ነው። ሰለዚህ የበሰልክ አዋቂ ባትሆን እንኳ ለብስለትና ለዕውቀት ከፍተኛ ፍላጎት ያለህ የዘወትር ተማሪ መሆንህን በማንበብና ዕውቀትን በማባረር ልታሳያት ትችላለህ።

የዓላማ ፅናት

የምትወደውን ነገር ለማግኘት ያለህ ጉጉትና ትጋት ያቀድከውን ለማሳካት የምታፈሰው ጉልበትና ጊዜ ለዓላማህ ያለህን ፅናት ያሳያል። ባለ ራዕይና ራዕዩን ለማሳካት በየቀኑ ማልደ የሚነሳ ወንድ ጠዋት ጠዋት ጣፋጭ ቁርስ ሰርታ የምታቀርብለት መልካም ሚስት የማግኘት ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው።

በራስ መተማመን

መልክ መልካም ያልሆኑ ወንዶች መልክ መልካም ከሆኑ ወንዶች በበለጠ ሁኔታ ሴቶችን የሚማርኩበት ድምፅ አልባ መሳሪያ ነው- በራስ መተማመን። በራስ መተማመን በዕውቀት፣ በችሎታ፣ በሰራ፣ በስኬት...እንዲሁም ራስህን ደጋመህ በማለመን የሚገነባ ብቃት ነው። በድንገተኛ አውሎ ነፋስ የሚፈርስ ሳይሆን በዘላቂነት ካንተ ጋር በሚቆይ መልኩ አድርገህ ገንባው።

ቸርነት

ስግብግብነት መቼም የሚደነቅ ብቃት ሆኖ አያውቅም። መልካም

ወደ ገጽ 63 ዘሯል



መፍትሄ ያጡ ...

ከገጽ 35 የዞረ

ምክንያት ካለመከባበርና ከመናናት የተነሳ ነው። ምክንያቱም በዓይን ለማየት እንደተቻለው የውጭ አገር ዜጋ በሆኑ ሰዎች ስንጋበዝ እንኳን መዘግየት ቀርቶ አልፎ ተርፎን ቀድመን ስንገኝ እንታያለን።

መደምደሚያ ከላይ ለአብነት ያህል ስለተጠቀሱት የባህል፤የትውልድ ዘመን ልዩነት(Generation Gap) ባመጣው ችግር የመከባበር፤ የመናናትና በጊዜ አጠቃቀም ላይ ትኩረት ቢሰዋባቸው ለልጆቻችን አርያ ሆነን ለመገኘትና ክብር፤ ሞገስና ምስጋናን ለማትረፍ ይረዳል!!

ይህን የየግል ኃላፊነት ሰራ በአግባቡ ለመጠቀም ያስችል ዘንድ የጊዜ አጠቃቀም ዘዴን በመጠቀም የሰዴት ኑርአችንን ሂደት ማስፈጸሚያ መማሪያ አድርገን ካልተገለገልንበት በቀር መማርና በውጭው ዓለም መኖር ብሎም ከአጠቃቀም ጉድለት በሰዓት አጥረት ማመካኘት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።

የአገሩን ጎብረተሰብ እንደ ምሳሌ አድርገን ብወስድ አንኳ ሰፋ ያለ ድግስ ለማካሄድ ሲወጥኑ ልጆች እንደሚመጡ ስለሚገምቱ የልጆች ማስተናገጃ ክፍልና ጠባቂ ሰው አስቀምጠው ልጆና ወላጆችን ለየብቻቸው አያስተናገዱ በመሸኘት መስለው ይኖራሉ።ልጆች ያሳደጉ ወላጆች እንደሚረዱት በተለይ በሳምንቱ ማለቂያ አካባቢ ልጅ ጠባቂ ሰራተኛ አግኝቶ ለመቅጠር አስቸጋሪ ነው!!

ሠራተኛ ከተገኘም አጠረት መኖሩን ስለሚውቁ ከፍ ያለ ክፍያ ሲጠየቁ ወጪ ለመቀነስ የልጆችን ጉዳይ ትኩረት ሳይሰጡት ስለሚያልፉት ያልተጠበቀ ችግር ውስጥ ማለትም ለተከራዩት ክፍልና ውንበር መቀሽሸ፤ ተጨማሪ ወንበርና ጠረጴዛ ይምጣልኝ ጥያቄ፤ ለአቃ መስበር ክፍያ ውዝግብ ውስጥ ይገባሉ።

ይህ ችግር መኖሩን ሁሉም ሰው ቢያውቅም የመዘግየቱና ያልተጋበዙ ሰዎችን አስከትሎ መምጣት ጉዳይ አሁንም መፍትሄ ያልተገኘለት አንገብጋቢ ጉዳያችን ሆኖ እየታየ ማስተካከል ሲገባ ልጆችም እንደኛው እየዘገዩና ጓደኞቻቸውን አስከትለው አንዲመጡ የሚጋብዙ ስላሉ ስህተቱን ለማስተላለፍ ታጥቀን የተነሳን ይመስላል።

ያልተጋበዙ እንግዶችን ለመቆጣጠር ካስፈለገ "የግብዣ ወረቀቱ አይለየወት" የሚል መልዕክት ካስቀመጡ ቁጥጥር እንዳለ እንግዶችም ስለሚጠረጥሩ ተላጠፈ ሰው/ ከአንድ ልጅ በላይ አስከትሰው አያመጡም። ስለሆነም በቀጥሮ ሰዓት መገኘትና ደጋሾች ያወጡትን የመስተንግዶ ህግጋት ማክበር ከላይ የተመለከቱት ችግሮች በደጋሾች ላይ እንዳይደርስ እንዲሁም እንግዶች ተከብረውና በሥነስርዓት ተስተናግድው እንደሚለሱ ሳይረዳ እንደማይቀር ይገመታል።

አስተያየት ቢኖር ከላይ በተመለከተው ኢሜል አድራሻ ደራሲውን መድረስ ይቻላል።

Note: This and other church issues will be dealt with in great extent in the upcoming book: "Ethiopian Diaspora Religious Organizations in America"



ህሊና ያላቸው ሰዎች ህሊናቸውን የሚመግቡት ለሌሎች ቸርና ቅን በመሆን ነው። ለቤተሰቡ፣ ለጓደኞቹ እንዲሁም ለአካባቢውና ለአገሩ ቸር የሆነ ሰው ይወደዳል። ስለሆነም የራሱን ሕይወት አሳክቶ የሌሎችን ለማሳካት መልካም ህሊናና አስተሳሰብ ያለውን ወንድ ሴቶች እንደ ትኩስ ኬክ ይሻሙበታል።

ሐ. የችሎታ ብቃቶች

የማዳመጥ ችሎታ

የማዳመጥ ችሎታ ሴቶችን ለመማረክ፣ በሴቶች ለመፈቀር፣ ከሴቶች ጋር ለመኖር መሠረታዊ የሆነ ብቃት ነው። ሴቶች ጥያቄ ጠይቆ ተስተካክሎ ለሚያዳምጣቸው ወንድ ጥሩ ነጥብ ይሰጣሉ። ብዙ መናገር እንጂ ማዳመጥ የማይችሉ ወንዶች በምሉባት ዓለም ውስጥ አድማጭ ሆኖ መገኘት አንዱ የማራኪነት ምስጢር ነው። የማዳመጥ ችሎታ በመጀመሪያዎቹ የፍቅር ሳምንታት ላይ ብቻ መሆን የለበትም።

ይህ ችሎታ ስትናገር ማድመጥ ብቻ ሳይሆን የምትልህን ነገር በደንብ መስማት፣ ሃሳብዋን በደንብ መስማትና መተግበር ጭምር ማለት ነው። ደስ የሚለው ነገር ይህ ብቃትም በልምድ ልታዳብረው የምትችለው ነው።

ፍቅር የመግለፅ ችሎታ

ሴቶች ማራኪ ቃላትን ገጣጥሞ ፍቅሩን መግለፅ የሚችል ወንድ ይወዳሉ። ፍቅርህን ለመግለፅና ለማወደስ ጊዜ ስጥ። ስታልፍ ስታገድም "አወድሻለሁ፣ አፈቅርሻለሁ" ማለት ሳይሆን አሰበህ አቅደህ አሪፍ የፍቅር አጋጣሚዎችን (ሮማቲክ ጊዜያትን) እየፈጠርክ በጥሩ የፍቅር ቋንቋ ፍቅርህን የመግለፅ ልምድ አዳብር። የቻልከውን ያህል ግጥም በመፃፍም ይሁን ጥሩ ጥሩ ቃላት በመደርደር፣ በራስህ እጅ ፅሁፍ የፍቅር ማስታወሻ የመተው፣ አበባና ቾኮሌት የመስጠት፣ ወደ ሲኒማ ቤት የመውሰድ፣ ሮማንቲክ የሆነ እራት የመጋበዝ፣ የዘወትር ልምድ ሊኖርህ ይገባል። የፍቅረኛሞች ቀን፣ ልደቷና ሌሎች በዓላት ፍቅርህን ለመግለፅ ልትጠቀምባቸው የሚገቡ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው።

ፍቅር የመሰራት ችሎታ

ይሄ ነገር በጣም ትልቅ ነጥብ የሚያስጥ ችሎታ ስለሆነ ግልጥ ግልጥልጥ አድርገን እንነጋገርበት። ፍቅር የመሰራት ችሎታ ማለት እልጋ ላይ አሷን የማስደሰት ብቃትህ ማለት ነው። "ድርጊት ከቃላት በላይ ይናገራል" የሚባለው አባባል ትክክለኛ ቦታው አዚህ ላይ ነው። ለእሷ ያለህ ፍቅርና ታማኝነት የሚገለፀው ብቸኛ የአልጋህ ንግስት እንደሆነችና እንተም ብቸኛ የአልጋዋ ንጉስ መሆንህን በተደጋጋሚ ብቃትህ ስታሰመሰክር ነው።

ከአልጋው ዙፋን ሳትወርድ የምንጊዜም ንጉስዋ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብሃል።



በወሲብ ማንኙነታችሁ ዙሪያ በግልፅ የመነጋገር ልምድ እንዲኖር አድርግ። በወሲብ ዙሪያ ያላትን ማንኛውም ሰሜትና ሃሳብ በግልፅ እንድትነግርህ አበረታታት። ፍቅር በምትሰሩበት ጊዜ መጀመሪያ እሷ መደሰቷን መርካቷን እረጋግጥ።

በወሲብ ላይ ያለህን ዕውቀትና ችሎታ ለማሻሻል ሁሌም ዝግጁ ሁን። የወሲብ ችሎታና ዕውቀት የተለያዩ ጥናቶች፣ ፅሁፎችና መፅሐፎች በማንበብ እንደሚሻሻል አውቀህ ከማንበብ አትቆጠብ።

ቤት ውስጥ የመሰራት ችሎታ

ቤት ውስጥ ሪሞት ኮንትሮል ጨብጠህ ሶፋ ላይ ጉብ ብለህ ከህ አስከ ፕ ቻናሎችን እየለዋወጥህ የማየት ዝንባሌ ብቻ ካለህ ለባልነት የመታጨትህ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይገባል። አልጋ ከማንጠፋ ሻጂ እስከማፋላት የመሰሉ የቤት ውስጥ ስራዎች የመሰራት ፍላጎትና ዝንባሌ ሊኖርህ ይገባል። ሴቶች ትዳር ውስጥ ሲገቡ "ሁሉንም አትርቡልኝ" የሚል ትልት ህፃን ልጅ አንዲኖራቸው አይፈልጉም።

ጥሩ ገቢ የማግኘት ችሎታ

ጥሩ ገቢ ያለው፣ ጥሩ የተረጋጋና ሰላማዊ ሕይወት ይኖራል። የገቢ ማነስ ትዳርን ሊያደፈርስ ይችላል። ጥሩ ገቢ የማግኘት ችሎታ ከፍላጎት፣ ከቃታረነት፣ ከአውቀት፣ ከችሎታና ከራዕይ ጋር የተያያዘ ነው። የተሻለ ሕይወት የመኖር ፍላጎት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እውቀትን የማዳበር ልምድ፣ ራዕይን ለማሳካት ጠንክሮ የመሰራት ባህል ያለው ወንድ ስትዳር ተመራጭ ነው።

መ. የቁመና ብቃቶች

የአለባበስ ስታይል

"Dress To Impress" የሚለውን አባባል ‹አሳምረህ ልበስ፣ የሴትን ልብ ለማሳወሰው› በማለ ለመቀየር ይፈቀድልኛ። አለባበስ የሴቶችን ቀልብ ይማርካል። ሽክ ብለህ የለበስክ ቀን "ዋው! በጣም አምሮብሃል" የምትል ሴት አታጣም። ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ለፋሽንና ለስታይል ትኩረት ይሰጣሉ።

አሪፍ አለባበስና አሪፍ ስታይልን የሚረዳ ስድስተኛ የስሜት ሕዋስ ሳይኖራቸው አይቀርም። አሪፍ አለባበስ የሚለብስ ፍቅረኛ ያላት ሴት ኩራት ይሰማታል። በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ አብሯት እንዲገኝም ትጋብዘዋለች።

ማራኪ የፊት ገፅታ

የፊትህ ቅርፅ ምንም ይሁን ምን ጥራቱንና ውበቱን ከጠበቅክለት በቂ ነው። ሴቶች በስነ ስርዓቱ የተላጨና አስፈላጊውን እንክብካቤ የተደረገለት የፊት ገፅታ እንዲኖረን ይፈልጋሉ። ፂምህን ከላጨህ በኋላ እንደ አፍተር ሼቭና ኮሎኝ የመሳሰሉ ነገሮችን ተጠቀም። ፊቱን በሚገባ የማይንከባከብ ወንድ ሴቶች ዜሮ ነጥብ ይሰጡታል። ፊቱን ያልተንከባከበ ምንም ነገር ሊንከባከብ አይችልም ብለው ያስባሉ። ልክ ናቸው።

ቁመት

በተፈጥሮ ረጅም ከሆንክ እንኳን ደስ ያለህ። እንደኔ አጭር ከሆንክ ግን ከተፈጥሮ ጋር ግብግብ መግጠም የለብንም። ሴቶች በአውቀትና በልምምድ ልናዳብራቸው በምንችላቸው ብቃቶች ላይ እናተኩር። ደስ የሚለው ከዚህኛው በስተቀር አብዛኞቹ ተፈላጊ ብቃቶች ከተፈጥሮ ጋር ያልተያያዙ ለዳብሩ የሚችሉ ናቸው።

የግል ንጽሕና አጠባበቅ

"ሰዎችን የምንመግመው በውበታቸው ሳይሆን በመልካም መዓዛቸው ነው" ጄኒፈር ሎፔዝ

ከሰዎች ጋር አብሮ ለመስራትና አብሮ ለመኖር ንፅህና በማም ወሳኝ ብቻ ሳይሆን ግዴታ ነው። ወደ ፍቅር ሰንመጣ ደግሞ የበለጠ ይከራል። መደባበስ፣ መተቃቀፋ፣ መሳሳሙና አብሮ መተኛቱ ይመጣል። ስለዚህ ማራኪ መዓዛና ሳመኝ ሳመኝ የሚል ጠረን ሊኖር ይገባል።


ምንጊዜም የሚላስ ገላና የሚላም ከንፈር ይኑርህ። ይህ ማለት ደግሞ ቢያንስ በ24 ሰዓት ውስጥ አንድ ጊዜ ገላህን መታጠብ አለብህ። በ24 ሰዓት ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ አፍህን ማፅዳት (መቦረሽ) አለብህ። ዲዮደራንት፣ ንጹህ ልብስ መልበስና ሽቶ መቀባት የግል ንፅህና አጠባበቅ አካል ነው።

በስፖርት የዳበረ ስውነት

የእክል ብቃት እንቅስቃሴ በመስራት አካላዊ ቅርፅ መጠበቅ ለግል ጤንነት ከመጥቀሙ ባሻገር ሴቶችን የሚማርክ አንድ ራሱን የቻለ ብቃት ነው። ለጤና፣ ላማረ ቁመናህ የምትሰጠው ጊዜና ትኩረት በራሱ ጥሩ ነጥብ ያሰጥሃል።

ሌላውና ወሳኙ ነገር ደግሞ ፍቅረኛህ ልታቅፈው፣ ልትስመውና ልትንተራሰው የምትፈልገው ገላ አሪፍ እንዲሆን ትፈልጋለች። ባንተ ገላ ላይ አሷም ሼር አላት! "Six pack " የሚባለው የወንዶች የሆድ ቅርፅ ሴቶችን ከሚማርኩ የወንዶች አካላዊ ብቃቶች መካከል ነው። "Six Pack" ማድረግ ካታተህ ቢያንስ ቦርሜ አይኑርህ።

ክፍቅር ኪሚስትሪ



ቅዳሜ

በዚህ ዓምድ በ ዕለት ተለት የኑሮ ውጣ ውረድ ምክያንያታዊነታን ነገሮች በማንሳት አየተመቻቸሁን እንማማራለን። የማህበራዊ ኑሯቸን አካል የሆኑ የተለያዩ ጉዳዮች ይነሳሉ። የዚህ ዓምድ ጸሀፍ የጻሃፊው ቦግለ አቋም መሆኑ ይታወቅ።

በቴዎድሮስ ጎይሌ
dinqmagazine@gmail.com

ነገን ማን አለበ

ከአስታት አንድ ቀን ሰብሰብ ብለው ይጌዱ የነበሩ ወንደች አንድ ክረጪት ጥራጥሬዎችን ይዘው ይጓዙ ነበር። አንዱም አንዲህ አለ። "ከአናንተ ጋር መሄድ አልፈልግም። አንድ ፍሬ በቶሎ ሰጡኝና ቶጆችሁ ልሂድ።"

ሌላኛውም "ምን ሆነሃል? ለምንድነው አብረን የማንሄደው? በቶሎውን ተካፍለን ምግባችንን ቢጋራ አያበሰልን እንካፈላለን። አንድ ፍሬ በቶሎ ብትወስድ ምንም አያደርግልህም።" አለው።

ሰውየውም "ይህ አንተን እይመለከትህም። አንጂን ፍሬ በቶሎ ብቻ ነው የምፈልገው።" ብሎ መለሰለት። ወጣቶቹም ሰዎች ተመካክረው "አንድ ፍሬ በቶሎ ለእኛ ምንም ማለት አይደለም አንስጠው።" ተባባሉ።

ሰዮተውትም ሲሄድ በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ የበቶሎ ምግም ታዚጋጅ የነበረች ሴት አግኝቶ አንዲቷን ፍሬ በቶሎ ማሰሮዋ ውስጥ ወርውሮ "ለእራት እመጣለሁ።" ብሎ ሄደ።

እንግዳውን ሰው በመገረም ተመልክቶው ዝም አለች። የዚያን አለት ምሽት የእራት ሰአት እስኪያልፍ ጠብቶ ወደቤቱ ተመለሰ። ሁሉም ሰዎች ምግባቸውን በልተው ጨርሰው ነበርና አንዲህ አሉት "ምግቡን ከጨረስን በኋላ በመምጣትህ እናዝናለን። ከእኛ ጋር ትመገብ ነበር።"

አሱም አንዲት የበቶሎ ፍሬ ይዞ መምጣቱንና ነገር ግን ሴትየዋ በቶሎውን ስትፈጭ እንዲቷ ፍሬ የት እንደገባች አለማወቋን ነገራቸው። ከዚያም ጠንከርና በስጨት ብሎ "ወይ ምግቤን ሰጡኝ አለበለዚያ ማሰሮውን ልውሰድ።" አላቸው።

አነአርሱም "እንዴት ያለው አብድ ሰው ገጠመን?" ብለው "እንግዲህ፣ ምግቡ ስላለቀ ምንም ልንሰጥህ አንችልም። ባይሆን እንካ ማሰር" ብለው ሰጡት።

ማሰሮውን ይዞ ወደውንዝ በመውረድ ውሃ ከሞላ በኋላ የፍየሎች መንጋ ሲመጣ ተመልክቶ መንገዳቸው ላይ ማሰሮውን ስላስቀመጠው ፍየሎቹ ውሃውን ስመጠጣት ሲሻሙ ማሰሮውን ሰበሩት።

በዚህ ግዜ የፍየሎቹን ባለቤት ጠርቶ "ተመልከት! ፍየሎችህ ማሰሮዬን ሰብረውብኛል። ወይ ማሰሮዬን ሰጠኝ አለበለዚያ አንዲቷን ፍየል እወስዳለው።" አለው።

የፍየሎቹም ባለቤት "ችግር የለም። ሌላ ማሰር አሰጥሃለው" አለው። ሰውየው "የራሴን ማሰር እንጂ ሌላ አልፈልግም።" አለ። የፍየሎቹም ባለቤት የተሰበረውን ማሰር መጠገን ስለማይችል ላይወድ በግዱ አንድ ፍየል ሰጠው።

ሰውየውም ፍየሏን ወስዶ በመሄድ ላይ አያለ ምሳቹውን በልተውና ጠግበው በመፈንጨት እየተመለሱ ያሉ ግመሎችን ሲመለከት ፍየሏን መንገዳቸው ላይ በማሰር ጨፈላልቀው እንዲገድሏት አደረገ። ከዚያም የግመሎቹን ጠባቂ አስቁሞ "ተመልከት ፍየሌን ገድለሁብኛል። ወይ ፍየሏን ወደ ህይወት መልስልኝ አለበለዚያ አንድ ግመል ትሰጠኛለህ" አለው።

አረኛውም "ይህ የማይቻል ነው። ፍየሏን አንዴት ነው ወደ ህይወት የምመልሳት? ሌላ ፍየል ፈልጌ አሰጥሃለው" አለው። ሰውየውም "አይሆንም ፍየሌን ወይንም ግመል" አለው። ፍየሏ ስለሞተች አረኛው አንድ ግመል ለመስጠጥ ተገደደ።

ሰውየውም ግመሉን ይዞ በመሄድ ላይ ሳለ የጓደኛው የቀብር ስነ ስርአት ላይ ይደርሳል። "አስኪ አንድ ግዜ ቀፎኝ። የዚህን ሰው አስክሬን አፈልገዋለው። በግመል ለውጡኝ።" አላቸው።

ሰዎቹም ሰብሰብ ብለው አስክሬኑ ዋጋ አንደሌለውና ግመሉ አንደሚጠቅማቸው መክረው ሲያበቁ አስክሬኑን በግመል ለወጡት።

ቀኑ አየመሸ ባለበት ሰአት ወደ አንዲት ትንሽ መንደር ሄዶ ሰዎች ተቀምጠው አየበሉ ያያቸውና "ጤና ይስጥልኝ። መንገደኞች ነን። ሰለመሸብን ጓደኛዬን አዘሀኛው ቤት፣ እኔ ደግሞ የሚተዋለው ጎጆ ውስጥ አንደር።" ብሎ ጠየቃቸው። ከዚያም አስክሬኑን ወንበር ላይ አስቀመጠው። ሰዎቹም የሞተ ሰው አልመሰላቸውም። ወደ ውጪ በመውጣት ላይ አያለ አስክሬኑን በጦር ወግቶት ወደ አጎራባች ቤት ሄደ። በአፋር ባህል መሰረት ምግብ የሚፈልግ ሰው አንደ አንግዳ ሰለሚጋበዝ አራቱን ሰጡት። አራቱን አየበላ ሳለም ከሚተዋለው ጎጆ የጩኸት ድምፅ ሰማ። "ጓደኛዬን አዚያ ነው የተውኩት። ሄደን አንየው።" አላቸው። ወደሚተዋለው ጎጆም አየሮጡ ሲሄዱ አጎራባች ያሉት ሰዎች አስክሬኑ በጦር ተወግቶ አገኙት።

በዚህ ግዜ ጓደኛዬን ገደሉብኝ አያለ መጮህ ጀመረ። ብዋብጥና ጩህትም ስለበረከተ ጎረቤቶቹ ጓደኛውን አንደገደሉበት ተወሰኑ። በዚህም ካሣ ሊሰጡው ይገባል። የአንድ ሰው ካሣ ደግሞ 100 ግመሎች ወይም 400 ከብቶች ነው። ሰውየውም ግማሹን በግመሎችና ግማሹን ደግሞ በከብቶች ተከፍሎት ሃብታም ሰው ሆነ።

ሁለት ሚስቶችንም አግብቶ ከአንደኛዋ አራት ልጆችን ከሁለተኛዋ ሚስቱ ደግሞ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ወለደ። ከዚያም ስብዙ አመታት በደስታ ኖሮ ሞተ። ሲሞት አስክሬኑ በግመል ጀርባ ላይ ተጭኖ ወደ መቃብር ቦታው አንዲወሰድ ተናዘ ሰለነበር በግመል ጭነው አየወሰዱት ሣለ ግመሉ ደንብሮ መሮጥ ሰለጀመረ ግራ ገባቸው። ልጆቹም አስክሬኑ ካልተቀበረ በውርስ ላይ ችግር አንደሚገጥማቸው ያውቃሉ።

ከዚያም አራቱ የመጀመሪያዋ ሚስት ልጆች አንዲህ ብለው አሰቡ "ወንድማችንን ለምን አንገድለውም? ከዚያም የሚቀበር አስክሬን ስለሚኖረንና ሁሉም ነገር የእኛ ብቻ ስለሚሆን በውርስ ላይ ችግር አይኖርብንም።"

ስለዚህ ወንድማቸውን ገድለው ወደ መቃብር ቦታው ወሰደው በመቅበር ላይ ሳሉ የአባታቸውን አስክሬን ይዞ የጠፋው ግመል አስክሬኑን ይዞ ተመልሶ መጣ።

ነገር ግን የአባትየው አስክሬን ሙሉ ለሙሉ ተበጣጥሶ ስላለቀ ግመሉ ጀርባ ላይ የቀረው ጭንቅላቱ ብቻ ነበር። ሰዎቹም ግመሉን አቁመው ሲመለከቱ አየቀበሩ ያሉት የመሰላቸውን ሰው ጭንቅላት ተመለከቱ። አናም አንዲህ አሉ "ለምን? ይህ አየተበርነው ያለው ሰው ጭንቅላት አይደለም?" ተባባሉ፣ አስክሬኑንም ፈተው ሲመለከቱ የልጂ አስክሬን መሆኑን ደረሱበት። በዚህም ምክንያት የመጀመሪያዋ ሚስት ቤተሰቦች በሙሉ ከሁለተኛዋ ሚስት ቤተሰብ ጋር ጦርነት ከፍተው አርስ በአርስ ተጨራረሱ።

ዛሬ የምናደርጋት አያንዳንዷ ነገር፣ ከዛሬ ሰሜታዊነትና ግንፍልነት አልፋ፣ ነገ በአገር ላይ ፣ ነገ በቤተሰብ ላይ፣ ነገ በልጆቻችን ላይ ፣ ነገ በማህበረሰብ ላይ ፣ ነገ በቤተክርስቲያን/በመስጊድ ላይ፣ ነገ በሚመጣው ትውልድ ላይ የሚያመጣውን ጣጣ ልናስብና ድርጊታችንን በነገም ዓይን ልንቃኘው ግድ ነው።

ዛሬ የተመቸን አና በድርጊታችን ደስ ያለን ልንሆን አንችላለን - የነገውን ጣጣ ማሰብ ካልቻልን ግን ራስ መዳደች ነን። በራስ መዳድነት ደግሞ ዓለም ውደቱን ሊቀጥል አይችልም። ዛሬ ተንኮልና አባችን ፣ ስድብና ዛቻችን፣ ቅናትና ምቀኝነታችን ለለተመቸን ብቻ፣ ነገ የሚያመጣውን ላለማሰብ አለምሯችንን አንዘጋ!

_____//_____

-ፍልስፍና-



ስለ ሃሜት ፍልስፍና

ሰዎች ስለ ሌሎች ሲያወሩ የሐሜት ተግባር ሰሩ ማለት እንደሆነ እንገንዘብ። ጓደኛህ መጥፎ ነገር እንዳስወራብህ ስማህ እንበል። የተፈጠረውን ነገር ችላ ብለህ ማለፍ ትችላለህን? ፤ወደ ጓደኛህ ቀርበህ በተረጋጋ መንፈስ ስለ ሁኔታው ልታነጋግረው ትችላለህን?፤አንተም በዚህ ጓደኛህ ላይ ልታስወራበት የምትችለው ነገር አለን? በጓደኛህ ላይ ባለማስወራትህስ አሱን ከመበቀል መቆጠብ ትችላለህን?

ከላይ ላሉት ጥያቄዎች "ትንሽ ይከብዳል" ወይም "በጭራሽ!" የሚል መልስ ከሰጠህ፤ ሌሎች ስለ አንተ ሲያወሩብህ ሁኔታውን በተሻለ መንገድ መያዝ የምትችልበትን መንገድ ይጠቁምሃል።

አንዳንድ ጊዜ ሐሜት ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፤ ለምሳሌ ያህል፣ አንዳንዶች ሆን ብለው ውሸት በመናገር ስምህን ለማጥፋት ይሞክሩ ይሆናል። ይሁን እንጂ የተወራብህ ነገር ያን ያህል መጥፎ ላይሆንም እንኳ ስሜትህን ሊጎዳው ይችላል፤ በተለይም ግለሰቡ የቅርብህ ሰው ከሆነ ልትጎዳ ትችላለህ።

እውነታው፦ ሐሜቱን ያሰራጨው ሰው የቅርብ ጓደኛህ ሆነም አልሆነ ስለ አንተ መጥፎ ወሬ መወራቱን ስትሰማ እንደማትደሰት የታወቀ ነው። ሰዎች ስለ ሌሎች እንዲያወሩ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው አርስ በርሳቸው መጨዋወት ይወዳሉ። በመሆኑም ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ማውራታችን የተለመደ ነገር ነው። "ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ስለ ሌሎች ሰዎች ማውራት ያስደስታቸዋል!"

"ስለ ሌሎች ሰዎች ማወቅ እና ስለ እነሱ ማውራት እንደሚያስደስተን አልክድም። ለምን እንደሆነ ባለውቅም ደስ ይለኛል።"የሚሉ ሰዎች በርካቶች ናቸው።

ሥራ መፍታት፦ በጥንት ዘመን የነበሩ አንዳንድ ሰዎች "ትርፋ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስለ አዳዲስ ነገሮች በማውራትና በመስማት ብቻ" እንደነበረ ይናገራል። ዛሬም ቢሆን ሁኔታው ተመሳሳይ ነው።

"አንዳንድ ጊዜ ሰዎች፣ በዙሪያቸው አዲስ ነገር ካልተፈጠረ ወሬ ፈጥረው ስለ ሌሎች ያወራሉ።"

በራስ አለመተማመን፦ ራሳችንን ከሌሎች ጋር እንዳናወዳድር መጠንቀቁ ተገቢ ነው። የሚያሳዝነው፣ አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው ስለማይተማመኑና ስራሳቸው ያላቸው ግምት ከፍ እንደሚል ስለሚሰማቸው ሌሎችን ያማሉ።ይህ ከባድ የስነልቦና ችግር ነው።

"አንድ ሰው ሐሜተኛ መሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ስለ እሱ የሚያሳየው ነገር አለ። ብዙውን ጊዜ ይህ ሰው የሚያማውን ግለሰብ እንደሚቀናበት ይጠቁማል። ሐሜተኛ ሰዎች አሉባልታ የሚያሰራጩት ስለ ራሳቸው ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ነው፤ በሌላ አባባል እንዲህ በማድረግ ከዚያ ግለሰብ የተሻሉ እንደሆኑ ራሳቸውን ያሳምናሉ።"

እውነታው፦ ወይድክም ጠላህ ሰዎች ስለ ሰዎች ማውራታቸው አይቀርም፤ ይህ ደግሞ አንተንም ይጨምራል።ታዲያ ምን ይሻላል? ሰዎች ጨርሶ ስለ አንተ እንዳያወሩ ማድረግ አትችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ለዚህ የምትሰጠው ምላሽ በአንተ ላይ የተመካ ነው። ስለ አንተ እየተወራ እንደሆነ ካወቅህ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ማድረግ ትችላለህ።

እማራጭ 1፦ ችላ ብሎ ማለፍ። አብዛኛውን ጊዜ የተሻለው እማራጭ ችላ ብሎ ማለፍ ነው፤ በተለይም የተወራው ነገር ያን ያህል ከባድ ካልሆነ እንዲህ ማድረጉ የተሻለ ነው። "ሐሜትን ለመዋጋት ከሁሉ የተሻለው መሣሪያ ጥሩ ስም ማትረፍ ነው። ጥሩ ስም ካለህ፣ መጥፎ ነገር ቢወራብህ እንኳ ወሬውን ብዙ ሰው አያምነውም። እውነት ማሸነፉ አይቀርምና።"

ጠቃሚ ምክር፦ ስለ አንተ የተወራውን ነገር እና ወሬው ምን ስሜት እንደፈጠረብህ አስብ። ሁኔታውን 'በልብህ ካሰብክበት' በኋላ ችላ ብሎ ማለፍ ቀላል ሊሆንልህ ይችላል።

እማራጭ 2፦ ወሬውን ያስወራብህን ሰው ቀርበህ እነጋገረው። እንዳንድ ጊዜ፣ ወሬው በጣም ጎጂ ከመሆኑ የተነሳ ያስወራብህን ሰው ማነጋገር ሊያስፈልግህ ይችላል።

"መጥፎ ነገር ያስወሩብህን ሰዎች ቀርበህ ካነጋገርካቸው፣ ሐሜት ዞሮ ዞሮ ባለቤቱ ጀርመ መድረሱ እንደማይቀር አያስተማርካቸው ነው። በተጨማሪም በመካከላችሁ የተፈጠረውን ችግር መፍታትና ሐሜቱን ካሰራጨው ግለሰብ ጋር ያለህን ግንኙነት ማደስ ትችል ይሆናል።"

መጥፎ ነገር ያስወራብህን ሰው ቀርበህ ከማነጋገርህ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ።

... 'ስለ ጉዳዩ የተሟላ መረጃ አለኝ? መጥፎ ነገር እንደተወራብኝ የነገረኝ ሰው፣ የሰማውን ነገር በተሳሳተ መንገድ ተረድቶት ይሆን?'

... 'መጥፎ ነገር ያስወራብኝን ሰው ለማነጋገር ጊዜው አመቺ ነው? ስለ ጉዳዩ ስሜታዊ ሳልሆን መናገር እችላለሁ? ወይስ ስሜቴ አስኪረጋጋ ድረስ ጥቂት ጊዜ መጠበቅ ይኖርብኛል?'

'ሐሜቱን ያሰራጨሁት ሰኔ ብሆን ኖሮ ባለቤቱ እንደት ቢያነጋግረኝ ደስ ይለኛል? ስለ ጉዳዩ ያት ቢያናግረኝ አመርማለሁ? የተሻለ ውጤት የሚያስገኘው የትኛውን ቃላት ወይም ምን ዓይነት አቀራረብ መጠቀም ነው?'

ጠቃሚ ምክር፦ በሕይወትህ ውስጥ ከሚያጋጥሙና ሁልጊዜ ልትቆጣጠራቸው ከማትችላቸው ነገሮች አንዱ ሐሜት ነው። ይሁን እንጂ እንተን እንዳይቆጣጠርህ ማድረግ ትችላለህ።

StateFarm

Jerome B Johnson, Sr.
Agent

3101 Clairmont Road NE, Suite B
Atlanta, GA 30329-1044
Bus 404 321 6688
Fax 404 477 0299
www.jeromebjohnson.com
jerome.johnson.glqk@statefarm.com

The greatest compliment you can give is a referral.

ከዕለታት አንዱ ቀን

ONCE UPON A TIME

መብላት ያስለመድከው ሲያይህ ያዛጋል

ከዕለታት አንድ ቀን የዱር አራዊት ንጉሥ የሆነው አያ አንበሶ በጉልበት በማን አለብኝና በገዢነት ስሜቱ መዋጡን ትቶ፣ ከሁሉም አራዊት ጋር አብሮ መኖርና ተጋግዞ በጋራ ፋሬ ማፍራትን በመፈለጉ፣ የዱሮው አያ አንበሶ መሆኑን ለመተው ማሰቡን ይፋ ለማድረግ አሻ።

ስለሆነም ዋና መርሆው፡- "ከሌሎች የዱር አንሰሳት ጋር ተባብሮ መኖር ነው!" አለ

ይህንኑ በተግባር ለመተርጉም አያ ጅቦ ጋ ሄደና፤ "አያ ጅቦ የውትር ጠብና የገዢና ተገዢ ነገር ያብቃና በጋራ ተሳስበን እንኑር ብዬ አስቤያለሁ"፤

"መልካም ሀሳብ ነው። ደስ ብሎኛል" አለ።

አያ አንበሶ ቀጥሎ ወደ አያ ነብሮ ሄደና፤ "አያ ነብር፤ የወትር ጠብና የገዢና ተገዢ ነገር ያብቃና በጋራ ተሳስበን የምንኖርበት ሥርዓት እንፍጠር" አለው።

አያ ነብር፤ "እጅግ ቀና ሃሳብ ነው - ይህን የተቀደሰ ሃሳብ ማን እምቢ ይላል?" አለና መለሰ።

ቀጥሎ ተኩላ ጋ ሄደ። ተባብሮ አብሮ የመሥራትን ሥርዓት ጉዳይ አነሳበት።

ተኩላ፤ "ይሄማ አሰየው ነው። ምን ሆኜ እታወመዋለሁ?" አለ።

የሦስቱም መልስ እጅግ ያስደስተዋል።

"እንግዲያው የተስማማንበትን በታማር ማየት አለብን" አለ ተኩላ። ተስማሙና ታላቁ አደን ላይ ተሰማሩ። ሄደው ሄደው አርፋደው ትልቅ ጉሽ ሬቃቸው ድቅን አለ፤ ተረባረቡና ጉሹን መሬት ላይ ጣሉት። ከዚያ ተካፍሎው ድርሻ ድርሻቸውን መውሰድ ነበረባቸው። አሁን ጉድ ፈላ ፡ አንበሳ ዋና ደልዳይና አከፋፋይ ሆነ። አራቱም የምግብ አጠቃቀም ዘዬአቸው የተለያየ ነው። አብረው መብላት የማይታሰብ ነው። አያ አንበሶ፤ "መብላት አለብን፤ ተካፍለን እንመገብ" አለ።

ሌሎቹ ልባቸው ባያምንበትም "በጀ" አሉ። አንበሳ የጉሹን ሥጋ አራት ላይ ከፈለው።

የመጀመሪያውን የቅርጫ መደብ፤ "ይሄ መደብ የአኔ ነው። የአራዊት ንጉሥ በመሆኔ የማገኘው ድርሻዬ ነው"

ቀጠለና፤ "ሁለተኛውን መደብ የሚያገኘው አደኑ ላይ ትልቅ ሚና የተጫወተው ነው ያ ደግሞ እኔ ራሴ ነኝ።"

"ሦስተኛው መደብ፤ እኔ ራሴ በአንበሳነቱ ልክ እንደናንተው ድርሻዬ ነው" አለ።

አያ አንበሶ፤ አራተኛውን ቅርጫ ወደ ወለሉ ገፋና "ይሄን የቅርጫ መደብ የሚነካ ወዮለት!" አለ።

ዕቃ ስላማን አብረን በላን ፣ አንጂ መች አኩያ ነን?

በድሮው ዘመን አንድ አዛውንት አሰር ቤት ይገባሉ። በዚያን ጊዜ አሰረኞች አራሳቸው ባወጡት ህግ መሰረት፤ አዲስ ገቢ ሲመጣ ለአሰር ቤቱ መኖሪያ ማዋጣት ያለበት ገንዘብ ነበር። የአሰር ቤቱ የህዝብ ግንኙነት፤ "እንግዲህ በክሩላችን ህግ መሰረት ያቅምዎትን አዋጡ" አላቸው አዛውንቱም፤ "ቤተሰቤ ምን ይሰጠኝ ምን ሳላውቅ ይሄን ያህል አዋጣለሁ ማለት ያስቸግረኛል" አሉ።

"ግዴለም ከመጣልዎት ውስጥ ይሄን ያህሉን አለግሳለሁ፤ ቢሉና ቃል ቢገቡ እንኳ በቂ ነው" አሳቸው።

ይሄኔ አዛውንቱ፤ "እስቲ አሳቤን በውግ ልግሰጥ" አሉና፤ "ጥንት ጎጃም ውስጥ ሁለት ሴቶች ሜዳ ሊውጡ ከቤት ወደ ደጅ ይሄዳሉ። ቅዳሜ ለአሁድ አጥቢያ ሚታ ነው።

አንደኛዋ፤ ‹አንግዲህ እደራ፣ ነገ በተስኪያን ጠዋት ስንመጣ፣ አንቺ ከቀደምሽ አንቺ፤ እኔ ከቀደምኩ እኔ፤ ቀድመን ቦታ እንያዝ - አሌቶች መቆሚያ ቦታ› አለቻት።

በተስኪያን ውስጥ ማልደ መጥቶ ቦታ ካልያዙ ሰው ብዙ ስለሆነ ደጅ ሆኖ ማስቀደስ ግድ ስለሚሆን ቀድሞ መገኘት ዋና ነገር ነው። ይሄኔ፤ ሁለተኛይቱ ሴት፣ በሚያቅማማ ድምፅ፤ "እንግዲህ ማልዶ ቦታ ለመያዙም፣ በተስኪያን ውስጥ ገብቶ ለማስቀደሱም፤ ወንዶቹ እንዴት እንዳሳደሩን አይቶን ነዋ!" አለች።

(በዕምነቶቹ መሰረት ከወንድ ተገናኝታ ያደረች ሴት፤ በተስኪያን ውስጥ መግባት ክልክል በመሆኑ ነው። ያ ደግሞ በድርው ዘመን በተለይ የወንዱን ፍቃድና ፍላጎት የሚሻ ጉዳይ ነው!)

1 ጥያቄ አለኝ

(ይህ ዓምድ መታሰቢያነቱ ለጳውሎስ ኞኞ ይሁን)

(አዘጋጅ— ዞብል ዘ ጨርቆስ)

ስምህ ማነው? = ጊታ ያውቀዋል

የምትወደው የወንድ ስም? = በእንጽኪያ ክርስቲያን ትባላላችሁ ተብሏል፤ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ወንድሜ ነው ...

የምትጠላው የወንድ ስም? = ምግባር አንጂ ስም አይጠላም ....

የምትወደው የሴት ስም? = ማርታ .. ጌታን ቤታ ተቀብላ በማስተናገዷ

የምትጠላው የሴት ስም? = በጌታ ስም ጥላቻ ከውስጤ ጸውጣ !!

ከመፈክር የምትወደው? = "እየሱስ ጌታ ነው!"

ከምግብ የምትወደው? = የተባረከ ምግብ ሁሉ

ከምግብ የምትጠላው? = ጌታ የፈጠረው ሁሉ ጎሹህ ነው ....

አንሰሳ ብትሆን ምን መሆን ይሻልሃል? = አህያ—ጌታ ስለተቀመጠበት

ከሞት አስነሳ ብትባል? = ከሞት ማስነሳት የፈጣሪ ሥራ ነው።

በህይወትህ ከሚቀጪህ ነገሮች? = ጌታን ሳላውቅ የኖርኩባቸው ዓመታት

ከሴት አካል የምትወደው? = በፈጣሪ አምሳል ስለተፈጠረች እንኳን የለባትም .....

ለአንድ ቀን የኢትዮጵያ መሪ ብትሆን? = የምችለውን ያህል ወንጌል አስፋፋለሁ .....

ለአንድ ቀን የዓለም መሪ ብትሆን? = ክርስቶስን ለማያውቁ ሁሉ ለአንድ ቀን አንዲሰበክላቸው አደርግ ነበር .....

መንግስቱ ኃይለማርያምን ድንገት መንገድ ላይ ብታገኘው? = የመዳን ቀን ዛሬ መሆኑን አንግረውና ጥፋቱን ተናዝ ንስሃ አንዲገባ አደርገው ነበር ...

ከዚፈን ? = "ዘፋኞች የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም"

ከመጽሙር? = ጌታን የሚያመሰግን ሁሉ .....

ከቤት ውስጥ ሥራ የምትጠላው? = አልችልም አንጂ የምጠላው የለም

ነገ ትሞታለህ ብትባል? = ደስ ይለኛል፣ ከጌታ ጋር ስለሆንኩ አልፈራም።

ስምሽ ማነው? = ቲቲ

የምትወጂው የወንድ ስም? = ዮኒ

የምትጠይው የወንድ ስም? = ረዣዥም ስም አልወድም . በተለይ ገብረምናምን አይነቶች አይመቹኝም ....

የምትወጂው የሴት ስም? = ሔዋን ፡ የመጀመሪያዋ ሴት ስለሆነች

የምትጠይው የሴት ስም? = ጓደኛዬ ትገስኛለች . ይቅርብኝ ....

ከመፈክር የምትወጂው? = "ለውን ማመን ቀብሮ ነው"

ከምግብ የምትወጂው? = ኪክ

ከምግብ የምትጠይው? = ጎመን .. ጥርሴ ላይ እየተለጠፈ ስለሚያስቸግረኝ ....

እንሰሳ ብትሆኝ ምን መሆን ይሻልሻል? = አንጄ፤ ዮኒ ግን (ዩኔፍሬንዲ ነው) ነብር ነሽ ይለኛል ... መኝታ ላይ ሃይለኛ ነኝ መስለኝ ... ሎል

ከሞት አስነሺ ብትባይ? = መስሰ ዜናዊን .. አሁን ያሉው መሪ አይመቹኝም .....

በህይወትሽ ከሚቀጪሽ ነገሮች? = አባቴን ሳልጠግበው መሞቴ ....

ከወንድ አካል የምትወጂው? = እንትኑን .. ቂቂቂቂ .. መዋሸት የለብኝም አይደል? ..

ለአንድ ቀን የኢትዮጵያ መሪ ብትሆኝ? = መብራትና ውሃ እንዳይጠፋ አደርጋለሁ ፣ .....

ለአንድ ቀን የዓለም መሪ ብትሆኚ? = ውይ ይቅርብኝ.. ከስንቱ ጋር ተዳርቄ እችላለሁ ...

መንግስቱ ኃይለማርያምን ድንገት መንገድ ላይ ብታገኚው? = ማነው መንግስቱ?

ከዘፈን ? = ወዛመይ ዳሚት ነጋ ...

ከመዝሙር? = የዘርፈ .....

ከቤት ውስጥ ሥራ የምትጠይው? = አልጋ ማንጠፍ .. ሚሚ ትሙት አልጋዬ ተነጥፎ አያውቅም .....

ነገ ትሞቻለሽ ብትባይ? = ምን አረኩህ አንተ ?

-የወሩ እንግዳ-

ፊደል ካስትሮ ሩዝ

ኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ አራተኛውን የአብዮት በዓሏን መስከረም 2 ቀን 1971 ዓ.ም. ለማክበር የመዲናይቱ ነዋሪዎች ከመሪዋ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ አብዮት አደባባይ ከትመዋል። ርእሰ ብሔሩ ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዕለቱን የክብር እንግዳቸውና ቁርጠኛ ወዳጃቸው የወቅቱ የኩባ ፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮ ሩዝን ሊቀበሉ በዳግማዊ ምኒልክ ጎዳና ቢታላቅ አጀብ ቦሌ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ደርሰው ይጠብቁ ነበር። ፊደል ካስትሮን የያዘው አይሮፕላን ግን ድምፁ አልተሰማም።

ፕሬዚዳንቱ በመዘግየታቸው ሊቀመንበሩ ወደ አብዮት አደባባይ ተመለሱ በአደባባዩም የሦስቱን ዓመታት «ትግልና ድል»



የሚዘክር መሰናዶ እያዩ አዲስ በታነፀው ሰገነት ላይ ሆነው ይከታተሉ ጀመር።

አብዮታዊ ዲስኩራቸውን እያሰሙ ባሉበት ሰገነት ላይ አንዱ ተጠግተቸው ፊደል ካስትሮ አዲስ አበባ መድረሳቸውን ነገሩቸውና ንግግራቸው አቋርጠው ሊቀበሏቸው ቦሌ ዘለቁ። አቀባበልም ተደረገላቸው። ከቦሌ እስከ አብዮት አደባባይ ግራና ቀኝ የተሰለፉት በተለይ የከፍተኛ 18 እና ከፍተኛ 19 ነዋሪዎች አጀቡን አደመቁት። «ቪቫ መንግሥቱ ቪቫ ካስትሮ» እየተባሉ በቅብብሎሽ ከአደባባዩ ደረሱ። ዘውዳዊ ምልክቱ በመዶሻና ማጭድ በተተካው በቀዩና ግልጽ ማርቸዲስ አውቶሞቢል ቢሆንም አደባባዩን ዞሩ። ይህ ከሆነ ድፍን 38 ዓመት ሆነው።

የኢትዮጵያ ቁርጠኛ ወዳጅ፣ ከ40 ዓመት በፊት ወረራ የፈጸመችባትን ሶማሊያ ለመግታት ከ15 ሺሕ በላይ ወታደሮቿን አሰልፋ ከደም ጠብታ እስከ መስዋዕትነት የተሰለፈችው ኩባ መሪዋ ፊደል ካስትሮ ከ40 ዓመት በፊትም በ«ቀውጢው ዘመን» አዲስ አበባ ጎራ ብለው ነበር። መጋቢት 5 ቀን 1969 ዓ.ም. በወቅቱ አጠራር በኢምፔሪያሊስቶችና በአድኅሮት ያረብ አገሮች አጋፋሪነት ምሥራቅ ኢትዮጵያን ወርራ የያዘችውን የዚያድ ባሬ ሶማሊያን ሃይ ለማለት መትጋታቸው አልቀረም። የሁለቱ አገሮች ጦርነት የቀዝቃዛው ጦርነት አካል የሶቪየት ኅብረትና የአሜሪካ፣ የሶሻሊስቱና የካፒታሊስቱ ዓለም ጎራ ዐውደ ውጊያ ሆኖ የታየበት ነበር።

እስከ አፍንጫዋ ታጥቃ የነበረችው የምዕራቡና የዓረቡ ዓለም ድጋፍ የነበራት ሶማሊያ፣ ከአሜሪካ ጦር መሣሪያ በገንዘቧ ገዝታ «ዓይንሽን ላፈር» የተባለችውን ኢትዮጵያን እስከ 700 ኪሎ ሜትር ድረስ ድንበር ጥሳ ወሰን አፍርሳ ሕዝብ አፈናቀለች።

የፊደል ካስትሮና የኢትዮጵያ ሌላኛዋ ወዳጅ የደቡብ የመን (የመን ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ) ሶሻሊስት ፓርቲ መሪው አብዱልፈታህ እስማኤል ጭምር የተደረገው የማደራደር ጥረት አልተሳካም።

ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም «ትግላችን» ባሉት የመጀመሪያው መጽሐፋቸው እንደጻፉት፣ የፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮና የፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ እስማኤል የእደን ሽምግልና ሳይሳካ ቀረ።

«ጓድ ፊደል ሲቀበሉን ጦርነቱን ገጥመን፣ የተሸነፍን ይመስል በማዘንና በመጨነቅ ሊያፅናኑን ሞከሩ። ሶማሊያዎች ውጊያውን ሊያሸንፉ ይችላሉ። በጦርነቱ አሸናፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው በማለት እኛ መልሰን አፅናናናቸው።»

ሊቀመንበር መንግሥቱ የካስትሮ ምላሽንም በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። «ልክ ናችሁ በጦርነት አሸናፊው አብዮት ነው። እኛ የጠላነው፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መሸነፋችንን በመገመት ነው።»

ጦርነቱ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ጎን በአጋርነት የተሰለፉት የኩባና የደቡብ የመን ጭምር መሆኑ ነው። እስፍ ሲልም የምዕራቡና የምሥራቁ ዓለም የአንድ ክንፍ ፍልሚያ።

«ተነሥ ታጠቅ ዝመት አብዮታዊት እናት አገርህ ተደፍራለች» በሚለው «ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት» ዘመቻ፣ የኩባም የየመንም ወታደሮች ታከሉበት። በፍልሚያው ጎራ በምሥራቅና በደቡባዊ ምሥራቅ የዘመቱት አርመኛ ወታደሮች ለአገር ነፃነት ተሰዉ። የነዚያ ጀግና ወታደሮች ልጆችም የፊደል ካስትሮዋ ኩባ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ሰጠች። በጦሳኑ የጦር ግንባር «ቶሬ» እና በ«መንግሥቱ ኃ/ማርያም» ስም ትምህርት ቤቶችንም መሠረተች

«ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼጉቬራ» እያለ ያቀነቀነው ያ ትውልድ ፊደል ካስትሮም ታክዩ ነው። የኢትዮጵያ አብዮት በተቀጣጠለበት የሶሻሊስት ርዕዮት የሚያንፀባርቁ መጻሕፍት በየፈርጁ በተተረጐመበት ጊዜ አንዱ የኩባ አብዮት ታሪክ ነበር። የአዲስ አበባን ገበያንም ይዞት ነበር።

አራተኛው አብዮት በዓል በሶማሊያ ላይ ከተገኘው ድል በኋላ የተከበረ በመሆኑ ልዩ ስፍራ ነበረው። ከ1968 እስከ 1970፣ እንዲሁም ከ1972 እስከ 1983 የአብዮት በዓል መስከረም 2 ብቻ ነበር። ፊደል ካስትሮ የተገኙበት የ1971 ዓ.ም. የአብዮት በዓል ግን በመስከረም 2 ብቻ አልተገደበም። በማግስቱ መስከረም 3 ቀን በወታደራዊ ሰልፍ መከበሩ ይታወሳል። «ትግል ድል» የተሰኘው ታላቅ ዐውደ ርዕይም በሸዋ ሜዳ አሜሪካ ኢምባሲ ፊት ለፊት የአሁኑ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ ተቋም ቅጥር ግቢ ሲታይ ፊደል አካሉ ነበሩ። ኩባ ለኢትዮጵያ ከ40 ዓመት ወዲህ የደረሰች እንግዳ አልነበረችም። በታሪክ እንደሚወሳው ከ80 ዓመት በፊት ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ኩባዊው አልሲንዳር ለነፃነት ተዋግቷል። «ቀይ አንበሳ» የተሰኘ መጽሐፋንም የዘመኑ ፋሺስት ወረራን አስመልክቶ መጻፉና ወደ አማርኛም መተርጐሙ ይታወሳል።

ከሦስት ወራት በፊት ኩባውያኑ የሚያከብሯቸውን የቀድሞው መሪያቸው ፊደል ካስትሮን 90ኛ የልደት በዓል ለማክበር ሽር ጉድ እያሉ ነበር። የልደታቸው ቀን በሚውልበት ነሐሴ 7 ቀን ለፊደል ካስትሮ ልዩ ስጦታ ለማበርከት ሲታትሩ ከቀዩት መካከል፣ የኩባ ሲጋራ አምራቹ ጆሴ ካስትለር አንዱ ነበሩ። ካስትለር ከረዳቶቹ ጋር በመሆን ለ10 ቀናት በቀን 12 ሰዓት እየሠሩ 90 ሜትር የሚረዝመውን ሲጋራ ሠሩ። ፊደል ካስትሮ ሲጋራ ማጨስ ያቆሙት

ወደ ገጽ 78 ዞሯል

ሴት ከሴት

በዚህ ዓምድ የሚቀርቡት ደብዳቤዎች የአሃዞቹ እንጂ የድንት መጽሄት አቋም ላይሆኑ ይችላሉ፣

ሂላሪና ትራምፕ

የትራምፕ ሂላሪን ማሸነፍ አስካሁንም ያልተዋጠልኝ ነገር ነው። ግን አገሩ የዲሞክራሲ ነውና ተቀብሎ መቀጠል ያዋጣል። ባለፈው ዕትም እንዳላችሁት፣ ነገሩ አስገራሚ ነው። እንዳንድ ሰዎች ለልጃቹ ምን ልበል? ሲል አጋጥሞኛል—እኔ ለልጄ የምነግረው የአሜሪካ ዲሞክራሲ እንዴት የህዝብ ውሳኔን እንደሚያከብር ነው። (አያሌው ሙሉት ዲንሸር ኮሎራዶ)

ልመና

ገሞራው ያነሱት ሃሳብ ብዙ ያወያያል፣ ነገሩ እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን ሆኖ እንጂ፣ ርዳታ ጠያቂዎች ሁሉ በርግጥ ርዳታ ፈላጊዎች ናቸው ብሎ መቀበል ያስቸግራል። እንደተባለው ግን ራሳቸውን ችለው የሚቆሙበት መንገድ ቢፈልጉ ጥሩ ነው፣ ሰዉ በዚህም በዚያም አየቆነጠረ እየሰጠ ባክኖ ቀርቷል። ባይሰጥም ግልምጫና ስም ማጥፋት አይቀርለትም። አስቸጋሪ አኮ ነው። (ገነት ከአትላንታ)

የዱባዩ መሪ

ዱባይ ለሥራ አመላለሳልሰው፣ ከሚገርመኝ ነገር አንዱ የዚያች አገር የንግድ አሰራርና እንደት ለዓለም ሁሉ መሰህብ ሆነች የሚለው ሚስጥር ነው። በ አክራሪ አገራት ተከባ እንኳን ሁሉም እንደፈለገው የሚሆንበትን ስር ዓት መዘርጋቷ፣ ለመሪዋ ያለኝን አድናቆት ከፍ አድርጎታል። አሁን ደግሞ ድንቅ ሳይ የኚህን የዱባይ መሪ ታሪክ በዝርዝር ሳነበው የበለጠ የሚከበሩ ሆነው አገኘኋቸው። አንድ ነገር ግን ጣል ማድረግ አፈልጋለሁ። አንዳንድ የኛ ሴቶች ከውንዶች ጋር መውጣት እንደ አቋራጭ ገንዘብ ማግኛ አድርገው ማየታቸው አሳዝኖኛል። ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሲባል፣ ስማቸው የሚነሳው በዚህ ነገር ብቻ ነው—ራስን አክብሮ ሌላ ሥራ መስራትም ይቻላል።
(ብስራት—ከፊኒክስ አሪዞና)

የፍቅር ገጻችሁ ሰፋ ቢል

ስለ ፍቅርና ትዳር የምትጽፉበት ዓምድ ሰፋ ቢል ጥሩ ይመስለኛል። ለሁሉም ነገር መስረቱ ፍቅር ነው። ጥሩ የፍቅር ግንኙነት ከሌለ ጥሩ ትዳር፣ ጥሩ ትዳር ከሌለ ደግሞ ጥሩ ሰው ማፍራት አይቻልም። ፍቅር ከሌለበት ቤት የሚወጣ ሰው ደግሞ ጥሩ የአገር መሪ ለመሆን አይችልም። ለሁሉም ነገር መሰረቱ ፍቅር ነው። በደንብ ጻፉበት። ጥሪ ዕውቀት የሚሰጥ ዓምድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

መፍትሄ መፍትሄ መፍትሄ

ባለፈው የኖቬምበር ዕትም ለአገራችን ችግር መፍትሄው ምንድነው? የሚል ጽሁፍ አንብቤያለሁ። እኛም የቾገረን ፣ ችግሩን የሚነግረን አንጂ መፍትሄ የሚጠቁም አለመኖሩ ነው። አሁን አሁን ስለ አገራችን ችግር መስማት እየሰለቸኝ ነው። ኑሮ ተወደደ፣ ሰው ታሰረ፣ ተገደለ፣ አንዲህ ሆነ ፣ አንዲያ ሆነ .. ሁሉም ይህን ያወራል። ታዲያ ምን አናድርግ? ሲባል የጋራ የሆነ የመፍትሄ ሃሳብ፣ የተጠና እና ውጤት የሚያመጣ ሃሳብ ያለው የለም። ዝም ብሎ መፍትሄው መታገል ነው ይላል። ምን ማለት ነው መታገል? ድፍን ያለ ነገር። እንኳን በአገር ቀርቶ በመካከላችን በመንፈሳዊውም በማህበራዊውም ተቋማት አካባቢ ችግር ሲፈጠር፣ ያንኑ ችግር "እንዲህ አርገው፣ አንዲያ አርገው" እያለ የሚያወራው እንጂ ፣ እንዲህ ቢሆን ጥሩ ነው ብሎ አስታራቂ ሃሳብ የሚያመጣ ሰው አልገጠመኝም። (ዓለም ስምኔ ከአትላንታ)

መውጣትና መውረድ

ድንቅ ጽሁፍ ነው። ዳንኤል ክብረትን ተባረክ በሉልኝ። ለአገለአችን መፍትሄ የጠፋው ሥልጣን ላይ ያሉት ድንገት ቢወርዱ የት እንደሚሄዱ ፣ እንዴት እንደምንቀበላቸው ስለማያውቁ ነው። በሰላም ውጥቶ ፣ በሰላም መውረድ እንደሚኖር የምናይበት ዘመን ሩቅ አይሁን—አሜን ! (ባና ከሲያትል)

Tapestri

diversity. advocacy. empowerment.

በታፕስትሪ የሚዘጋጅ

ወርሃዊ መልክት

የሆነ ሰው

- ... ወደ አሜርካን አገር በውሸት ማታለል ወይም በጋብቻ አምጥቶዎታል?
- ... በአካላዊ፣በወሲባዊ፣ በስነልቦናዊ፣ ወይም በእውንታዊ ማስፈራሪያ አድርሶቦታልከዚህ አገር እንደሚያስወጣዎ ያስፈራራዎታል?
- ... የማይገባዎን ዕዳ እንዲከፍሉ ያስገድዶዎታል?
- ... በስራ ቦታዎ ደህንነት እንዳይሰማዎ እና ሰራ የመልቀቅ ወይም የማቋረጥ መብትዎን ወይም ነፃነተዎን ነፍጎታል?
- ... አርስዎን በመጠቀም ገንዘብ ወይም ሌላ ለግሉ ጥቅም አውሏል?
- ... በአሜርካን ሐገር ወይም በትውልድ ሐገርዎ ካሉ ዘመድ ወይም ጓደኛዎ አንዳይገናኙ አግድዎታል?
- ... ቃል እንደተባልዎ ወይም ከሚሰጡት አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ አልተከፈልዎትም?
- ... የተለያዩ ማስረጃዎችን ደብቆቦታል?
- ... አዎን ከሆነ ምላሽዎ ወይም ሌላ ጥያቄ ካለዎት አንረዳዎታለን በሚከተሉት ስልክ ቁጥሮች ይደውሉልን?
- ... 866- 317- 3733 ወይም 404-299- 0895

የሰራ ባልደረባዎ ወይም የቤተሰብ አባል

- ... በመደብደብ በመግፋት ፣ በመጨፍ ወይም ቁሳቁሶችን በመጠቀም ያስፈራራዎታል?
- ... ያለሱ ወይም ያለሱዋ መኖር አንደማይችሉ ይነግሩዎታል?
- ... ርካሽነት ወይም የበታችነት እንዲሰማዎት ያደርጎታል?
- ... ከዚህ ሐገር እንደሚያስባርርዎት ያስፈራራዎታል?
- ... የኢሚግሬሽን ወይም የስደተኖች ጉዳይ ጽ/ቤትን እ?ርስን ለመቅጣጠር ይጠቀምቦታል
- ... በስራዎ ላይ ጣልቃ ለመውሰድ ለማራቅ ያስፈራራዎታል?
- ... ልጆችዎን ክርሶ ለመውሰድ ወይም ለማራቅ ያስፈራራዎታል?
- ... ከቤተሰብዎ ወይም ከጓደኖዎ ይነጥልዎታል?

... ከእነዚህ አንዱ ነገር ከተሰማዎ ብቻዎትን አዳልሆኑ ይወቁ
... አርዳታ ማግኘት ይችላሉ
... ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 404- 299- 2185
... ታፒስትሪ ብለው ደውሉ

ታፕስትሪ ኢንክ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ በአትላንታ የሚገኝ ድርጅት ነው። ዓላማው የቤት ውስጥ በደል አንዲቆም ማድረግ ነው። ከዚያም ጋር በተያያዘ ሰዎች ስለ ቤት ውስጥ በደልና ስለ ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች እውቀት አንዲኖራቸው ያስተምራል።

ታፕስትሪ ይህንን ለማድረግ የተጥቃ የምክር አገልግሎትና አንዳንድ ጊዜም የህግ ምክር የሚያገኙበትን መንግድ ያመቻቻል። በተጥቃ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ተበዳዮች አስፈላጊ ከሆነ ጊዜያዊ መጠለያ

በደል ከደረሰብዎት በ404 299 2185 ይደውሉ!

ፊደል ካስትሮ...

ከገጽ 74 የዞረ



በ1980ዎቹ ቢሆንም፣ የወጣላቸው አጫሽ እንደነበሩ ለማስታወስ ሲጋራው ተሠርቶ ለልደት በዓላቸው ተበርክቶላቸዋል።

ካስትሮ አብዝተው የሚወዱትን ሲጋራ ለማቆም የወሰኑት ሕዝባቸው ሲጋራ በማጨስ ከሚመጡ በሽታዎች ራሱን እንዲጠብቅ ለማስተማር ሲሉ ነበር። አ.ኤ.አ. በ1985 ገደማ ከአንድ ሚዲያ ጋር በነበራቸው ቃለ ምልልስ፣ ‹‹ሲጋራ ከለኮስኩ ብዙ ወራት ተቆጥረዋል። ከዚህ ውሳኔ የደረስኩት አንድ ለሕዝቤ የምከፍለው የመጨረሻው መስዋዕትነት ሲጋራ ማጨስ ማቆም ስለሆነ ነው። ራሴን ከሲጋራ መነጠል ለኩባውያን ጤና የክፈልኩት መሰዋዕትነት ነው፤›› ብለው ነበርና የቢዝነስ ኢንሳይደር ጋዜጠኛ ክርስቶፈር ውድ ለካስትሶር አንድ ጥያቄ አቀረበለት።

‹‹ካስትሮ ማጨስ ያቆሙት በ1980ዎቹ ነው። አንተ ደግሞ 90ኛ ዓመታቸውን ለሚያከብሩት ካስትሮ 90 ሜትር ርዝመት ያለው ሲጋራ ሰጠታ እበርክተሃል። ትርጉሙ ምንድነው?›› አለው።

ካስትሮም፣ ‹‹ካስትሮ እንደማያጨስ እውቃለሁ። ነገር ግን ለልደቱ ሲጋራውን ለማበርከት ምን ያህል እንደሰፋን ለማሳየት ነው፤›› ሲል ከፊደል ካስትሮ አገዛዝ ጠንካራ ሠራተኝነትን መማሩን ገለጸለት።

አ.ኤ.አ. ከሐምሌ 2006 ጀምሮ ሕመም ላይ የነበሩት ካስትሮ ለ49 ዓመታት የያዙትን ሥልጣን በይፋ የለቀቁትና ለወንድማቸው ራውል ካስትሮ ያስረከቡት አ.ኤ.አ. በ2008 ነበር። ከዚህ ጊዜ ወዲህ ብዙም በሕዝብ ፊት ያልታዩት ካስትሮ 90ኛ ዓመት የልደት በዓላቸውን ለማክበር በሃቫና ካርል ማርክስ ቴአትር ማዕከል በተዘጋጀው ድግስ ከወንድማቸውና ከሌሎች ወዳጆቻቸው ጋር ተገኝተው ነበር።

በዕለቱ የታደለውን መልዕክት ጠቅሶ ቢቢሲ አንዳሰፈረው ካስትሮ ሕዝባቸውን ሰያመሰግኑ፣ የአሜሪካ ተሰናባች ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ጃፓንን በጎበኙበት ወቅት አሜሪካ በሔሮሺማ ላይ ለፈጸመችው በደል ይቅርታ አለመጠየቃቸው ትክክል አለመሆኑን ነቅፈዋል።

ሕዝባቸው ላሳያቸው ክብርና ላበረከተላቸው ሰጠታ ምሥጋና ያቀረቡት ካስትሮ፣ ‹‹ሕዝቤ ከጎኔ መሆኑን ሊፖርቱ አባላትና ለወሳኝ ድርጅቶች ያሉኝን ሐሳቦች እንዳካፍል ጥንካሬ ሰጥቶኛል፤›› ሲሉም ለሕዝባቸው ያላቸውን ክብር አስተላልፈዋል።

በአብዛኛው ኩባውያን ልብ ውስጥ የፍትሐዊነትና የማኅበራዊ አኩልነት ተምሳሌት የሆኑት ካስትሮ፣ 90ኛ የልደት በዓላቸውን ካከበሩ ከሦስት ወራት በኋላ ኅዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

በቁማቸው አያሉ በአልበገር ባይነታቸውና በሶሻሊዝም ጽኑስ ሐሳብ አተጋገኝነታቸው የሚታወቁት ካስትሮ፣ በኩባ ትምህርትና ጤናን ሙሉ ለሙሉ ነፃ በማድረጋቸው የደሃ አባት ይባላሉ። ለደሃና ደሃ አገሮች ደጋፊ እንደነበሩም ዘገባዎች ያሳያሉ። ‹‹ለደሃ አገሮች ክፉደል ካስትሮ የበለጠ የሠራ የለም፤›› የሚሉ አስተያየቶችም በሞታቸው ማግሥት እየተሰነዘሩ ነው።

ለኩባውያንም ሆነ ለዓለም የካስትሮ ሌጋሲ የማይረሳ ነው። በሥልጣን በቆዩባቸው ዓመታት በስደት ያሉ ኩባውያን የሰብዓዊ መብት ይጥሳሉ ብለው ቢወነጅሏቸውም፣ በአገር ውስጥ አኩልነትንና ማኅበራዊ ፍትሕን እንግሠዋል።

መንግሥታቸው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ደክተሮችና መምህራን አፍርቷል። በኩባ የሕፃናት ሞትና መሃይምነት በማም ጥቂት ነው። ሆኖም መንግሥት መር የሆኑ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ብዙ ኩባውያን ህብታም እንዳይሆኑ አግዷል የሚል ትችት አለ።

ካስትሮ ባደረጉት ድጋፍ ከኩባ ወታደሮች ጋር የኢትዮጵያ ጦር የዚያድ ባሬ መደበኛና ሰርጎ ገብ ውራሪ ወታደሮችን ከኢትዮጵያ ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ፣ በ1971 ዓ.ም. በጅግጅጋ በተከናወነው የድልና የመልሶ ማቋቋም በዓል በመገኘትና ከወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ ከሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጋር በመሆን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ አሴቶች የተስተናገዱበትን ኢግዚቪሽን በጋራ የከፈቱት ካስትሮ፣ በኢትዮጵያ በጤናውና በትምህርቱ ዘርፍ የነበራቸው ድጋፍም አይዘነጋም።

በወቅቱ ከጅግጅጋ የአሥር ደቂቃ በረራ በማድረግም የኢትዮጵያና የኩባ ወታደሮች ‹‹የልምምድ አንበሳ›› በሚል መጠሪያ ያካሄዱትን የውጊያ ልምምድ መመልከታቸው ይታወሳል።

የወቅቱ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ጋዜጠኛ እንደሚያስታውሱት፣ ካስትሮ ንግግር አላደረጉም። ሆኖም ከጋዜጠኛው በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ‹‹ቢታሪክ የማውቅትን ኢትዮጵያ በአካል በማየቴ ደስተኛ ነኝ። ሁለቱ አገሮች በጤናውና በትምህርቱ ዘርፍ አብረው የሚሠሩ ይሆናል፤›› ብለው ነበር። ቃላቸውን የጠበቁት ካስትሮ በወቅቱ በኢትዮጵያ ያደረጉት የጤናና የትምህርት ድጋፍም የሚዘነጋ አይደለም። ኢትዮጵያ ከማሊያን ወረራ በኋላ ቃይቶ የማይታወቅ አደገኛ ወረራ ሲካሄድባት ቀድመው የደረሱት ካስትሮ እንደነበሩ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም።

ካስትሮ ከባላንጣቸው አሜሪካ ጋር በነበራቸው አሉታዊ ግንኙነት ሳቢያ፣ አሜሪካ ካስትሮን ከሥልጣን ለማስወገድ ያልፈነቀለችው ድንጋይ አልነበረም። የኢኮኖሚ ማዕቀብ ከመጣል አስከ ግድያ ሙከራ ደርሳም ነበር። ሆኖም የኩባ የቀድሞ ዋና ደጋፊ ሶቪየት ኅብረት ከተበታተነች በኋላ እንኳን፣ አሜሪካ ኩባን ማንበርከክ ወይም አጋር ማድረግ አልቻለችም ነበር። ካስትሮን ለመግደል ከ600 በላይ ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን፣ አሜሪካም በብዙዎቹ እጇ አንዳለበት ዘገባዎች ያሳያሉ። እንደ ዘገባዎች፣ አሜሪካ ካስትሮን ለማስገደል ወይም ከሥልጣን ለማውረድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጪ አድርጋለች። ሆኖም አልተሳካላትም።


የአሜሪካ ባለሀብቶች ከኩባ ጋር ያላቸውን ንግድ ሙሉ ለሙሉ ቢያቋርጡ፣ የአሜሪካ መንግሥት ደግሞ በኩባ የዲሞክራሲ አራማጅና የካስትሮ ተቃዋሚ የሆኑ ድርጅቶችን ቢረዱም ለውጥ አልተገኘም። ከባራክ ኦባማ በፊት በነበሩ አሥር ፕሬዚዳንቶች ዘመን ኩባን ለማንበርከክ የተከናወኑ ሽፍጠችም አልተሳኩም።

የአሜሪካው 44ኛ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ አ.ኤ.አ. በ2014 ያልተጠበቀ ንግግር ሚድረጋቸው በኩባና አሜሪካ መካከል የነበረውን የሻከረ ግንኙነት እርግቦታል። ኦባማ አሜሪካ ከኩባ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማደስ እንደምትፈልግና በኩባ ላይ ተጥሎ የነበረው የንግድ ልውውጥና የጉዞ ማዕቀብም መላላት ለሁለቱ አገሮች መልካም እጋጣሚ ነበር።

በአንድ በኩል በኩባ ላይ የተጣለ ገደብ ምንም ለውጥ እንዳላመጣ በመናገራቸው፣ በሌላ በኩል ደሞክራሲን አናሰፍናለን የሚሉና ካስትሮን የሚቃወሙ ድርጅቶችን መደገፋቸው ያስተቻቸው ኦባማ፣ ከኩባ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረትም በአሜሪካ የታሰሩ ሦስት የኩባ ሰላዮችን ለቀዋል። ኩባም በምትኩ የአሜሪካ የልማት ሠራተኛ ተብሎ ለሲአይኤ ሲሰልል የተገኙትን ሦስት አሜሪካውያን ለቃለች። ይኼ በኩባ ታሪክ ትልቁ ድል ቢሆንም ሥልጣናቸውን አ.ኤ.አ. ከ2008 ወዲህ ለወንድማቸው ራውል ካስትሮ ያስተላለፉት ካስትሮ ዝምታን ነበር የመረጡት። ‹‹አሁን ጠርነቱን አሸንፈናል፤›› ሲሉም መግለጫ የሰጡት ራውል ነበሩ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የላቲን አሜሪካ ታሪክ ሲነሳ ያለፈደል ካስትሮ አይሆንም የሚል አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ሲሆን፣ የተለያዩ አገር መሪዎችም

ወደ ገጽ 87 ዞሯል



በዳንኤል ክብረት
www.danielkibret.com

ክትውረዩ

አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር በዋናው በር በኩል ወደ አሙራ ጎዳናው ይወጣል።

ጥቂት እንደተጓዘ ደግሞ አዚያ አካባቢ ቆመው አለፊ አግዳሚውን ከሚላከፉ ጎረምሶች ጋር ይጨቃጨቃል። ጭቅጭቁ በምን እንደተጀመረ ማናችንም አላወቅንም። እነዚያ ጎረምሶች ግን በመምህሩ ላይ ‹ሙድ› ይዘውበታል። ‹እሺ - - ሊቁ› እያሉ በሰድብ ጠረባ ይረፈርፉታል።

አርሱ ደግሞ ሰድቡን አልቻለበትም። ‹‹ያልተማራችሁ፣ ማይሞች፣ ከሰድብ በቀር ሌላ የማታውቁ፣ ደደቦች›› ይላል ሥሩ አስኪንታተር ድረስ በቁጣ። በቸከሻው ያንጠለጠለው ቦርሳ ይዘወዘዛል፣ መነጽሩም ልውደቅ ልውደቅ ይላል።

‹‹እሺ ሊቁ፣ ለምን ላፕቶፕሽን ከፍተሽ ዕውቀት አትቄጽብንም›› አያሉ ጎረምሶቹ ይሳሳቁበታል።አርሱ ይበግናል። ‹‹ኤፍ ብቾ ነው እንደ ቦርሳሽ ሙስጥ የያዝሽው፤ በናትሽ አንድ አምስት ኤ የለሽም›› ይሉታል። አርሱ ይንዘፈዘፋል። ‹‹አንድ ሁለት ኤ ብትሰጡን ችብ አርገን በርጫ እንገዛበት ነበር›› ይሉታል። ሰው እየተሰበሰበ፣ እየከበበው ይሄድና የጎረምሶቹን ስድብ እንደመዝናኛ ቱጥርት አብሯቸው ይሳሳቃል። አርሱን ኮሜዲ ፊልም እንደሚሠራ ተዋናይ ቆጥረውት በነጻ ይኮመኩማሉ። ጎረምሶቹ እንድ ተረብ በመረቀሩ ቁጥር ከብቦ የተሰበሰበው ‹አስገቡለት› አያስ እንደ ጎጃም ልቅሶ ያጅባቸዋል።

አየቆየ ክበባው አየሰፋ፣ ሳቁ አየደራ፣ የመምህሩ ጎዲት ወደ እሳተ ገሞራነት እየተቀየረ ሄደ። መምህሩ ከዚያ ክበባ ልውጣ ቢል እንኳን ሰው በጎረምሶቹ ተረብ ስለተዝናና በቀላሉ የሚያሰወጡት አይመስልም። የተከፈለው አዝማሪ መስሏል። የሚያውቃቸው ሰድቦች አልቀውበት አሁን ማቁን ማውጣትና ‹‹አሳይሃለው›› አያለ መዛት ጀምሯል።

> “ኣንበሳው በገዛ ጫካው ቢኖር ማን ዓጸፍርው ነበር?..”

የአንዳንድ የእንግሊዝኛ ሰድቦችን ሲሳደብም
የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው
በእንግሊዝ አናግሪያቸው›› ብለው ሳቁበት። በልቡ አንዳች የሥሊስ ኃይል መጥቶ አንዲገላግለው አየተመኘ ነበር። ወደ ሰድቡ ሜዳ አሰቦ ሰላልገባ አሰቦ ሊወጣ አልቻለም።

በዚህ መካከል በግራ አጃቸው ጋዜጣ አጣጥፈው የያዙ አንድ አዛውንት ሁላችንንም አየገረተሩ፣ እንደ ሙሴ የሕዝቡን ባሕር ለሁለት አየከፈሉ ወደ መካከል መጡና ያንን መምህር እጁን ይዘው በገዘምታ ጎትተው ከክበባው አወጡት፤ ጎረምሶቹም ‹ሼባው ልቀቀው እንጂ›› እያሉ ተረቢቸው። አርሳቸው ቀናም አላሉ፤ መልስም አልሰጡ። አየሰነጠቁ አንደገቡ፣ አየሰነጠቁ ወጡ።

ከዚያም ወደ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መታጠፊያ ዘወር አደረጉትና ‹‹ለምን ልጂ፣ ለምን?›› አሉት።

‹‹ከዩኒቨርሲቲ ስጣ ለከፉኝ፤ አኔም መልስ ሰጪቻው››
‹‹ተማሪ ነህ?›
‹‹የዩኒቨርሲቲ መምህር ነኝ››
‹‹እና መምህር ሆነህ ነው ከአነርሱ ጋር ሰድብ የገጠምከው፤ ጥፋተኛው አንተ ነህ›› አሉት። እኛ ትንሽ ራቅ ብለን የሚሉትን መሰማት ጀመርን።
‹‹ተመልከት አዚያ›› አሉት በአመልካች ጣታቸው ወደ አንበሳ ግቢ እቅጣጫ አያመለከቱ። ‹‹እዚያ ግቢ ውስጥ ምን አለ?›› አሉና ጠየቁት።
‹‹አንበሳ ነዋ››
‹‹አንበሳ ማን መናሪያው ግቢ ውስጥ ነው አንዲ?››
‹‹አንበሳማ የዱር አንሰሳኮ ነው፤ ምን ዓይነት ጥያቄ ነው የሚጠይቁኝ፤ የዩኒቨርሲቲ መምህር ነኝ አያልኩም›› መምህሩ ተናደደና ጥሏቸው ሊሄድ ከጀለ።

አርሳቸውም ከአናቱ ጋር መንገድ አንደሚሻገር ሕጻን እጁን አጥብቀው ያዙት። ‹‹ወዳጂ፣ ሰው በውስም ነገር ሊት አይሆንም። በአንዱ ሊት ሲሆን በሌላው ማይም ነው፤ በአንዱ መምህር ሲሆን በሌላው ተማሪ ነው፤ በአንዱ ጎበዝ የሆነ ለሌላው ሰነፍ ነው›› አሉት። ትንሽ ቀዝቀዝ አለ።

‹‹አንበሳው በገዛ ጫካው ሙስጥ ቢሆን ኖሮ ማን ይደፍረው ነበር? ማን ጀግና ነበር ሃምሳ ሳንቲም ከፍሎ በሃምሳ ሜትር ርቀት የሚያየው? ማን ጀግና ነበር ቀርቦ ፎቶ የሚያነሳው? ማን ጀግና ነበር ከአንበሳው ጋር ፎቶ ሲነሳ የሚውለው? ጫካው የአርሱ ክልል ነው፤ የአርሱ ሠገነት ነው።

አዚያ የቀለበቱ ጌታ (Lord of the Ring) አርሱ ነው። ከተማው

ወደ ገጽ 86 ዙሯል

በጀትና እርዳታ...

ከገጽ 11 የዞረ .....

ለማሳየት ብቻ እንጂ። ሰዎች የሚሆናቸውን መርጠው፣ ዓትማቸውን እይተው፣ ደስ ብሏቸው ከሆነ እሰየው። ጥያቄው ነው ወይ? ነው።

ትንሽ ትንሽ የሚያገኟትን ትርፍ በምኑም በምኑም እየወሰድንባቸው እንዳያድጉ እንዳናደርጋቸው ያሰጋል። ብዙዎቹ ብሶት አላቸው፣ ከማሻሸ በላይ የሚሆነውን የስፖንሰርሺፕ ጥያቄ "ከሰው ላለመለየት" ያደርጉታል እንጂ ደስ ብሏቸው አይደለም። ብዙዎቹ ንግድ ቀዝቅዞ ልንዘጋ ነው ቢሉ እንኳን፣ ስርዳቱው ጥያቄ ቢታቸውን የጎበኙ ሁሉ መጥተው ማሟሟቃቸው ያጠራጥራል። በሚቀጥለው ዓመት ሲመጡ ተዘግቶ እንኳን ቢደርሱ "ሙይ ቀዘጋ እንዲ?" ብለው ወደሚቀጥለው ይሄዳሉ እንጂ ችግሩን የሚጋሩ ጥቂቶች ናቸው።

ይህ ነገር ትዳር ላይም ችግር ሲፈጥር ይታያል። ባል ሲሰጥ ሚስት እታውቅም፣ ሚስት ስትሰጥ ባል እያውቅም። አንዳንድ ጊዜ ባልና ሚስቱ ባላንጣ የሆኑ ድርጅቶች ደጋፊ ይሆኑና እሱ ለዚያ፣ እሷ ለዛኛው እየሰጡ ጦርነቱን ያሰፋታል። ከዚያስ በላይ አንድ ቦታስ ቢሆኑ ያለ በጀት የሚደረግ ወጪ ሁሉ ጭቅጭቅ መፍጠሩ ይቀራል?



አንኳን እኛ ዝቅተኛ ኑሮ ያለን ቀርቶ ሚለየነር የሆኑት አንኳን በ ዕቅድ ነው የሚያደርጉት። ዘ ዊክንድ (አቤል ተስፋዬ) የተባለው በዓለም ታዋቂ ኢትዮ-ካናዳዊ ዘፋኝ፣ ሚለየነር ነው። በሙዚቃው ዓለም ቁንጮ ሆኗል። ያድርግለት። ግን አቤልም አንኳን ሲረዳ በዕቅድ ነው። ባለፈት 8 ወራት ውስጥ ለሶስት ድርጅቶች የረዳው ሃምሳ ሃምሳ ሺህ ዶላር ነው። ይህ የመደበው በጀት ነው። ምናልባት እሱ የረዳው ድርጅት የሚፈልገው መቶ ሺህ ይሆናል - ግን የአቤል ድርሻ 50ሺ ነው። ሌላውን ደግሞ ሌላው ይሙላ እንጂ ገና ለገና አለኝ ብሎ መቶሺውን ላጥ አላደርገም። በበጀት መኖር መልመድ ግድ ነው።

በኢኮኖሚስቶች ምክር መሰረት አንድ ሰው ለቤት ኪራይ ወይም ለሞርጌጅ ማውጣት ያለበት ከገቢው 30% ብቻ ነው። ከዚህ በላይ ላውጣ ካለ ከበጀት ውጥቷል። አንድ ሺ ዶላር በወር የሚያገኝ ሰው ከ300 ብር በላይ አውጥቶ የቤት ኪራይ ከተከራየ ገንዘቡን እያባከነ ነው ማለት ነው። ከዶለገ ደባል ሆኖ፣ ከፈለገ አንድ መኝታ ቤት ለሁለትም ቢሆን እየኖረ በጀቱን መጠበቅ አለበት። ያ ማለት ሁልጊዜ የደሃ ኑሮ ይኑር ማለት አይደለም። ዘና ማለት ከፈለገ ገቢውን ከፍ ማድረግ ይኖርበታል። በወር አስር ሺህ ብር አግኝቶ የሶስት ሺህ በር በወር አፓርትመንት ወይም ቤት ውሰጥ ቢኖር መብቱ ነው።

ጥያቄው ለጠየቀን ሁሉ በይሉኝታ እየሰጠን አስከመቼ በመንገዳገድና በምሬት እንኖራለን? ነው። ልክ ነው፣ ማህበራዊ ኑሯችን በዝቷል፣ በመንፈሳዊውም ይሁን በፖለቲካው ቦታ የምናውቃቸው ሰዎች ሺህ ሆነዋል፣ ስለዚህ ከመዋጮ ጥያቄ ልናመልጥ አንችል ይሆናል። ግን አናስተውል፣ ልናደርግ የምንችለው አንድ ነገር፣ ያቅማችንን ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብን ችግር በሙሉ የማስወገድ ሃላፊነት እኛ ላይ አልተጫነም። አንድ ሀዳን አንዳትማችን ከረዳን፣ ያገሩን ሁሉ ህዳን የግዴታ መርዳት የለብንም። ለሌላው ደግሞ ሌላ ሰው ይኖረዋል። በረዳነው ሰው ብዛት አንጸድቅም፣ ያቅማችንን ያህል በማድረጋችን እንጂ።

አንዳንዶቻችን ባለን ጊዜ ፣ በ"ደህናው ጊዜ" ስንሰጥ የኖርን ነን። ዛሬ ኑሮ እንደ ድሮው አይደለም፣ ሥራ ቀዝቅዟል፣ ሞርጌጅ እንኳን በመክራ ነው የምንከፍለው፣ ይህን ሁሉ በልባችን እናውቃለን። ነገር ግን ድሮ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበረን ስምና ዝና እንዳይጠፋ በመስጋት ብቻ ዛሬ መዝረጥ እያደረግን የምንሰጥ አለን። ይህንን የሚያውቁ እንኳን "እሳቸው መኝም የታውቀው ነው፣ ጨረታውን መሙሰጻቸው አይቀርም - አባ መስጠት ናቸው" አያሉ ማሚሟቁንም ይችሉበታል። እኛም ያቺ የድሮ ዝና እንዳትጠፋ የሚቀጥሉው ወርን የሞርጌጅ ገንዘብ አውጥተን ሰጥተን ሜብጨባ በሜብጨባ እንሆናለን። መቅረት ያለበት ይህ ነው። ፈጣሪም ከአሥር አንድ ያለው ለዚህ ነው። ገቢያችን ከቀነሰ እኛም መስጠታችን መጠኑ ሊቀንስ ግድ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ ለጠየቀን ሁሉ መስጠታችን የልመና ባህልን አንዳያስፋፋ ያሰጋል። አበሻ መስጠቱ አይቀርም ብለው በየቀኑ ርዳታ ጠያቂዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። መቶ ብር ዘርዝረን ለምናውቃቸውም ለማናውቃቸውም ለአስር አስር ብር ከምንሰጥ በደንብ ሥራቸውን አጥንተን፣ ግልጽነታቸውን እይተን፣ አምነንበት ለመረጥነው ለአንዱ መቶ ዶላሩን ብንሰጥ የበለጠ የሚሻል ይመስለናል። ሰው የማያምንበትና ግልጽ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ ለምን ይሰጠዋል? ሃምሳ ዳቦ ከመላስ አንዱን መማመጥ ይላሉ አባቶቻችን። በዚህ የተነሳ በትክክል የሚሰሩት እየተጎዱ፣ የማይሰሩት እየተጎሟቸው ይታያል። እንደዚያ ካደረገን በትክክል እንዲሰሩና ግልጽ እንዲሆኑ ማነቃቃት እንችላለን።

አስቡት፣ ብዙ ቦታ የሚመጡ የርዳታ ጥያቄዎች፣ የመዋጮ ጥያቄዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ይሁን እንጂ፣ ዓላማቸው ባብዛኛው ተመሳሳይ ነው። ሌላ ነገር ከሌለ በስተቀር ሊቀላቀሉ የሚችሉም ናቸው። ቤተክርስቲያን በፍጹም እጥረት በሌለበት በዲሲ አካባቢ፣ አንድ ሰው ተነስቶ አዲስ ልከፍት ነውና ርዳታ ቢለን ፣ "ለምን?" ብለን ብንጠይቅ እግዜር የሚቆጣ አይመስለንም። አስራ ምናምን ሬዲዮ ጣቢያ ባለበት ከተማ አንድ ሰው ተመሳሳይ አንድ ሬዲዮ ቢከፍት ርዳታ ቢጠይቅ "ለምን?" ብሎ መጠየቅ ሃጢአት አይደለም። የፖሊቲካ ድርጅት እጥረት በሌለበት የኢትዮጵያ ፖሊቲካ፣ አዲስ ድርጅት መስርቶ "እርዱኝ" ቢል ለምን ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ለአስር የፖሊቲካ ድርጅት አስር አስር ብር ሰጥቶ ከቤት ኪራይና ከሰልክ ወጪ አንዳያልፉ ከማድረግ ተቀራርበው አንድ ሆነው ወይም ለአንዱ የበለጠ ለምናምንበት መቶ ብሩን ሰጥተን ከቤት ኪራይና ሰልክ ተርፎ ሌላ የፖሊቲካ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ይሻላል። የሚረዳው ያጣ እኮ ቢዘጋስ ምን ችግር አለው?

አንድ ጊዜ ደብረብርሃን ሥላሴ በቀን ሁለት ጊዜ ተቀደሰ አሉ። እናም አንዱ ደብተራ "ጉድ ጉድ ጉድ" እያለ ሲጮህ፣ ሰዎች ተጠግተው "ምን ሆነህ ነው ጃል?" ይሉታል። "አልሰማችሁም እንዴ? ደብረብርሃን ሥላሴ በቀን ሁለት ጊዜ ተቀደሰ አኮ ቃይቶ የማይታመቅ ነገር !!" ሲል ይመልሳል። እነሱም "ለምን አባክህ?" ይጠይቁታል። እሱ ምን ቢል ጥሩ ነው "ለምን የሚል ጠፍቶ!!"

በርግጥ ለምን ተብሎው ሲጠየቁ "ከረዳህ አርዳ፣ ለምን ምናምን ብሎ ጥያቄ ምንድነው?" ብለው የሚቆጡ አሉ። ከዝርዝራችን ውስጥ ማስወገድ ያለብን እነዚህ ዓይነቶቹን አትጠይቁን ባሎችን ነው። ጥሩ የሚሰሩ ሊደገፉ ይገባል። ለዚህ ደግሞ እንደገቢያችን መጠን በጀት መመደብ ይገባናል።

በበጀት እንዳንኖር የያዘን ምንድነው? ለመሆኑስ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ሰዎችና የንግድ ባለቤቶች ምን ይላሉ? ዞር ዞር ብለን ለማነጋገር ሞክረናል። በሚቀጥለው ወር ያሉትን ይዘን እንመለሳለን። ሃሳብና አስተያየት ካላችሁ በአድራሻዎቻችን ላኩልን። ይቆየን።

[redacted]

Kids/Parents Corner

LOVE YOUR MOTHER

A poor couple who lived in a small village in London. They had only one son. Gave him the best education. Son graduated as an Engineer in the nearby city. Eventually,got married to a rich girl.

Initially, they lived with his parents in the village. Soon the wife got tired of village life and persuaded the husband to move to the city leaving the old parents in the village.

As time passed by the husband seen an advert in the newspaper about a vacancy in Barnet. He was successful and lived in Barnet for years with his wife. Regularly he used to send money to parents. Eventually with time he stopped and forgot about his parents ever existed. Every year he made Hajj(pilgrimage) and immediately after that he used to see someone telling him in a dream that his Hajj is not accepted.

One day he related story to a pious Aalim who advised him to go back to London to visit his parents.

The man flew to London and reached the boundary of the village. Everything had changed. He could not find his house. He asked a small boy about the whereabouts of so and so. The little boy directed the man to a house and said: "In this house lives an old blind lady who lost her husband a few months ago. She has a son who migrated to Saudi Arabia years back and never came back again. What an unfortunate man?"

Son enters the home and finds his mother on the bed. He tip-toed as not to wake her up.He hears the mother whispering or mumbling something. He gets closer to hear her voice. This is what the mother was saying: "God ! I am now very old and blind. My husband just died. There is NO HUSBAND to lower me in my grave when I die. So please send my son to fulfill my last wish. "

This is the ending of a story where the PRAYERS of a mother is accepted. A human body can bear only 45 del (unit) of pain. But at the time of giving birth,a mother feels up to 57 del(unit) of pain. This is similar to 20 BONES GETTING FRACTURED, all at the same time!! LOVE YOUR MOTHER WITH EVERY RESOURCE IN YOUR LIFE, EVEN WITH YOUR HUSBAND OR WIFE. ♥ LOVE YOUR PARENTS ♥

አርሰዎ የትኛው አይነት ወላጅ ናት?

(ወ/ሮ መታሰቢያ ማሞ)

ወላጆች በጥቅሉ ሦስት አይነት የአስተዳደግ ዘይቤን ሊከተሉ ይችላሉ። ‹‹ፈላሚ ቆራጭ ወላጅ››፣‹‹ሁሉም ይሁን ባይ ወላጅ›› እና ‹‹የአኩልነት ወላጅ›› ብለን እንከፍላቸዋለን። አርሰዎ ከየትኛው ወገን እንደሚመደቡ ለመለየት የሚከተሉትን ሦስት ምሳሌዎች ይመልከቱ።

1. የነ ወይዘሮ ሔርሜላ ቤተሰብ

ወ/ሮ ሄርሜላ ልጆቻቸው በትምህርታው ስኬታማ እንዲሆኑ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤ ሆኖም ልጆቻቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ በብሰጭት የሚመልሱላቸው በመሆኑ ልጆቹ በመፍራት ያጋጠማቸውን ነገር ይደብቃሉ። ሲበሳጩባቸውም በልምጭ ይገርፏቸውና ያንበረክኳቸዋል። ልጆችን መምከርም ወላጅን እንደሚያደክም፣ አርጩሜው ግን ሰውነታቸው ላይ ምልክት ስለሚተው ስለሚቆጠቁጣቸው አዓጉል ባሕርይን ለማስተካከል ይችላሉ ብለው ያምናሉ። አዚህ ላይ አንድ ያልደበቁት ነገር ልጆቻቸው ምንም ነገር በግልጽ ሊያዋዩዋቸው ቁጭ ብሎ ለመወያየት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ነው። ለልጅ ፊት መስጠት ጥሩ አይደለም ብለው በጽኑ ያምናሉ።

2. የነ ወይዘሮ ምንትዋብ ቤተሰብ

ወ/ሮ ምንትዋብ የአምስት ልጆች አናት ናቸው። ባለቤታቸው የክባድ መኪና አሽከርካሪ ስለሆኑ ለብዙ ጊዜ በቤት ውስዋ አይኖሩም፤ልጆቻቸው የእጅ ሰራ የምግብ ዝግጅትም ሆነ ሌላ ክህሎት የሚጠይቅ ስራን በማንኛውም አድሜ ያው ቢሆን በሙከራ እንዲያዳብሩ እናታቸው ያለምንም ገደብ ይፈቅዱላቸዋል፣ ያበረታቷቸዋል። ልጆቹ ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የመረዳዳትና የመተዛዘን ሲሆን ቁጭ ብለው በሚነጋገሩበት ጊዜም ደስታ የተሞላበት ጊዜን ያሳልፋሉ፤ልጆቹ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። ችግሩ ምን እንደተማሩና ከማን ጋር እንደዋሉ ክትትል የሚያደርግ አካል ግን የለም። በመሆኑም ልጆች የፈለጉት ጓደኛ ቤት ሄደው ማደር ይችላሉ። ቤተሰብን ሳያስፈቅዱም ተመሳሳይም ሆነ ተቃራኒ ጾታ ጓደኛን ማሳደር ወይም በቤት ውስጥ ማኖር የተለመደ ተግባራቸው ነው። ያለገደብ ብዙ ነገር የማድረግ መብትን ይሰጧቸዋል።

3. የነ አቶ ታሪኩ ቤተሰብ

አቶ ታሪኩ እና ወ\ሮ ማርታ ሦስት ልጆቻቸውን በቤት ውስዋ የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ባህርያትን፣ ሲያጠፉም የሚወሰደውን እርምጃ ከልጆቹ ጋር በመስማማት አጽድቀው ተግባራዊ ያደርጋሉ።የቤተሰብ አባላቱ በየእለቱ ያጋጠማቸውንና ያከናወኑትን ቁጭ ብለው ይወያያሉ። ምንም ዓይነት ችግር ሲያጋጥም ሁሉም ለውይይት ይቀመጣሉ።ውሳኔም አብዛኛው ሰው በተስማማበት ይወሰናል። ቤተሰቡ አባላት ከቤት ውጪ አብረው ጊዜ የሚያሳልፉበት ፕሮግራም አላቸው። ልጆቹም እርስ በርሳቸው በትምህርት፣በመመካከርና በቁሳቁስም ይረዳዳሉ።

የእርሰዎ አስተዳደግ ከላይ ከተዘረዘሩት ውስዋ ከየትኛው ቤተሰብ ጋር ይመሳሰላል? እስኪ ቀጥሎ ደግሞ የአያንዳንዱን ቤተሰብ ሁኔታና መገለጫዎቹን ይመልከቱ።


የነወይዘሮ ሔርሜላ አስተዳደግ ‹‹ፈላጭ ቆራጭ አስተዳደግ›› በመባል ይታወቃል። ብዙም ተመራጭ አይደለም። ይህ አይነቱ አስተዳደግ የሚከተሉት መገለጫዎች አሉት። ወላጆች፡ ልጆች ምን ማድረግና አለማድረግ አንዳለባቸው ይነግራሉ። - ህጎቻቸው ግልጽና ሊቀየሩ የማይችሉ ናቸው። - ማንኛውም የውሳኔ ሂደት ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ። - የቤተሰቡን ግብ ብቻቸውን ያወጣሉ። ማበረታቻን ይሰጣሉ። - ቅጣትን ራሳቸው ይፈጽማሉ። አቋመ ጽኑ ናቸው። - ምንም ድርድር አይፈቅዱም። ውጤት ተኮር ናቸው።አስገዳጆች ናቸው። - ትእዛዝ ተኮር አቀራረብ አላቸው። አንዲሁም ስልጣን ተኮር አቀራረብ አላቸው።

2. የነወይዘሮ ምንትዋብ ቤተሰብ ‹‹ሁሉም ይሁን ባይ አስተዳደግ›› ዘይቤን ይከተላል። ብዙም ተመራጭ አይደለም። የሚከተሉት መገለጫዎች አሉት። ልጆች ሁሉን ነገር በራሳቸው እንዲያከናውኑ በመተው ችግር ሲደርስባቸው ብቻ ጣልቃ የሚገባበት ነው። - በሚፈቀዱና በማከለከሉ ነገሮች ላይ ድንበር ወይም ገደብ ያስቀምጣል ነገር ግን ተግባራዊነቱ ላይ ክትትል የለም፤ - ልጆቹ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው ሁሉም ነገር የልጆቹ ሀሳብ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድበት ዓይነት አስተዳደግ ነው። የልጆችን የውስጥ ተነሳሽነት (ማለትም ራስን የማሻሻል፤ በግል ግብ ላይ መድረስና የመሳሰሉት ፍላጎቶቻቸውን) ለማውቅ ወላጆች ችሎታ ይኖራቸዋል። በመሆኑም ልጆችን ወደሚፈለገው አቅጣጫ ለመምራት ያስችላል። ራሳቸውን እንዲገልጹ ያበረታታሉ ይህም የልጆቹን የፈጠራ ችሎታ ከማሳደጉ በተጨማሪ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ እድልን ይሰጣቸዋል። ወላጆች አሞላቃቂ ናቸው። ብዙ አስገዳጅነት አያሳዩም። - ወላጆች ከልጆች የሚጠብቁት ጥቂት ነገር ነው። - ልጆች ምንም ላይነት ጥፋት ቢያጠፉ ታጋሽነት ይታይባቸዋል።

3. የነአቶ ታሪኩ ቤተሰብ ‹‹ አኩልነት ያለበት የአስተዳደግ›› ዓይነት ይባላል። የሚከተሉትን ያካትታል። .. ልጆች ምርጫ እንዲያደርጉ ሚና ይኖራቸዋል። ... የቤተሰቡ አባላት ግብን በማውጣት፣ ውሳኔን በመስጠት ላይና በችግር አፈታት ረገድ ተሳትፎ ያደርጋሉ። .... የመደራደርና ሀሳብን የማቀራረብ ግንኙነት በሰፋት ይተገበራል። ...ቀለል ያሉ ህጎችን ማውጣትና ካልተተገበሩም ሊደርስ የሚችለውን ውጤት ልጆቹም ተረድተውት የሚከናወን ከመሆኑም ባሻገር ለለውጦች ቦታ የሚሰጥ ነው። ... እውንታዊ ግንኙነት ከመኖሩም በላይ ግልጽነት ይታይበታል። ...ችግሮችን እንደ ራስ ማየት መቻል ይታይበታል። የቤተሰብ አባላት ይደጋገፋሉ። የስነስርዓት እርምጃ/ቅጣት እንደ ማስተማሪያ የሚወሰድበት አስተዳደግ ነው። በአጠቃላይ ሁሉም የአስተዳደግ አይነቶች የራሳቸው ጥቅምና ጉዳት ቢኖራቸውም እኩልነት ያለበትን አስተዳደግ የሚከተለው የአቶ ታሪኩ ቤተሰብ የተሻለ ውጤታማ ልጆችን የማፍራት እድል አለው። በሌላ አነጋገር ይህንን አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ለልጆቻቸው ፍላጎቶች ምላሽና ትኩረት የሚሰጡና ስሜት የሚኖራቸው ናቸው። እርሰዎም ይህንኑ አይነት አስተዳደግ ለማዳበር ይሞክሩ።

ወይዘሮ መታሰቢያ ማሞ ‹‹ብአሁን ጊዜ ልጆችን አሳድጎ ለፍሬ ማብቃት›› የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲ ናቸው።

ፖሊስ



ከአዲስ አበባ 97 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። አመሠራረቷም ከኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መስመር ጋር የተያያዘ ነው። ከተማዋ 100ኛ ዓመቷን አክብራለች። በቀዳሞትነት ኦሮሞዎች የመሠረቷት ሲሆን በኋላ ላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ሆናለች። ይህም የሥራ፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የመቻቻልና የዕድገት ከተማ አስብሏታል።

የከተማዋም መሠረተ ልማት በመንገድ፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ በኤሌክትሪክ ኃይልና በትምህርት ቤቶች እሽፋን ሲታይ ከሞላ ጎደል መልካም ነው። በተለይም በትምህርት ዘርፍ ከአፀደ ሕፃናት (ቅድመ መደበኛ ትምህርት) ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ እንዲሁም በጤና ዘርፍ የግሉን ዘርፍ ጨምሮ ከጤና ጣቢያ እስከ ሪፈራል ሆስፒታል አላት።

በኢንዱስትሪውም፣ የሙጫ ባለሀብቶችንም ያሳተፉ ኢንዱስትሪዎች ባለቤት ናት። ከጥቃቅንና አነስተኛ ተነስተው ትልቅ ደረጃ የደረሱ ማፍራት የተቻለባት ከተማ ስትሆን፣ በተለይ ለአዲስ አበባ ቅርብና የኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መሥመር መተላለፊያ መሆኗ፣ አንድ የንግድ ማዕከል ሆና እንድታገለግል አድርጓታል።

ለኦሮሚያ ክልልም ሆነ በአጠቃላይ ለአገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ የኮንፍረንስ ማዕከል ሆና እያገለገለችም ትገኛለች። ይሁን እንጂ ገልማ አባገዳ አዳራሽን ጨምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች፣ የሶደሬ ሪዞርት፣ ባኮ የአንፋሎት ጠበል የመሳሰሉ መሰህብ ቢኖራትም፣ በቱሪዝም ዘርፍ ብዙ ተሠርቷል ለማለት አያስደፍርም። የሚጎበኙ ቦታዎችን ከማዘጋጀትና ከአደረጃጀት አኳያ መከናወን የሚገባቸው ሰፊ ሥራዎችም አልተነኩም።

በታላቁ የሰምጥ ሸለቆ ውስጥ የምትገኘው ይህች ከተማ ሞቃታማ የአየር ፀባይ ቢኖራትም፣ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ፣ ዋል አደር ብሎ ለሚመለስ ወይም በአጠቃላይ ለጎብኚዎቿ ጥሩና ተስማሚ ናት። ብዙ የተዘመረለትና አየዘመነች ያለችው ይህች ከተማ አዳማ ትባላለች። በነዋሪዎቿም ዘንድ የሰምጥ ሸለቆዋ አንቱ ከተማ የሚል ቅጽል ሥም አትርፋለች።

የተቆረቆረችበት ስፍራ፣ ‹‹አሮጌ አዳማ›› ወይም ‹‹መልካ አዳማ ቀበሌ›› ይባላል። ቦታው ከ100 ዓመት በፊት የኢትዮ ጂቡቲ አሮጌው የባቡር ሐዲድ የተዘረጋበትና ዙሪያውም በአፋን ኦሮሞ ‹‹አዳሜ›› በአማርኛ ደግሞ ‹‹ቁልቋል›› የሚባል ተክል የበዛበት ነበር። ከተማዋም ስያሜዋን ያገኘችው ከዚሁ ቁልቋል ወይም አዳሚ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል።

በአሮጌዋ አዳማ ሙሰጥ በርካታ አባወራዎች ይገኛሉ። ሁሉም የሚተዳደሩት በግብርና ነው። ምንም እንኳን እንደ ምዕተ ዓመት የሞላት ብትሆንም፣ አሰካሁን ድረስ ክለ.ነክን ጨምሮ የውሃና የኤሌክትሪክ አገልግሎት የላትም። ውሃ ለማግኘት ቢያንስ እስከ ስድስት ኪሎ ሜትር ድረስ በእግር መጓዝ ግድ ይላል። ከነዋሪዎቿ መካከል ጥቂቶቹ የሶላር ብዙዎቹ ደግሞ የኩራዝ ተጠቃሚዎች ናቸው።

የአዳማ ከተማ ከተቆረቆረችበት ከፍታ ቦታ ላይ አሁን ወደምትገኝበት ዝቅተኛ ቦታ ላይ እንዴት ልትሰፈፋ ቻለች የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። እንደሚነገረው ከሆነ የዛሬ 100

ወደ ገጽ 92 ዞሯል

አትውረድ ... ከገጽ 77 የዞረ

ግን የአንበሳ መደብ አይደለም፣ አርሱ ለከተማ አልተፈጠረም፣ ከተማውን አይችልበትም፤ በግቢ ውስጥ መኖር፣ በአጥር መከለል፣ ከአንበሳው ተፈጥሮ ውጭ ነው። ስለዚህ ከሚያውቀው ወደማያውቀው፣ ከሠገነቱ ወደ ባርኔቱ፣ ከሚያሸንፍበት ወደሚሸነፍበት፣ ከሚችልበት ወደማይችልበት፣ አወደርነውና፤ በከተማ፣ ግቢ ውስጥ አሥረን አንደልባቸውን አንጪወትበታለን።

አሁን የሚፈልገውን አድኖ ሳይሆን የምንሰጠውን ይበላል፣ በፈለገው ሰዓት ሳይሆን በሰጠነው ሰዓት ይመገባል፣ ወደፈለገው ቦታ ሳይሆን ወደፈለግነው ቦታ ይሄዳል፣ የፈለገውን ሳይሆን የፈቀድንለትን ብቻ ያያል። ለምን? ወደኛ ሜዳ አውርደንዋላ፣ ሜዳውን ትቶ መኖቷላ፣››

ዝም አሉና ቀና ብለው አዩት። ቦርሳውን ወደ ላይ ገፋ ገፋ አደደረገ ይመለከቷቸዋል። እኛም መጨረሻውን ለማወቅ ጓጉተን አፍጠን አናያቸዋለን። ሰድብና ድብድብ ለማየት ተሰብስቦ የነበረው ሰውም ነገሩ ፅውቀትና ቁም ነገር ሲሆንበት ጊዜ ቀሰ በቀስ ‹‹ሼባው ነገሩን ትምሮ አደረጉት›› አደለ ከአካባቢው ሸሸ። ‹‹የሚቢቱሱ መስሎኝ ነበር፤ ሼባው አበላሸው። ስድድቡ ተመችቶኝ ነበር ›› አደሉ በቁጭት ጥለዋቸው ሄዱ።

‹‹አንተም አንደ አንበሳው ሆንክ›› አሉ ሽማግሌው። ወረድክ ከመደብህ፣ ከምትችለው የፅውቀት ክርክር ሜዳ፣ ከምታሸንፍበት የሃሳብ ክርክር ሜዳ፣ ከለመድከው የጥናት ክርክር ሜዳ፣ ወረድክላቸው። ጎበዞች ናቸው ደግሞ አድንቃቸው። አወረዱህና በሚችሉት ሜዳ ላይ በደንብ አድርገው ቀጠቀጡህ። አንተም ሞኝ ነህ በማታውቀው ሜዳ ላይ ትግል ገጠምክ።

‹‹ሶምሶን ከፍልስጤማውያን ፀቅም በሳይ ሲሆንባቸው። ፍልስጤማውያን ምን አደረጉ? በደሊላ በኩል ሶምሶን ወደማይችለው አነርሱ ግን ወደሚችሉት ሜዳ አወረዱት። በሚችሉት ሜዳ አውርደው ደኅና አድርገው ቀጥቅጠው ያንን ኃያል ሰው ወፍጮ ፈጭ አደረጉት።

‹‹ብልጥ ከሆንክ አትውረድ፣ ጀግና ከሆንክ የወረዱትን አውጣቸው።አሁን አሁን ብዙ ሰው በዚህ እየተሸነፈብን ነው። አሸኪ ጋዜጣውን፣ መጽሔቱን፣ ፌስ ቡኩን፣ ሰልፉን፣ የፖለቲካ ክርክሩንም ተመልከተው። ብዙዎቹ ከሚዳቸው ወርደዋል። ብልጠቹ ከፍ ወዳለው ሃሳብ፣ ፅውቀት ወደሚጠይቀው ክርክር፣ በመረጃና በማስረጃ ወደሚደረገው ውይይት፣ ሳቅ ወዳለ ትግል፣ ወደ ልዕልናና ወደ ሠለጠነ አስተሳሰብ ማደግ አንደማይችሉ ያውቁታል። በፅውቀትና በሃሳብ ክርክር፣ በሠለጠነና ደርዝ ባለው ትግል፣ ማንበብን፣ ማወቅን፣ መመራመርን፣ በሚጠይቅ መሥመር መጓዝ፣ ተጉዘውም ማሸነፍ አንደማይችሉ ያውቁታል።

ስለዚህ አንተን መሰል ሰዎችን ወደ ሜዳቸው ‹ውረድ አንውረድ› ብለው ያወርዷችኋል። በአነርሱ አጀንዳ፣ በአነርሱ ዕቅም፣ በአነርሱ ተራ ነገር፣ በአነርሱ አሉባልታ፣ በአነርሱ ሰድድብ፣ በአነርሱ ጠባብነትና ጎጠኝነት፣ በአነርሱ ወንዘኛነትና መንደርተኛነት፣ በአነርሱ ተረብ ይገጥሟችኋል።

ከዚያም ያሸንፏችኋል። አሁንማኮ ሁላችንንም አወረዱን፣ አንደነርሱ አንድናስብ፣ አንደነርሱ አንድንጽፍ፣ አንደነርሱ አንድንደራጅ፣ አንደነርሱ አንድንናገር፣ አንደነርሱ አንድንዘፍን፣ አንደነርሱ አንድናምን፣ አንደነርሱ አንድንለብስ አደረጉንኮ።

አትውረድ ልጄ፣ ዕውቀት ዋጋ ወደማታገኝበት፣ ሃሳብ ልዕልት ወደማትሆንበት፣ ችሎታ ወደሚያስቀጣበት አለማወቅ ወደሚያስከብርበት፣ ማፅም አለቃ ወደሆነበት፣ ክርክር ተረብ ወደሆነበት፣ ውይይት አንደ ኮካ ኮላ ጠርሙስ አንድ ዓይነት ወደሆነበት፣ አሳዋቂዎች ወደሠለጠኑበት፣ ከፅት ካለው ይልቅ አፍ ያለው ወደተሸመበት ሜዳ አትውረድ።

ከወረድክ ግን በማታውቀው ሜዳ፣ በማታውቀው ስልት፣ በወረደ ትግል ይደበድቡሃል። አትውረድ ልጄ። አትውረድ።

Do you Know you can receive DINQ in your address every month?

የመላኪያ ብቻ በመክፈል ድንቅ መጽሔትን በአድራሻም ማግኘት ይችላሉ

$25 for 6 months— $48 for 12 months

Send your address, phone number and Check to our address

"96 Pages of Knowledge"

ዲንቅ Dinq

በድንቅ መጽሔት ማስታወቂያዎች ሲጠቀሙ፤ ያገኘነው ከድንቅ ላይ ነው ብሎ መናገር አይርሱ ...

ፊደል ካስትሮ ሩዝ ...

ከገጽ 78 የዘረ

የካስትሮን ሞት ተከትሎ የሐዘን መግለጫ ልከዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያ አጋር በነበሩት ካስትሮ ሞት የተሰማውን ሐዘን ለኩባ መንግሥት መግለጹን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ገልጿል።

የአሜሪካው ተሰናባች ፕሬዚዳንት ኦባማ ‹‹ካስትሮ የሚዳኙት በታሪክ እንጂ በእኛ አይደለም፤›› ሲሉ፣ ተመራጩ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ‹‹እምባሳኒት ፊደል ካስትሮ ሞቷል፤›› ሲሉ በትዊተር ገጻቸው ማስፈራቸው ሲኤንኤን ዘግቧል።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ደግሞ ‹‹ነፃና ገለልተኛ፣ ኩባን ከአጋሮቹ ጋር የገነባ፣ የሩሲያ ታማኝ ወዳጅ፣ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተዕዕኖ ፈጣሪና ለሌሎች አገሮች አርአያ የሆነ የአንድ ክፍለ ዘመን መሪ፤›› ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

የሜክሲኮው ፕሬዚዳንት፣ ‹‹የሜክሲኮ ጓደኛ፣ የሁለትዮሽ ግንኙነትን በመከባበርና በንግግር ያሰፈነ መሪ፤›› ሲሏቸው፣ የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ‹‹ፊደል ካስትሮ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ፊርጥ ነበር። ህንድ ታላት ጓደኛዋን በማጣቷ እዝናለች፤›› ብለው በትዊተር ገጻቸው ማስፈራቸውን አሶቪየትድ ፕሬስ ዘግቧል።

የቫቲካን ሲቀ ጳጳስ ፍራንሲስ ለፕሬዚዳንት ራውል ካስትሮ በላኩት ቴሌግራም ለቤተሰቡ መፅናናትን ሲመኙ፣ የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዲዮ፣ ‹‹ታሪክ የማይረሳው አንደበተ ርቱዕ፤›› ብለዋቸዋል። የጆይናው ፕሬዚዳንትን ጂንፒንግ በበኩላቸው፣ ‹‹በዓለም ለሶሻሊዝም ዕድገት ታሪክ የማይረሳው አስተዋጽኦ ያደረገ መሪ፤›› ማለታቸውን ሲሲቲቪ ዘግቧል።

የቬንዙዌላ ኪንግያም ሌበር ፓርቲ መሪ ጀርሚ ኮርባይን፣ ‹ካስትሮ የሕይወታችን ትልቅ ነፀብራቅ ነው፤›› ማለታቸውን ቢቢሲ አስፍሯል።

ኮርባይን እንደሚሉት ካስትሮ የቱንም ያህል ስህተቶች ቢኖሩባቸውም፣ ከደቡብ አፍሪካ አፓርታይድን ለማስወገድ በነበራቸው ወሳኝ ሚና፣ አንዲሁም ማኅበራዊ ፍትሕን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስፈን ባበረከቱት አስተዋጽኦ ሁሌም ዓለም እንደማይረሳቸው ተናግረዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቦሪስ ጆንሰን ደግሞ፣ ‹‹እከራካሪ ሰው ቢሆንም ታሪካዊ ነው፤›› ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

‹‹የፊደል ካስትሮ ሞት የኩባ የረዥም ጊዜ አገዛዝ ማብቂያና ለኩባውያን አዲስ ሕይወት መጀመርያ ነው፤›› ሲሉም ጆንሰን አክለዋል።


አ.ኤ.አ. ነሐሴ 13 ቀን 1926 በብሪያን ኩባ የተወለዱት ካስትሮ፣ የ6 ዓመት ሕፃን ላሉ ነው ሳንቲያጎ ከሚኖሩ መምህራቸው ጋር አንዲኖሩ የተላኩት። በሰምንት ዓመታቸው በካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተጠመቁት ካስትሮ አ.ኤ.አ. በ1945 የሐቫና ዩኒቨርሲቲን አስከተቀላቀሉ ድረስ ልዩ ትኩት የሚሰጡት ለስፖርት እንደነበር ይነገራል።

ቢሐቫና ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍልን ሲቀላቀሉ የተጀመረው የፖለቲካ ሕይወታቸው ብዙ ፈተናን አስተናግዷል። በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት ለመሆን ካደረጉት ያልተሳካ ቅስቀሳ ጀምሮ በኩባ ፍትሕ እንዲሰፍንና ሙስና እንዲጠፋ የታገሉት ካስትሮ፣ አ.ኤ.አ. በ1946 በኩባ ስለተመራው ሙስናና በወቅቱ አገሪቱን ይመሩ የነበሩት ራምን ግራውስ መንግሥት ሥርዓት አልበኝነት የተናገሩት የብዙ ጋዜጦች የፊት ገጽ ሽፋን አግኝቶ ነበር። በኋላ ላይ በሽምቅ ውጊያ ባቲስታን ገልብጠው የፖለቲካና የመቃደራዊ ሥልጣኑን መቆጣጠር ችለዋል።

ከዩኒቨርሲቲ ሕይወታቸው ጀምሮ አሜሪካ በካሪቢያን ያላትን ጣልቃ ገብነት ሲነቅፉ የነበሩትና እ.ም.ፔሪያሊዝምን የሚያወግዙት ካስትሮ፣ በኩባ የሶሻሊዝም ኑድፈ ሐሳብን የተገበሩ መሪ ነበሩ። በአቋማቸው በምዕራባውያኑ ብዙም ተቀባይነት ያልነበራቸው ካስትሮ ለ47 ዓመታት በነበራቸው የሥልጣን ቆይታ በዓለም ተዕዕኖ ፈጣሪ ለመሆን በቅተዋል።

አኘህ ዓለም የማይዘነጋቸው አብዮታዊ መሪ የ11 ልጆች አባት የነበሩ ሲሆኑ፣ በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።!!!





ጠበታ ማር

የአባትህን ጠላት አግኝተኸዋልና በርታ አትልቀቀው!

አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የካ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል አንድ ካህን ንባብ አይችልም ነበርና እርሱ ማንበብ ሲጀምር ‹‹አንዲህ በል አንዳበል›› የሚል መላሽ በመብዛቱ ሲቸገር ይኖር ነበር። ነገር ግን አንድ ወንድ ልጅ ነበረውና ንባብ ቤት አስገብቶት በርቱዕ አንደበት ንባቡን ሲለበልው የሰሙ አንድ መምህር ‹‹ይህ ንባብ አዋቂ የማነው ልጅ?›› ብለው ጠየቁ። ‹‹የመምሬ እከሌ ልጅ ነው›› ሲሏቸው ተገርመው ‹‹ለካ መምሬ እከሌም ይህን የመሰለ አሳት የላለው አንባቢ ልጅ ወለደ አንዴ?›› ብለው በመደነቅ ‹‹አንተ ልጅ በርታ ያባትህን ጠላት አግኝተኸዋልና ለብልበው›› ሲሉ አበረታቱት ይባላል። አንግዲህ ያ ዓይነቱ ጥሩ አንባቢ በዘመናዊ ትምህርት ከገፋበት ደራሲና የሬዲዮ ጋዜጠኛ መሆን የማይችልበት ምክንያት አይኖርም።

ሌላው ካህን ደግሞ አንደዚሁ የንባብ ችሎታ የሌለው ሆኖ በድፍረት ለማንበብ ሲቀርብ ‹‹አንዲህ በል አንዳበል›› የሚል መላሽ በዝቶበት ቅኔ ማኅሌቱ ሲተራመስ በትዝብት የተመለከተች ሚስቱ ‹‹አንተ ስታነብ ይህን ያህል መላሽ የሚበዛበት ምክንያት ምንድን ነው?›› ብላ ብትጠይቀው ‹‹ሴላ አይምሰልሽ አነርሱ የማያውቁትን አዲስ ቀለም እያመጣሁባቸው ተቸግረው ነው›› አለ ይባላል።

-መክብብ አጥናው ‹‹ሁለገብ የአእምሮ ማዝናኛ›› (2005)

ቤት ሠሪው ግምበኛ

አንድ ግማሽ ቤት ሠሪ ግምበኛ ወደ ቀጣሪው ኮንትራክተር ሄደና ቀሪ ዘመኑን ከቤተሰቡና ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ዘና ብሎ በአረፍት ለማሳለፍ ጡረታ መውጣት እንደሚፈልግ ይነግረዋል። ለረጅም ጊዜ የቆየው ብርቱ ሠራተኛው ሊለየው በመሆኑ ኮንትራክተሩ እዘነ። ጡረታ ከመውጣቱ በፊት ግን አንድ የመጨረሻ ቤት ብቻ እንዲያንጽለት ለመነው።

ሽማግሌው ቤት ሠሪ ፈቃደኛ ቢሆንም አንደ ቀድሞው ልቡ በሥራው ላይ ሊሆን ባለመቻሉ ርካሽ የግንባታ ቁሳቁሶች በመጠቀም ከቀድሞ ሥራው የወረደና አዚህ ግባ የማይባል ቤት ሠራ። አንዳለመታደል የረጅም ጊዜ የሥራ ዘመኑን በዚህ መልክ ጨረሰ።

ሽማግሌው ቤት ሠሪ ቤቱን ሠርቶ አንደጨረሰ ኮንትራክተሩ የተሠራውን ቤት ሊጐበኝ መጣ። የቤቱን መግቢያ ቁልፍ ለሽማግሌው ቤት ሠሪ አስረከበውና፣ ‹‹ቤቱን እንድትሠራልኝ የለመንኩህ ላንተው ነው! ለረጅም ጊዜ አገልግሎትህ የማበረክትልህ ስጦታዬም ይኼ ቤት ነው!›› አለው።

ምንኛ አስደንጋጭ ነው! የገዛ ቤቱን አየሠራ መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ በምርጥ የግንባታ ቁሳቁሶች በሠራው ነበር። በእንዳንድ አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ምርጥ ችሎታችንን በሥራ ላይ አናውልም። አኛው የፈጠርነውን ሁኔታና አሁን የምንናኖርበትን የሠራነውን ቤት ስንመለከት ግን አንደነግማለን። ራሳችንን በሽማግሌው ቤት ሠሪ ቦታ አስኪ አናስቀምጥ፤ ስለ ቤታችንም አናስብ። ሕይወት ራሷ በቤት አንደምትመሰልም አንዘንጋ። ሚጨድ ኩሶፈቀደልን የምናጭደው የዘራነውን ነው.....

-ኃይል ከበደ ‹‹ጉርሻ አና ፈሽታ›› (2006)

የመታወቅ ጥማት

በየትኛውም ዘመን የሰው ልጆች የመታወቅ ጥማት አላቸው። የጥንቱን የሰናዖር ግንብ ስናስብ የሰው ልጆች ለስማቸው ማስጠሪያ የገነቡት ነበር።

በአገራችንም፦ ‹‹ልጅ የወለደና ግንብ ቤት የሠራ ዘላለም ይኖራል ስሙ አንደ ተጠራ›› ይባላል።

ሰዎች አንጻ ለመገንባት፣ ልጅ ለመውለድ የሚያስቡት ስማቸው አንዲጠራ ለሆን ይችላል። ብዙዎች ነገን የምናረው በልጄ ነው ይላሉ። ዛሬን አነርሱ ሳይኖሩ ነገን በልጃቸው ለመኖር ያስባሉ። አነርሱ ያልሠሩትን ልጆቻቸው የሚሠሩት ይመስላቸዋል። ልጅ አነርሱን አንደሚመስል አይገነዘቡም።

ካለፉት ዘመናት ይልቅ በዚህ በአኛ ዘመን ሰዎች የመታወቅ ጥማታቸው ከፍ ያለ ነው። መታወቅ ጥማት ብቻ ሳይሆን የብዙዎችም ፈተና ሆኗል። ታላላቅ ሰዎችን በማስናከል መታወቅ የሚፈልጉ፣ ከታላላቅ ድልድዮች ላይ ራሳቸውን በመወርወር ስማቸውን ለማስጠራት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። ኖረውና ሠርተው መታወቅ ቢያቅታቸው ሞተውና አበላሽተው ለመታወቅ የሚፈልጉትን ሰዎች ስናስብ ዘና የዘመናችን ትልቁ ፈተና አንደሆነ አንረዳለን። በዚህ ዓለም ላይ ርእስ የምንሆነው ለጥቂት ጊዜ ነው። ከዚያ በኋላ አንረሳለን ወይም ስንውቀስ አንኖራለን።

[redacted]

ጠቃሚ ስልኮች አትላንታ
Important numbers ATL

Eth. Community Asso. ATL	404 298 4570
Ethiopian Embassy	202 364 1200
US embassy in Ethiopia	124 24 24
Spiritual Places:	
Sealite Mihret Church	770 469 5466
Saint Michael Church	404 456 6499
Saint Gabriel Church	404 221 1717
Bisrate Gabriel Church	404 508 1330
Debre tsion Mariam church	770 899 0269
Abune GebreMenfes Kidus	770 979 1380
Kidist Sellasie EOTchurch	678 467 3905
Ethiopian Catholic Community	404 751 7375
Evangelical Church	770 496 1665
Life Gospel Ministry	404 444 3814
Rehoboth Ethiopian Church	770 879 2440
Hijira Islamic community	404 297 1942
Media:	
Mahderc Andenet Radio	404 603 8770
Voice of Ethiopia Radio	404 787 2010
Admas Radio	404 929 0000
Eth.Community Radio	404 748 9219
Dinq magazine	404 929 0000
Air Lines:	
Ethiopian Air lines	1800 445 2733
Lufthansa	800 645 3880
Hartsfield Airport	404 530 6830
Delta Air Lines:	800 221 1212
Air Tran:	800 AIR TRAN
Hotels:	
Hilton	800 445 8667
Marriot	800 228 9290
Hyatt	800 233 1234
Holiday Inn	800 465 4329
Westin	800 937 8461
Transport (Local)	
MARTA (bus & train)	404 848 4711
Cobb Country transit:	770 427 4444
Area Attractions:	
World Coca – Cola :	404 676 5151
Underground Atlanta:	404 523 2311
Fox Theatre:	404 881 2100
Atlanta Zoo:	404 624 5600
Six Flags over Georgia:	770 739 3400
Stone Mountain Park:	770 498 5690
Georgia Dome:	404 233 8687
Georgia Aquarium	404 581 4000
DEKALB county business directory	
I R S	1800 829 3676
Trade name	404 371 2250
Zoning and Permit	404 371 4915
Business licensc dcpt.	404 371 2461
Health dcpt.	404 508 7900
GA sales tax	404 417 4490
GA info linc	404 656 2000
Emergency:	911
Weather Service	770 486 8834

ወደ ሙት ባህር ሄድን

ሙት ባህር ከጊዜ በኋላ የተሰጠው ስም እንጂ ጥንታዊ ስሙ የጨው ባህር ነው። በአረብኛው "አል ባህር" "አል ማይት" ይሉታል።

በመሰቀል ጦርነት ጊዜ "የዲያቢሎስ ባህር" ይሉት ነበር። "የሰዶም ባህር" "የሎጥ ባህር" ሲባል ብትሰሙ ይህም ሙት ባህር ማለት ነው። የጨው ባህር ዮርዳኖስን ከእስራኤል ጋር ያዋስናታል። ባህሩ በጥልቀቱ 377 ሜትር ስለሚለካ ከዓለም ጥልቅ ባህሮችን ቀዳሚው ነው። ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው ርዝመቱ 55 ኪሎ ሜትር ሲሆን በጎን በኩል ሰፊው ቦታ 18 ኪሎ ሜትር ይሆናል። ፀጥ ብሎና ተረጋግቶ ከዳር ቆመው ሲያዩት የሰማይ አንዱ ክፍል ተሰብሮ የወደቀ ይመስላል።

የጨው ባህርን መፅሀፍ ቅዱስም ቅዱስ ቁርዓንም ከሰው ልጅ መፈጠር ጀምሮ ያለ ያደርጉታል። በሙት ባህር የሚታመሱ ታሪካዊ ድርጊቶች ተፈፅመውበታል። አብርሃም ግዙፍ ፍልሚያዎች አካሂዶበታል፤ ንጉስ ዳዊት ከሳኦል በሸሸ ጊዜም የተደበቀው እዚሁ አካባቢ ነበር። ነብዩ ሕዝቅኤልም ሕልም ያየው በቀይ ባህር አካባቢ ነው። ተመራማሪዎች በትነትና በመጋቢ ውኃዎች ማነስ ወደፊት ያንሳል ወይም ይደርቃል ቢሉም አማኞች ግን እስከ መጨረሻው ምልክት ሆኖ እንደሚቀር ይናገሩለታል።

የጨው ባህር ከመሬት ወለል በታች 416 ሜትር ዝቅ ይህም ሕይወት ያለበት ከዓለም ዝቅተኛው ቦታ መሆኑ ነው። የጨው ባሕር ስያሜውን ያገኘው ጨው በመሆኑ ነው። በሰሩም ሆነ በዳርቻው የጨው ክምር ታያላችሁ። በጣታችሁ ነክታችሁ ብትቀምሱት በአንድ ስኒ ውስጥ አራት የሻይ ማንኪያ ጨው የገባበት ውሃ ያህል ይሸመጥራችኋል።


የጨዉ ብዛት በባህሩ ውስጥ ገብቶ በደረትም ሆነ በጀርባ ተኝቶ ቢዋኙ እያሰምጥም። እኔ ራሴ በባህሩ ውስጥ በጀርባቸው ተንጋለው እየተንሳፈፉ ጋዜጣ ሲያነቡ አይቻለሁ። በሙት ባህር ያሉ

ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ..

ከገጽ 39 የዞረ

ማዕድኖች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ተዋሳኝ አገሮቹ ለኢንዱስትሪያቸው ጥሬ ሀብት ማግኛ አድርገውታል። ሙት ባህር የዚያ አካባቢ ታሪክ ብቻ ሳይሆን መጠቀሚያም ጭምር ነው።

የዮርዳኖስ ዜጎች ዋናው የአርብ የሣምንት መዝናኛቸው ሙት ባህር ነው። በርካታ ዮርዳኖሳውያን አርብ ዕለት ከንግዘ ጀምረው ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ወደ ሙት ባህር ዳርቻዎች ይጓዛሉ። በየዳርቻዎቹ ተሰባስበውና ምንጣፎቻቸውን አንጥፈው ግለቱ



የማይበርደውን የሙት ባህር ፍቅራቸውን ይወጣሉ። በሙት ባህር ዳርቻ ሆነው ሲጋራቸውንና ሽሻቸውን እያጨሱ በደስታ ባህር ይሰምጣሉ። መቸም ማጨስ ለዮርዳኖሳውያን ልዩ መለያ ሳይሆን አይቀርም። አነሱም ቢሆኑ በአጫሽነታቸው ይኮሩበታል። "እኔ እኮ ዮርዳኖሳዊ ነኝ" ይላል አጫሽነቱን ለመግለፅ።

የሙት ባህር የተለያዩ ደዌዎች ፍቱን መድሃኒት ተደርጎ ይቆጠራል። የዝሆኔ፣ የቁርጥማትና የቆዳ በሽታን ለመፈወስ፣ ፊትን ለማጥራት የሙት ባህር መድሃኒትነት ከጥንት ጀምሮ የታወቀ ነው። ጎብኚዎችና ተዝናኚዎች በውሃው መነከር ብቻ አይበቃቸውም። ስቆዳ መልካም ነው ስለሚባሉ ጭቃውን ከአግራቸው እስከ ግንባራቸው ተቀብተው ለሰዓታት ይቆያሉ። ፀሐይ ስታርፍበት የኮከብ ቅርፅ የሚሰራውን ነፀብራቅ ከሰማዩ ቀለሙ ጋር አያዩ መደሰትም ሌላው መዝናኛ ነው። እኛም ወደ ባህሩ ዳርቻ ተጠግተን ይህንን ሁሉ አየን።

ከሙት ባር በምዕራብ በኩል ሙጥጥ ያለ ዝንጀሮ አንኳን አትወጣውም የሚባል አይነት ገደል ነው። በገደሎቹ ያሉ ውሃ መውረጃዎችም በሙሉ ከታሪኩ ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ኢያን ደጋግሞ ነግሮናል።

የሰዶምና ገሞራ ከተሞች ነበሩበት ወደተባለው ቦታ ደረስን። ሰዶምና ገሞራ በአብርሃም ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2013 ዓ.ዓ ነበሩ።

ነዋሪዎቻቸው የሚፈነጥዙበት፣ አስረሽ ምቺው የሞላባቸው፣ ጭፈራ የደመቀባቸው ከተሞች ነበሩ። ይህም ጥጋብ ሲሰዘ የሚሰሩትን ያሳጣልና የሰዶምና ገሞራ ሕዝቦችም ፈጣሪያቸውን የሚያረሳ ቀማኛነትና ነውረኛ የዝሙት ምግባር ፈፀሙ። የአብርሃም የወንድም ልጅ ሎጥ ንብረቱንና ቤተሰቡን ከአገቱ ተካፍሎ በዚያች እኛ በቆምንባት አካባቢ በነበረችው በሰዶም ከተማ ይኖር ነበር።

"ሰዶማውያን ነውረኛ ተግባር እየፈፀሙ ሲያስቸግሩ ፈጣሪያቸው ሊያጠፋቸው በወሰነ ጊዜ ሎጥን ከነቤተሰቡ ከዚያች ከተማ አስወጣው" ይላል። መፅሀፍ ቅዱስ። የፈጣሪያቸው መልዕክተኞች ሚስቱንና ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ከከተማ አወጡለት። "ራስህን አድን፣ ወደኋላ እትይ፣ ወደ ተራራው ሽሽተህ አምልጥ" ብለው አዘዙት። "ከዚያም በኋላ የሰዶምና የጎመራ ከተሞች ከሰማይ የእሳት ዱን አዝንቦ በውስጣቸው ያለውንም በዙሪያቸው ያለውን ሁሉ የታቹ ወደላይ፣ የላዩ ወደታች አስኪሆን ገለባበጣቸው።

የሎጥ ሚስት ግን አልቻለችም፣ ሳይቸግራት ወሬ አያለሁ ብላ ዞራ አየች፣ ወዲያውም የጨው ሐውልት ሆና ቀረች" ይላል ቅዱስ መፅሐፍ። እኛ እዚያ የደረስነው ከዚህ ሁሉ መሞት ብዙ ዓመታት ቀይቶ ነውና ከተማ ሊያሰኝ የሚችል አንዳችም ቅሪት አላየንም። የጨው ሐውልት ሆና ቀረች የተባለችውን የሎጥ ሚስት ምልክት ግን አይተናል። በገደሉ ጫፍ ላይ የሚታየው የሀውልት ቅርፅ የሰው ምስል ይመስላል። ካመኑበትም የሴት ምስል ሊመስል ይችላል። ሐውልቱ


ወደ ገጽ 91

ከአንገቱ በላይ ወደ ኋላ ዘርጋል። አስተርጓሚያችን ኢያን "ይህቺ የጨው ሐውልት ሆና የቀረችው የሎጥ ሚስት ናት" አለ።

የራሱ የሎጥ መቃሰቢያው ጠፍቶ ሰዶምና ገመራ ተገለባብጠው የሎጥ ሚስት ስሟ እሰካሁን ይነሳል። ዛሬም የአሷን ስም የያዘ ድንጋይ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ያየዋል። ዛሬም ምልክቷ በገደል ጫፍ ላይ ሆኖ በሩቁ ይታያል። በዚህ ምክንያት የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ሆና ትቅር አንጂ ስሟ ግን ለዘላለም ኖሯል።

ሎጥስ የት ገባ? እየተከታተልነው ነው።

ሎጥ ያንን ሁሉ መዓት ሸሽቶ ወዳመለጠበት ወደ ዙሃር ተራራ ገሰገሰ። የሙት ባህር ደቡብ ዳርቻ ስንደርስ ወደ ግራ ያለውን ተራራ ግማሽ ያህል መውጣት



ወልዶ ዘሩን አስቀረ። ያ ዋሻ ሎጥና ልጆቹ የተክለሰበትና ልጆች ያፈሩበት መሆኑ የታወቀው በኋላ ነው። በአምስተኛው ክፍለ ዘመን አንደሆነ ተገምቷል። በዚያው ቦታ ቤተ ክርስቲያን ተገንብቶ አንደነበረ በተመራማሪዎች ተረጋግጧል፤ አውንም ፍራሹ ይታያል፤ ማስረጃዎችም ተገኝተዋል። ዘግይቶ በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኑ ጨርሶ ወድሟል።

ከዋና ከተማዋ 120 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው የሎጥ ዋሻ በሚገኝበት ሳያል አልሳፉ በሎጥ ስም የተሰየመ አዲስ ሙዚየም ተሰርቷል። ዕለቱ አርብ

ደጃፉም፤ የሙስጥ ክፍሎቹም ተለይተው ይታያሉ። ትንሽ ቢሆንም ውሃ አለው። ያ ዋሻ በኋላ የቅዱስ ሎጥ የተባለ ቤተ ክርስቲያን ተሰርቶለት ስለነበረ አሁን በአብዛኛው የሚታየው የቤተ ክርስቲያኑ ፍራሽ ነው።

የሎጥ መኖሪያ በኋላም በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ተሰራ በተባለው ቤተ ክርስቲያን በሞዛይክ የተሰሩ ቅርጾችና ፅሁፎች ይታያሉ። ተመራማሪዎች በቦታው ቁፋሮ አካሂደው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ3300 አስክ 3000 ሺህ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ቁሳቁሶች አግኝተዋል።

ተመራማሪዎች እነዚህ ሁሉ ምልክቶች ያ ዋሻ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2013 የነበረው የሎጥ ዋሻ መሆኑን መገመት አስችሏቸዋል።

ምሽት እየሆነ ነው፤ ፀሀይ በማታ ቀለሟ የሙት ባህርን ደም ተነከረ አስመሰለችው። በዳሩ እየቃከከን ወደ አማን መመለስ ጀመርን። ወደ አማን ከፍታ በወጣን ቁጥር የዮርዳኖስ ወንዝና ሙት ባህር እየሸሹ ከኋላችን ተሰወሩ።

የታሪክ ሽበት ያጎለበታቸውንና ያወረዛቸውን፣ ተዓምራት ግርማ ሞገስ የሰጣቸውን ቦታዎች በማየታችን በደስታ ሰምጠን፣ የዮርዳኖስ ውሃ ጭኑን ወደ ነጫጭ ክተማ ወደ አማ ተመለስን። በማግስቱ ተፈጥሮ ውበቷን ወዳሳየችበት ወደ ፔትራን እንሄዳለን። ገደል እንደ አክርማ



ነበረብን፤ ዳገቱ ቀጥ ያለ ነበር፤ ግን አንሸራታች ይሁን እንጂ አስከተወሰነ ድረስ መንገድ ተሰርቶለታል።

ሁለቱ ከተሞች ሰዶምና ገሞራ ጨርሰው እንዲወድሙ ሲፈረድባቸው መልካም ሆኖ የተገኘው ሎጥ ወደ ዙሃር ሄደ። ምናልባትም እኛ በሄድንበት መንገድ ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ይዞ ዋሻ ገባ፤ መሄጃም አልነበረውምና ከልጆቹ ጋር በዚያች ዋሻ ቆየ፤ በዚያ ዋሻ ከሁለቱ ሴት ልጆቹ በሰተቀር ሌላ ሰው አልነበረም፤ ስለዚህ በልጆቹ አሳሳቢነት ከሁለቱም ሴት ልጆቹ

በመሆኑ ስለተዘጋ አላየሁትም። ግን ኢያን እንደነገረኝ የሎጥ ሙዚየም በዋሻው የተገኙ ዕቃዎች ይታዩበታል። የሎጥ ዋሻ ወደሚገኝበት ድረስ ቀጥ ያለ ዳገት መውጣት ያስፈልጋል። ደግነቱ እስክ ዋሻው ድረስ ደረጃ ተሰርቶለታል። 350 የሚሆኑት ደረጃዎችን ወጥተን ከሎጥ ዋሻ መግቢያ ደርሰናል።


በዋሻው ደጃፍ ላይ ሆነን ወደ ምስራቅ የሚታየው ገደል ነው፤ ወደ ምዕራብ ሙት ባህር ተንጣሏል፤ በሙት ባህርና በተራራው ጥግ መሃል ለም የአርሻ መሬት ይታያል። በሎጥ ዋሻ

የሰዶማውያንና የገሞራውያን መገልገያ ሊሆኑ ይችላል የሚል ግምት አሳድረዋል።

በዋሻው መግቢያ ላይ የተለያዩ ቀለማት ባላቸው የሞዛይክ ጠጠሮች ተሰርቶ በግሪክ ፊደል የሚነበበው ዕውፍ ታላቅ ግኝት ሆኖ ተቆጥሯል። ፅሁፉ የጊዜው ጳጳስ ክርስቶፎር መሆኑን፣ አገረ ገዢው የራቢዮስ ልጅ አዳሚስ መሆኑን፣ የተቀደሰ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ተሰፍሮበታል። ይህ የሞዛይክ ፅሁፍ በ683 ዓ.ም የተሰራ መሆኑን አዚያው ላይ ተገልጿል። በየጊዜው ወደ ሎጥ ዋሻ ሄደው ያጠኑ

ተሰንጥቆ ጥበብ ወደሚታይበት ፔትራ፤ ስምንተኛው አስደናቂ ታሪክ ሆኖ ይመዝገብ አየተባለ አሰጥ አገባ ሙሳት ወደ ተገለመበት ፔትራ፤የተዋጊዎችን የብርታት ታሪክ ወደተመለከተው ፔትራ፣ አንሄዳለን።





ዓመት ከፍታ ቦታ ላይ ከሚገኘው አሮጌው አዳማ ውስጥ በተዘረጋው ሃዲድ በመጓዝ ላይ የነበረ የባቡር ፋርጎ ተበጥሶ ቁልቁለቱን ይወርድና ለገሃር ይቆማል። ከዚህ በኋላ ለምን ከተማዋን በዚሁ ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ አናደርጋትም ተብሎ አሁን በምትገኝበት ቦታ ልትሰፋፋ ቻለች።

በአሮጌዋ አዳማ ወይም በመልካ አዳማ ቀበሌ ነባሩ ሃዲድ ከተዘረጋ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ቤቶች አውንም አንዳሉ ሲሆን፣ ይህም የቱሪስት መስህብ ሆኖ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግም እንደሚረዳ ይታመናል።

በዚች ከተማ በአንድ ጊዜ 80 ሺህ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም ያለው ዘመናዊ ስታዲየም ለመገንባትና የከተማ መናፈሻ (ሲቲ ፓርክ) ለማቋቋም ታቅዷል። ለዕቅዱም እውን መሆን የስታድየሙና የመናፈሻ ዲዛይኖች ተሰርቷል። ለስታድየሙ ግንባታ የሚውል 33 ሄክታር መሬትም ተዘጋጅቷል።

ስሜትና ፍላጎት አለኝ የሚሉ ወጣት ድምፃዊያን የመፈተኛ ሙዚቃና ምርጫቸው የአስቴር ሙዚቃዎች ናቸው።

የዘፈናኛ ተወዳጅነት በአድሜ ክልል አይወሰንምና አራት ትውልዶችን እንደሰንሰለት አስተሳስራ ወደ እምስትኛው ትውልድ በመንደርደር ላይ የምትገኝ ድንቅ አርቲስታችን ነች። አስቴር ጎበዝ ተማሪም ነበረች። የሰድስተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና 100ፐርሰንት አምጥታ ስታልፍ ወላጆቿ ምን እንደሚመኙላት መገመት አይከብድም። ነገር ግን የሷ ጥሪ ሙዚቃ የሷ ጥሪ ዘፈን ነበርና የልቧን ጥሪ ተከትላ መጀመርያ የሄደችው እነ ንጋቷ ከልካይን ፣ እነ አሮኤል የሀንስን ፣ እነ ሸሸግ ቸኮልን ፣ እነ አሰፋ አባተን ፣ እነ ጥላሁን ገሰሰን እንዲሁም ሌሎች ታዋቂ አርቲስቶችን ወዳፈራው ወደ ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ነበር ። እዛም ፈተናውን በሚገባ አልፋ በድምፃዊነትና በተወዛዋዥነት በመቀጠር የተወሰነ ዓመት ካገለገለች በኋላ በተለያየ የሙዚቃ ባንዶች ጋር የተለያየ ሆቴል ውስጥ የሰራች ሲሆን በተለይ ከሸበሌ ባንድ ጋር በሸበሌ ሆቴል ውስጥ ሆና ታዋቂነት አትርፋለች።

በመቀጠልም ባህር ተሻግራ በሀገረ አሜሪካ ቷሚ መኖሪያዋን በማድረግ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ስራዎቿን በማቅረብ በርካታ የሀገር ውስጥና የባህር ማዶ አድናቂዎችን ያፈራች ሲሆን አድናቂዎቿ ከታዋቂዋ አሜሪካዊት የሶል ሙዚቃ አቀንቃኝ አሪታ ፍራንክሊን ጋር ያመሳስሏታል።



ብርቅዬዋ አርቲስታችን በሙዚቃ ቆይታዋ ከ20 በላይ የሙዚቃ ካሴቶችን በማሳተም ከ200 በላይ ሙዚቃዎችን ለአድማጮች አቅርባለች። በተለይ ከአመታት በፊት የድሮ ካሴቶችን በአዲስ አሬንጅመት በማቀናበር ካሳተመች በኋላ እንደገና በአድናቂዎቿ ዘንድ መነቃቃትን በመፍጠር ድምፀዋ እና ስራዎቿ እያደር እየጣፈጠ በመምጣት ዘመን ተሻጋሪ መሆኑን አስመስክራበታለች።

አስቴር ከድምፃዊነቷ ባሻገር የዜማ እና የግጥም ደራሲም ነች። በዚኖቿ ለብዙዎች ፍቅርን በጅር እንደማንሸካሸክ ያሀል በቀጥታ ወደ ልብ ሰርስሮ በሚገባ መልዕክቶችን በሚያስተላልፍ ቅብጥ በምታደርገው ድምፃ እየደባበሰች ከወደማይታወቅ ጥልቅ የፍቅር ባህር ውስጥ የሚያሰጥም አንዳች መግነጢሳዊ ሀይል በመፍጠር የተለያዩ ትውልዶችን የፍቅር ምጥ አዋልዳለች ጥንዶችን በፍቅር አስተሳስራ ለወግ ማዕረግ አብቅታለች።

በተለይ ከሀምሳዎቹ ወዲህ ያሉት ትውልዶች ለዚህ ምስክር ናቸው። በአንድ ወቅትም 'የአስቴር ዘፈን የመድሀኒት ፋርማሲ ውስጥ ነው መሸጥ ያለበት" የተባለበትም ዘመን ነበር።

ከዚህም በላይ አስቴር ሀገሯን በጣም ትወዳለች ፤ በአያንዳንዱ የሙዚቃ አልበሞቿ ውስጥ አንድ ስለሀገሯ የሚያወሳ ሙዚቃ ያልተጨመቀችበት ካሴት ትዝ አይለኝም። አስቴር በተለያየ ትልልቅ የሙዚቃ መድረኮች ላይም የሀገሯን የባህል ልብስ ሳትደምቅ ወደ መድረክ አትወጣም ። በአንድ ወቅት ለአንድ ጋዜጠኛ እንዲህም ስትል ተናግራለች...

" እኔ መድረክ ላይ ስወጣ የሀገሬን የባህል ልብስ ሳልብስ ከወጣሁ ባዳነት ይሰማኛል " ብላም ነበር። አስቱካ የመጀመርያ አልበሟን ከታዋቂው ዘፋኝና የጊታር ተጫዋች ከውበሸት ፍሰሀ ጋር በጊታር ታጅበው በታንጎ ሙዚቃ ቤት ለአድማጭ አቅርበዋል። በዛ የሽክላ አልበም ውስጥ "የሰራ ልብስሽ" ፣ "የኔ ነህ ወይ" ፣"ሎሚዬ ሎሚዬ" አንዲሁም ሌሎች ዛሬም ድረስ የሚደመጡ ሲሆን ።

"ካቡ" የሚሉው ዜማዋ አለም አቀፍ ዝናና ተደማጭነትን ያተረፈላት ቢሆንም እንደ አፍሪካዊቷ አቀንቃኝ ሎሞ ሳንጋሪ አንዲሁም ሌሎች ቀጣይነት ያለው አለም አቀፍ ስራና ታዋቂነትን አለማግኘቷ የሚያስቅጭ ጉዳይ ነው።

አናም በመጨረሻ አስቴር ረጅም የሙዚቃና የስኬት ዘመን እየተመኘሁ የምንወደውን የፍቅር ዜማዎቿን በምንወዳት ቅዳሜ እየተገባበዛችሁ የፍቅር ጊዜ ትዝታችሁን እየገረባችሁ መልካም የአረፍት ጊዜን አመኛለሁ።

[ስአደም ሀሴን[

አስቴር አወቀ በጨረፍታ

የዛሬ 30 ዓመት ገደማ በሀገር ፍቅር ትያትር ቤት ድምፃዊ ለመሆን ለትፈተን ሶስት ሙዚቃዎችን ተጫውታለች የብዙኀሽ በቀለን የሂሩት በቀለንና የሙሉቀን መለሰን ዜማዎች ፤ ዛሬ በተራዋ አሪፍ ድምፃዊና የሙዚቃ

ዜና ብልጭታ

ከገጽ 50 የቀጠለ

ሲዳሞ ያደጉት አቶ ተሾመ ፤ ማለደን ከሀገራችን በወጣ በአመቱ ነበር ትምህርት የጀመሩት ። በ1937 ጃንሆይ ሲዳሞን በነበኙ ጊዜ 10 ልጆችን ወስደው ለማስተማር ፈልገው ነበር ። ከእነዚህ ተማሪዎች መሃልም ታዳጊው ተሾመ አንዱ ነበሩ ። ታዳጊው ተሾመ አዲስ አበባ መጥተው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገቡ ። አቶ ተሾመ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ያሳለፉት ዘመን ለቀሪ የህይወት ዘመናቸው ትልቅ መሰረት እንዳሰቀመጠላቸው ያምናሉ ። ከአራተኛ እስከ 12 ክፍል ድረስ በተፈሪ መኮንን ያሳለፉት አቶ ተሾመ ብዙ ትዝታ አላቸው ።

ጠላት አገራችንን ወርሮ ነጻ በወጣን በ9 አመቱ ሀገራችን የኒቨርሲቲ ለመክፈት ላይ ታች ትል ነበር ። ያኒም ተፈሪ መኮንን ፤ ከጄኔራል ዊንጌት ፤ከዳግማዊ ምኒሊክ ክሌሎችም የተውጣጡ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አንዲገቡ ተደርጎ ነበር ። አብዛኛዎቹ ከተፈሪ መኮንን ነበሩ ። ከተፈሪ መኮንን በጊዜው ወደ ዩኒቨርሲቲ የገቡ ተማሪዎች ቁጥር 72 ይጠጋ ነበር ። ከነሱ አንዱም አቶ ተሾመ ነበሩ።

አቶ ተሾመ የህግ ትምህርታቸውን በካናዳ የተማሩ ሲሆን በጃንሆይ ዘመንም የማእድን ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር በመሆን አገልግለዋል ።

ከ1967-1975 ድረስ ለ 8 አመታት በደርግ ዘመን የታሰሩት ጋሽ ተሾመ ከተፈቱ በሁዋላ የጥብቅና ፈቃድ አውጥተው በሙያቸው ሲሰሩ ቆይተዋል። በሰራ አለም ከ50 ዓመት በላይ የዘለቁት አቶ ተሾመ ገብረማሪያም ከባለቤታቸው ከወይዘሮ አምሳለ መኮንን ፤ ወሰንየለሽ ተሾመን ወልደዋል። አቶ ተሾመ ከአንድ ሳምንት አሰቀድሞ በናሚቢያ ለሥራ ባቀኑበት ሰአት ድንገት በመታመማቸው ባለፈው ዲሴምበር 21/2016 ለሰላት ህይወታቸው ሊያልፍ ችሎአል።

አህያ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ታርዶ ለውጭ ገበያ ሊቀርብ ነው።

መሰረቱ በቻይና ሀገር የሆነና በኢትዮጵያ አህያን አርዶ ቆዳውንና ስጋውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ከኢትዮጵያ መንግሰት ፈቃድ የተሠጠው ሻንግ ዶንግ የተባለ ኩባንያ ከወራት በፊት ለሙከራ በሚል አህያን አርዶ ለገበያ



የማቅረቡን ስራ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ያልተጠናበትና የህገሪቱን ሁኔታ ከግንዛቤ ሳያስገባ የተጀመረ ስራ ነው በሚል የእርድ ስራውን እንዲያቆም ተገደ ነበር።

ፋብሪካው ስለ አሰራሩ በቂ ጥናት ሳይደረግና ከባህላችንና ማህበረሰባችን ጋር ሰለሚኖረው ተቀባይነትም ከግምት ውስጥ ሳይገባ ነው የስራ ፈቃዱ የተሰጠው የተባለ ቢሆንም፣ ፋብሪካው አህያን አርዶ በመርከብም ጭኖ ከኢትዮጵያ ምድር እስኪወጣ ድረስ አንዳችም ችግር እንዳይፈጠርና በኢትዮጵያ መሬት ላይም አንዲትም የአህያ ተረፈ ምርት ጠብታ እንዳይገኝ ተጠንቅቆ እንዲሰራ ትእዛዝ ተሰጥቶት ሥራውን አንዲጀምር ተነግሮታል ተብሏል።

አህያ ከምግብነት ውጪ ለኢትዮጵያ በዕቃ እመላለሽነት ትልቅ ሥፍራ ያለው ሲሆን፤ ዛሬም ድረስ የኢትዮጵያ ገበያዎች የሚተማመኑበት መጓጓዣ አህያ መሆኑ ይታወቃል። ከሰሰት ሚሊዮን በላይ አህዮች መኖራቸውም ሲነገር፣ ባሁኑ ገበያ አንድ አህያ ሶስት ሺህ ብር አንደሚያወጣ ነው የተነገረው።

በቨርጂኒያ ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በተመሳሳይ ወቅት ፤ በተመሳሳይ መንገድ፣ ግን የተለያየ ቦታ ሞተው ተገኙ።

. የፌር ፋክስ ሸርጂኒያ ፖሊስ እንዳስታወቀው፣ የ 22 ዓመቱ ሄኖክ ዮሃንስ በሚኖርበት ቤት ውስጥ ህይወቱ አልፎ ሲገኝ፣ እንዲሁም የ22 አመቷ ቅድስት ስለሺም እንዲሁ ከሄኖክ ቤት በ2 ማይል ርቀት በአንድ ዛፍ ሥር ህይወቷ አልፎ ወደቃ ነው የተገኘችው። ይህ የሆነው ባለፈው ዲሴምበር 24 ቀን ነው።



ፖሊስ እንደሚለው ሁለቱም ከወገባቸው በላይ አስቃቂ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ማን ይህን እንዳደረገ እንዲሁም በትክክል ምን እንደተፈጸመባቸው ለማወቅ ምርመራው ቀጥሏል። ሁለቱ ወጣቶች ይተዋወቁ አይተዋወቁም አስካሁን የተረጋገጠ ነገር የለም። ፖሊስ ምርመራዬን ቀጥያለሁ ፣ መረጃ ያላችሁ ማን ደውሉልኝ ሲል አስታውቋል። አሳዛኝ ታሪክ።



አትሌት ምሩፅ ይፍጠር በካናዳ ቶሮንቶ በሀክምና ሲረዳ ቆይቶ በ72 ዓመቱ አረፈ።

አትሌት ምሩፅ በ1972 ዓ.ም በሞስኮ በተካሄደው ኦሎምፒክ በ10 ሺህ እና 5 ሺህ ሜትር ተወዳድሮ ድርብ ወርቅ ለሀገሩ ማምጣት የቻለ ታሪካዊ አትሌት ነው። ምሩፅ በ1964 ዓመተ ምህረትም በሙኒክ ኦሎምፒክ በ10 ሺህ ሜትር ለሀገሩ የነሐስ ሜዳሊያ ማስገኘት ችሏል።



ከአባቱ አቶ ይፍጠር ተክለሃይማኖትና ከእናቱ ወ/ሮ ለተገብርኤል ገብረአረጋዊ ጥቅምት 5 ቀን 1937 ዓ.ም. በትግራይ፣ ዓዲግራት የተወለደውና በ72 ዓመቱ ያረፈው ምሩፅ ይፍጠር የሰባት ልጆች አባት ነበር ።

በ1,500 ሜትር መወዳደር የጀመረው ምሩፅ 5 ሺሕና 10 ሺሕ መደበኛ ውድድሮቹ ቢሆኑም በጎዳና ላይ ሩጫዎችም ተደጋጋሚ ድሎች ማግኘቱ አይሰተም። በተለይ በተከታታይ ዓመታት ድል የተጎናፀፈበት የፖርቶ ሪኮ ግማሽ ማራቶን ውድድር ለዓለም ክብረ ወሰን የበቃበት ነበር። ጥር 29 ቀን 1969 ዓ.ም. በፖርቶ ሪኮ ኮዓም የ21 ኪሎ ሜትር (ግማሽ ማራቶን) ውድድር ምሩፅና መሐመድ ከድር ተከታትለው ሲያሸንፉ ምሩፅ የገባበት 1 ሰዓት 02 ደቂቃ 57 ሰከንድ ያለም ክብረ ወሰን ሆኖ ተመዝግቦለታል። በ1972 በፖርቶ ሪኮ ግማሽ ማራቶን አሸንፎ እንደተመለሰ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫም ‹‹የማተኩረው በሞስኮ ኦሊምፒክ ስለሆነ በፖርቶ ሪኮው ድሌ አልኮራም›› ማለቱ አይዘነጋም።

በሞስኮ ኦሊምፒክ ለሦስተኛ ጊዜ ድሉን ለማጣጣም ቋምጠ የነበረው ፊንላንዳዊ ላሲ ቪረን በሞስኮ አየሩ ጥሩ ከሆነ እንደሚያሸንፍ መናገሩን ተከትሎ ምሩፅ በሰጠው አፀፋ ‹‹ሐሩርም ይሁን በረዶ እኔ ከማሸነፍ የሚገታኝ አንዳች ኃይል የለም›› ማለቱ ልበ ሙሉነቱን ያሳየበት አጋጣሚ ነበር።

ከሞስኮ ኦሊምፒክ ድሉ በኋላ ጥንታዊ ኦሊምፒክ በተመሠረተባት ግሪክ ለኦሊምፒያዊ ሽልማት ከተመረጡ አምስት አትሌቶች ቀዳሚ ሆኖ የኦሊምፒክ ሎሬት አክሊልን ክርዕሰ ብሔሩ የተቀበለው ምሩፅ ይፍጠር ነበር።

በዓለም ገናና ለሆነው ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ለሞሮኮው ሰዒድ አዊታና ለሌሎችም አርአያ የሆነው ምሩፅ፣ ኢንተርናሽናል አትሌቲክስ ፌደሬሽኖች ማኅበር በ1973 ዓ.ም. በምዕራብ ጀርመን ባደን ባደን ጉባኤውን ሲያካሂድ የዓለም አትሌቶችን ከወከሉ አትሌቶች አንዱ አርሱ ነበር።